# ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ።

(ክለሳ.1.20020507)

___ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። ___

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ በዖዝያንና ፡ በኢዮአታም ፡ በአካዝና ፡ በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ይሁዳና ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ያየው ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ የኢሳይያስ ፡ ራእይ ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ፥ ሰማያት ፡ ስሙ ፥ ምድርም ፡ አድምጪ ፤ ልጆችን ፡ ወለድኹ ፡
አሳደግኹም ፥ እነርሱም ፡ ዐመፁብኝ ።

3 ፤ በሬ ፡ የገዛውን ፡ አህያም ፡ የጌታውን ፡ ጋጣ ፡ ዐወቀ ፤ እስራኤል ፡ ግን ፡ አላወቀም ፥ ሕዝቤም ፡ አላስተዋለም ።

4 ፤ ኀጢአተኛ ፡ ወገንና ፡ በደል ፡ የተሞላበት ፡ ሕዝብ ፥ የክፉዎች ፡ ዘር ፥ ርኵሰትን ፡ የምታደርጉ ፡ ልጆች ፡
ሆይ ፥ ወዮላችኹ! እግዚአብሔርን ፡ ትተዋል ፡ የእስራኤልንም ፡ ቅዱስ ፡ አቃለዋል ፥ ወደ ፡ ኋላቸውም ፡ እየኼዱ ፡
ተለይተዋል ።

5 ፤ ደግሞስ ፡ ዐመፃ ፡ እየጨመራችኹ ፡ ለምን ፡ ገና ፡ ትቀሰፋላችኹ ፧ ራስ ፡ ኹሉ ፡ ለሕመም ፥ ልብም ፡ ኹሉ ፡
ለድካም ፡ ኾኗል ።

6 ፤ ከእግር ፡ ጫማ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ድረስ ፡ ጤና ፡ የለውም ፤ ቍስልና ፡ ዕበጥ ፡ የሚመግልም ፡
ነው ፤ አልፈረጠም ፥ አልተጠገነም ፥ በዘይትም ፡ አልለዘበም ።

7 ፤ ምድራችኹ ፡ ባድማ ፡ ናት ፤ ከተማዎቻችኹ ፡ በእሳት ፡ ተቃጠሉ ፤ ዕርሻችኹንም ፡ በፊታችኹ ፡ ሌላዎች ፡
ይበሉታል ፤ ባዕድ ፡ እንዳፈረሳት ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ ኾነች ።

8 ፤ የጽዮንም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በወይን ፡ ቦታ ፡ እንዳለ ፡ ዳስ ፥ በዱባ ፡ አትክልትም ፡ እንዳለ ፡ ጐጕ ፥ አንደ ፡ ተከበበችም ፡
ከተማ ፡ ኾና ፡ ቀረች ።

9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘርን ፡ ባያስቀርልን ፡ ኖሮ ፥ እንደ ፡ ሰዶም ፡ በኾንነ ፡ እንደ ፡ ገሞራም ፡ በመሰልነ ፡
ነበር ።

10 ፤ እናንተ ፡ የሰዶም ፡ አለቃዎች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ እናንተ ፡ የገሞራ ፡ ሕዝብ ፡
ሆይ ፥ የአምላካችንን ፡ ሕግ ፡ አድምጡ ።

11 ፤ የመሥዋዕታችኹ ፡ ብዛት ፡ ለእኔ ፡ ምን ፡ ይጠቅመኛል ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የሚቃጠለውን ፡ የአውራ ፡ በግ ፡
መሥዋዕትንና ፡ የፍሪዳን ፡ ስብ ፡ ጠግቤያለኹ ፤ የበሬና ፡ የበግ ፡ ጠቦት ፡ የአውራ ፡ ፍየልም ፡ ደም ፡ ደስ ፡ አያሠኝኝም ።

12 ፤ በእኔ ፡ ፊት ፡ ልትታዩ ፡ ብትመጡ ፡ ይህን ፡ የመቅደሴን ፡ አደባባይ ፡ መርገጣችኹን ፡ ከእጃችኹ ፡ የሚሻ ፡ ማን ፡
ነው ፧

13 ፤ ምናምንቴውን ፡ ቍርባን ፡ ጨምራችኹ ፡ አታምጡ ፤ ዕጣን ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አጸያፊ ፡ ነው ፤ መባቻችኹንና ፡
ሰንበታችኹን ፡ በጉባኤ ፡ መሰብሰባችኹን ፡ አልወድም ፤ በደልንም ፡ የተቀደሰውንም ፡ ጉባኤ ፡ አልታገሥም ።

14 ፤ መባቻችኹንና ፡ በዓላቶቻችኹን ፡ ነፍሴ ፡ ጠልታለች ፤ ሸክም ፡ ኾነውብኛል ፥ ልታገሣቸውም ፡ ደክሜያለኹ ።

15 ፤ እጃችኹንም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ብትዘረጉ ፡ ዐይኔን ፡ ከእናንተ ፡ እሰውራለኹ ፥ ልመናንም ፡ ብታበዙ ፡
አልሰማችኹም ፤ እጆቻችኹ ፡ ደም ፡ ተሞልተዋል ።

16 ፤ ታጠቡ ፡ ሰውነታችኹንም ፡ አንጹ ፤ የሥራችኹን ፡ ክፋት ፡ ከዐይኔ ፡ ፊት ፡ አስወግዱ ፤ ክፉ ፡ ማድረግን ፡ ተዉ ፥

17 ፤ መልካም ፡ መሥራትን ፡ ተማሩ ፥ ፍርድን ፡ ፈልጉ ፥ የተገፋውን ፡ አድኑ ፥ ለድኻ ፡ አደጉ ፡ ፍረዱለት ፡ ስለ ፡



www.ethiopianorthodox.org

መበለቲቱም ፡ ተሟገቱ ።

18 ፤ ኑና ፡ እንዋቀስ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ኀጢአታችኹ ፡ እንደ ፡ ዐለላ ፡ ብትኾን ፡ እንደ ፡ ዐመዳይ ፡ ትነጻለች ፤ እንደ ፡ ደምም ፡ ብትቀላ ፡ እንደ ፡ ባዘቶ ፡ ትጠራለች ።

19 ፤ ዕሺ ፡ ብትሉ ፡ ለኔም ፡ ብትታዘዙ ፥ የምድርን ፡ በረከት ፡ ትበላላችኹ ፤

20 ፤ እምቢ ፡ ብትሉ ፡ ግን ፡ ብታምፁም ፥ ሰይፍ ፡ ይበላችኋል ፤ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ተናግሯልና ፦

21 ፤ ፍርድ ፡ ሞልቶባት ፡ የነበረው ፡ የታመነችዪቱ ፡ ከተማ ፡ እንዴት ፡ ጋለሞታ ፡ ኾነች! ጽድቅ ፡ ዐድሮባት ፡ ነበር ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ገዳዮች ፡ አሉባት ።

22 ፤ ብርሽ ፡ ወደ ፡ ዝገት ፡ ተለወጠ ፤ የወይን ፡ ጠጅሽ ፡ ከውሃ ፡ ጋራ ፡ ተደባለቀ ።

23 ፤ አለቃዎችሽ ፡ ዐመፀኛዎችና ፡ የሌቦች ፡ ባልንጀራዎች ፡ ኾኑ ፤ ዅሉ ፡ ጉቦ ፡ ይወዳሉ ፥ ዋጋም ፡ ለማግኘት ፡ ይሮጣሉ ፤ ለድኻ ፡ አደጉ ፡ አይፈርዱም ፥ የመበለቲቱም ፡ ሙግት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አይደርስም ።

24 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ ኀያል ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ ቍጣዬን ፡ እፈጽማለኹ ፥ የሚቋቋሙኝንም ፡ እበቀላለኹ ።

25 ፤ እጄንም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፥ ዝገትሽንም ፡ በጣም ፡ አነጻለኹ ፥ ቈርቈሮሽንም ፡ ዅሉ ፡ አወጣለኹ ፤

26 ፤ ፈራጆችሽንም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ አማካሪዎችሽንም ፡ እንደ ፡ መዠመሪያው ፡ ጊዜ ፡ መልሼ ፡ አስነሣለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የጽድቅ ፡ ከተማ ፡ የታመነችም ፡ ከተማ ፡ ተብለሽ ፡ ትጠሪያለሽ ።

27 ፤ ጽዮን ፡ በፍርድ ፡ ከርሷም ፡ የሚመለሱ ፡ በጽድቅ ፡ ይድናሉ ።

28 ፤ በደለኛዎችና ፡ ኀጢአተኛዎች ፡ ግን ፡ በአንድነት ፡ ይሰበራሉ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚተዉ ፡ ይጠፋሉ ።

29 ፤ በወደዳችኋት ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ ታፍራላችኹና ፥ ስለ ፡ መረጣችኋትም ፡ አትክልት ፡ ዕፍረት ፡ ይይዛችኋልና ፤

30 ፤ ቅጠሏ ፡ እንደ ፡ ረገፈ ፡ ዛፍ ፥ ውሃም ፡ እንደሌለባት ፡ አትክልት ፡ ትኾናላችኹና ።

31 ፤ ኀይለኛውም ፡ እንደ ፡ ተልባ ፡ ጭረት ፥ ሥራውም ፡ እንደ ፡ ጠለሸት ፡ ይኾናል ፤ ዐብረውም ፡ ይቃጠላሉ ፡ እነርሱንም ፡ የሚያጠፋ ፡ የለም ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ ይሁዳና ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያየው ፡ ቃል ።

2 ፤ በዘመኑም ፡ ፍጻሜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተራራ ፡ በተራራዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ይቆማል ፥ ከኰረብታዎችም ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፥ አሕዛብም ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይሰበሰባሉ ።

3 ፤ ሕግ ፡ ከጽዮን ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይወጣልና ፥ ብዙዎች ፡ አሕዛብ ፡ ኼደው ፦ ኑ ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፥ ወደያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ቤት ፡ እንውጣ ፤ ርሱም ፡ መንገዱን ፡ ያስተምረናል ፥ በጐዳናውም ፡ እንኼዳለን ፡ ይላሉ ።

4 ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ይፈርዳል ፥ በብዙ ፡ አሕዛብም ፡ ላይ ፡ ይበይናል ፤ ሰይፋቸውንም ፡ ማረሻ ፡ ጦራቸውንም ፡ ማጭድ ፡ ለማድረግ ፡ ይቀጠቅጣሉ ፤ ሕዝብም ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ሰይፍ ፡ አያነሣም ፥ ሰልፍም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይማሩም ።

5 ፤ እናንተ ፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ኑ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ እንኺድ ።

6 ፤ ሕዝብኽን ፡ የያዕቆብን ፡ ቤት ፡ ትተኻልና ፤ ይኸውም ፡ የምሥራቅን ፡ ሰዎች ፡ ዐመል ፡ ስለ ፡ ተሞሉ ፥ እንደ ፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ሟርተኛዎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ከባዕድ ፡ ልጆችም ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተባበሩ ፡ ነው ።

7 ፤ ምድራቸው ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ ተሞልታለች ፥ ለመዛግብቶቻቸውም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፤ ምድራቸውም ፡ ደግሞ ፡ በፈረሶች ፡ ተሞልታለች ፥ ለሠረገላዎቻቸውም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ።



www.ethiopianorthodox.org

8 ፤ ምድራቸው ፡ ደግሞ ፡ በጣዖታት ፡ ተሞልታለች ፤ ጣቶቻቸውም ፡ ላደረጉት ፡ ለእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ይሰግዳሉ ።

9 ፤ ታናሹም ፡ ሰው ፡ ዝቅ ፡ ብሏል ፥ ጨዋውም ፡ ተዋርዷል ፤ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቅር ፡ አትበላቸው ።

10 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ማስደንገጥና ፡ ከግርማው ፡ ክብር ፡ የተነሣ ፡ ወደድንጋይ ፡ ዋሻ ፡ ግባ ፥ በመሬትም ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸግ ።

11 ፤ ከፍ ፡ ያለችውም ፡ የሰው ፡ ዐይን ፡ ትዋረዳለች ፥ የሰዎችም ፡ ኵራት ፡ ትወድቃለች ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

12 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ በትዕቢተኛውና ፡ በኵራተኛው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ባለውም ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ ርሱም ፡ ይዋረዳል ፤

13 ፤ ደግሞም ፡ በረዥሙ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ በሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ በባሳንም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥

14 ፤ በረዥሙም ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ ከፍ ፡ ባለውም ፡ ኰረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥

15 ፤ በረዥሙም ፡ ግንብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ በተመሸገውም ፡ ቅጥር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥

16 ፤ በተርሴስም ፡ መርከብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ በሚያማምሩ ፡ ጣዖታትም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

17 ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ይዋረዳል ፥ የሰውም ፡ ኵራት ፡ ይወድቃል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

18 ፤ ጣዖቶቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ።

19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምድርን ፡ ያናውጥ ፡ ዘንድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፥ ሰዎች ፡ ከማስደንገጡና ፡ ከግርማው ፡ ክብሩ ፡ የተነሣ ፥ ወደድንጋይ ፡ ዋሻና ፡ ወደምድር ፡ ንቃቃት ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

20 ፤ በዚያን ፡ ቀን ፡ ሰው ፡ ይሰግድላቸው ፡ ዘንድ ፡ ያበጃቸውን ፡ የብሩንና ፡ የወርቁን ፡ ጣዖቶቹን ፡ ለፍልፈልና ፡ ለሌሊት ፡ ወፍ ፡ ይጥላል ።

21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምድርን ፡ ያናውጥ ፡ ዘንድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ከማስደንገጡና ፡ ከግርማው ፡ ክብር ፡ የተነሣ ፡ ወደድንጋይ ፡ ዋሻና ፡ ወደተሰነጠቁ ፡ አለቶች ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

22 ፤ እስትንፋሱ ፡ በአፍንጫው ፡ ውስጥ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ተዉት ፤ ርሱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይቈጠራል ፡፡

________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ እንሆ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኢየሩሳሌምና ፡ ከይሁዳ ፡ ድጋፍንና ፡ ብርታትን ፥ የእንጀራን ፡ ድጋፍ ፡ ኹሉ ፡ የውሃውንም ፡ ድጋፍ ፡ ኹሉ ፥

2 ፤ ኀያሉንም ፥ ተዋጊውንም ፥ ፈራጁንም ፥ ነቢዩንም ፥ ሟርተኛውንም ፥

3 ፤ ሸማግሌውንም ፥ የዐምሳ ፡ አለቃውንም ፥ ከበርቴውንም ፥ አማካሪውንም ፥ ብልኁንም ፡ ሠራተኛ ፥ አስማት ፡ ዐዋቂውንም ፡ ይነቅላል ።

4 ፤ አለቃዎቻቸው ፡ እንዲኾኑ ፡ ብላቴናዎችን ፡ አስነሣባቸዋለኹ ፥ ሕፃናትም ፡ ይገዟቸዋል ።

5 ፤ ሕዝቡም ፥ ሰው ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ሰውም ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፥ ይገፋፋል ፤ ብላቴናውም ፡ በሽማግሌው ፡ ላይ ፡ የተጠቃውም ፡ በከበርቴው ፡ ላይ ፡ ይኰራል ።

6 ፤ ሰውም ፡ በአባቱ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ወንድሙን ፡ ይዞ ፦ አንተ ፡ ልብስ ፡ አለኽ ፡ አለቃም ፡ ኹንልን ፡ ይህችም ፡ ባድማ ፡ ከእጅኽ ፡ በታች ፡ ትኹን ፡ ሲለው ፥

7 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፦ እኔ ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ የለኝምና ፡ ባለመድኀኒት ፡ አልኾንም ፤ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አታደርጉኝም ፡ ይላል ።



www.ethiopianorthodox.org

8 ፤ የክብሩን ፡ ዐይን ፡ ያስቈጡ ፡ ዘንድ ፡ ምላሳቸውና ፡ ሥራቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ ኢየሩሳሌም ፡ ተፈታች ፥ ይሁዳም ፡ ወደቀ ።

9 ፤ የፊታቸውም ፡ ዕፍረት ፡ ይመሰክርባቸዋል ፤ እንደ ፡ ሰዶምም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ያወራሉ ፥ አይሰውሯትም ። በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ሠርተዋልና ፥ ለነፍሳቸው ፡ ወዮ!

10 ፤ የሥራቸውን ፡ ፍሬ ፡ ይበላሉና ፡ ጻድቁን ፦ መልካም ፡ ይኾንልኻል ፡ በሉት ።

11 ፤ እንደ ፡ እጁ ፡ ሥራ ፡ ፍዳው ፡ ይደረግበታልና ፥ ለበደለኛ ፡ ወዮ! ክፉም ፡ ደርሶበታል ።

12 ፤ ሕዝቤንስ ፡ አስገባሪዎቻቸው ፡ ይገፏቸዋል ፥ አስጨናቂዎችም ፡ ይሠለጥኑባቸዋል ። ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ የመሯችኹ ፡ ያስቷች኿ል ፡ የምትኼዱበትንም ፡ መንገድ ፡ ያጠፋሉ ።

13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለፍርድ ፡ ተነሥቷል ፡ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ ሊፈርድ ፡ ቆሟል ።

14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ከአለቃዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይፋረዳል ፤ የወይኑን ፡ ቦታ ፡ የጨረሳችኹ ፡ እናንተ ፡ ናችኹ ፤ ከድኻዎች ፡ የበዘበዛችኹት ፡ በቤታችኹ ፡ አለ ፤

15 ፤ ሕዝቤንም ፡ ለምን ፡ ታደቋቸዋላችኹ ፤ የድኻዎችንስ ፡ ፊት ፡ ለምን ፡ ትፈጫላችኹ ፤ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

16 ፤ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የጽዮን ፡ ቈነጃጅት ፡ ኰርተዋልና ፥ ዐንገታቸውንም ፡ እያሰገጉ ፡ በዐይናቸውም ፡ እያጣቀሱ ፥ ፈንጠርም ፡ እያሉ ፥ በእግራቸውም ፡ እያቃጨሉ ፡ ይኼዳሉና ፥

17 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ የጽዮንን ፡ ቈነጃጅት ፡ ዐናት ፡ በቡሓነት ፡ ይመታል ፥ እግዚአብሔርም ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋቸውን ፡ ይገልጣል ።

18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ጌታ ፡ የእግር ፡ አልቦውን ፡ ክብር ፥ መርበብንም ፥ ጨረቃ ፡ የሚመስለውንም ፡ ጌጥ ፥ የጕሮ ፡ እንጥልጥሉንም ፥

19 ፤ አንባሩንም ፥ መሸፈኛውንም ፥ ቀጸላውንም ፥

20 ፤ ሰንሰለቱንም ፥ መቀነቱንም ፥ የሽቱውንም ፡ ዕቃ ፥

21 ፤ ዐሸን ፡ ክታቡንም ፥ የእጅና ፡ የአፍንጫ ፡ ቀለበቱንም ፥

22 ፤ የዓመት ፡ በዓልንም ፡ ልብስ ፥ መጐናጸፊያውንም ፥ ልግም ፡ በገላውንም ፥ ከረጢቱንም ፥

23 ፤ መስተዋቱንም ፥ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ የተሠራውንም ፡ ልብስ ፥ ራስ ፡ ማሰሪያውንም ፥ ዐይነ ፡ ርግቡንም ፡ ያስወግዳል ።

24 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ በሽቱ ፡ ፋንታ ፡ ግማት ፥ በመታጠቂያውም ፡ ፋንታ ፡ ገመድ ፥ ጠጕርንም ፡ በመንቀስ ፡ ፋንታ ፡ ቡሓነት ፥ በመጐናጸፊያ ፡ ፋንታ ፡ ማቅ ፥ በውበትም ፡ ፋንታ ፡ ጠባሳ ፡ ይኾናል ።

25 ፤ ጕልማሳዎችሽ ፡ በሰይፍ ፥ ኀያላንሽም ፡ በውጊያ ፡ ይወድቃሉ ።

26 ፤ በሮቿ ፡ ያዝናሉ ፡ ያለቅሱማል ፤ ርሷም ፡ ብቻዋን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ትቀመጣለች ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ሴቶች ። የገዛ ፡ እንጀራችንን ፡ እንበላለን ፡ የገዛ ፡ ልብሳችንንም ፡ እንለብሳለን ፤ ስምኽ ፡ ብቻ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ይጠራ ፥ መሰደባችንንም ፡ አርቅ ፡ ብለው ፡ አንዱን ፡ ወንድ ፡ ይይዙታል ።

2 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጥቋጥ ፡ ለጌጥና ፡ ለክብር ፡ ይኾናል ፥ ከእስራኤልም ፡ ወገን ፡ ላመለጡ ፡ ሰዎች ፡ የምድሪቱን ፡ ፍሬ ፡ ለትምክሕትና ፡ ለውበት ፡ ይኾናል ።

3 ፤ 4 ፤ ጌታም ፡ የጽዮንን ፡ ቈነጃጅት ፡ እድፍ ፡ ባጠበ ፡ ጊዜ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ደም ፡ በፍርድ ፡ መንፈስና ፡ በሚያቃጥል ፡ መንፈስ ፡ ከመካከሏ ፡ ባነጻ ፡ ጊዜ ፥ በጽዮን ፡ የቀረ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የተረፈ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ለሕይወት ፡ የተጻፈ ፡ ኹሉ ፥ ቅዱስ ፡ ይባላል ።



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ማደሪያ ፡ ኹሉ ፡ በጉባኤያቸውም ፡ ላይ ፡ በቀን ፡ ዳመናንና ፡ ጢስን ፡ በሌሊትም ፡ የሚቃጠለውን ፡ የእሳት ፡ ብርሃን ፡ ይፈጥራል ፤ በክብርም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ መጋረጃ ፡ ይኾናል ።

6 ፤ በቀን ፡ ከሙቀት ፡ ለጥላ ፥ ከዐውሎ ፡ ነፋስና ፡ ከዝናብም ፡ ለመጠጊያና ፡ ለመሸሸጊያ ፡ ጐጆ ፡ ይኾናል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ አኹን ፡ ስለ ፡ ወዳጄና ፡ ስለወይን ፡ ቦታው ፡ ለወዳጄ ፡ ቅኔ ፡ እቀኛለኹ ። ለወዳጄ ፡ በፍሬያማው ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ነበረው ።

2 ፤ በዙሪያው ፡ ቈፈረ ፥ ድንጋዮችንም ፡ ለቅሞ ፡ አወጣ ፥ ምርጥ ፡ የኾነውንም ፡ ዐረግ ፡ ተከለበት ፥ በመካከሉም ፡ ግንብ ፡ ሠራ ፥ ደግሞም ፡ የመጥመቂያ ፡ ጕድጓድ ፡ ማሰበት ፤ ወይንንም ፡ ያፈራ ፡ ዘንድ ፡ ተማመነ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሖምጣጣ ፡ ፍሬ ፡ አፈራ ።

3 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩ ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ በእኔና ፡ በወይኑ ፡ ቦታዬ ፡ መካከል ፡ እስኪ ፡ ፍረዱ ።

4 ፤ ለወይኔ ፡ ያላደረግኹለት ፥ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ አደርግለት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ወይንን ፡ ያፈራል ፡ ብዬ ፡ ስተማመን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሖምጣጣ ፡ ፍሬ ፡ አፈራ ፧

5 ፤ አኹንም ፡ በወይኔ ፡ ላይ ፡ የማደርገውን ፡ እነግራችኋለኹ ፤ ዐጥሩን ፡ እነቅላለኹ ፥ ለማሰማሪያም ፡ ይኾናል ፤ ቅጥሩንም ፡ አፈርሳለኹ ፥ ለመራገጫም ፡ ይኾናል ።

6 ፤ ባድማ ፡ አደርገዋለኹ ፤ አይቈረጥም ፥ አይኰተኰትም ፤ ኵርንችትና ፡ ሾኽ ፡ ይበቅልበታል ፤ ዝናብንም ፡ እንዳያዘንቡበት ፡ ዳመናዎችን ፡ አዝዛለኹ ።

7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ ርሱ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ነው ፥ የደስታውም ፡ አትክልት ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ ፍርድን ፡ ተስፋ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፥ እንሆም ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ኾነ ፤ ጽድቅንም ፡ ይተማመን ፡ ነበር ፥ እንሆም ፥ ጩኸት ፡ ኾነ ።

8 ፤ ስፍራ ፡ እስከማይቀር ፡ ድረስ ፡ እናንተም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ብቻችኹን ፡ እስክትቀመጡ ፡ ድረስ ፥ ቤትን ፡ ከቤት ፡ ጋራ ፡ ለሚያያይዙ ፡ ዕርሻንም ፡ ከዕርሻ ፡ ጋራ ፡ ለሚያቀራርቡ ፡ ወዮላቸው!

9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጆሮዬ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በእውነት ፡ ብዙ ፡ ታላቅና ፡ መልካም ፡ ቤት ፡ ባድማ ፡ ይኾናል ፥ የሚቀመጥበትም ፡ አይገኝም ።

10 ፤ ከወይኑ ፡ ቦታ ፡ ዐሥር ፡ ጥማድ ፡ በሬ ፡ ካረሰው ፡ አንድ ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ብቻ ፡ ይወጣል ፤ አንድ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ብቻ ፡ ይሰጣል ።

11 ፤ ስካርን ፡ ለመከተል ፡ በጧት ፡ ለሚማልዱ ፥ የወይን ፡ ጠጅም ፡ እስኪያቃጥላቸው ፡ እስከ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡ ለሚዘገዩ ፡ ወዮላቸው!

12 ፤ መሰንቆና ፡ በገና ፡ ከበሮና ፡ እንቢልታም ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ በግብዣቸው ፡ አለ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ አልተመለከቱም ፥ እጁም ፡ ያደረገችውን ፡ አላስተዋሉም ።

13 ፤ ስለዚህ ፥ ሕዝቤ ፡ ወደ ፡ ምርኮ ፡ ኼዱ ፥ ጌታን ፡ አላወቁትምና ፤ ከበርቴዎቻቸውም ፡ ተራቡ ፥ ሕዝባቸውም ፡ ተጠሙ ።

14 ፤ ሲኦልም ፡ ሆዷን ፡ አስፍታለች ፥ አፏንም ፡ ያለልክ ፡ ከፍታለች ፤ ከበርቴዎቻቸውና ፡ ዐዛውንቶቻቸው ፡ ባለጠጋዎቻቸውም ፡ ደስተኛዎቻቸውም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ይወርዳሉ ።

15 ፤ ሰውም ፡ ይጐሰቈላል ፥ ሰውም ፡ ይዋረዳል ፥ የትዕቢተኛዎችም ፡ ዐይን ፡ ትዋረዳለች ፤

16 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በፍርድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏል ፥ ቅዱሱም ፡ አምላክ ፡ በጽድቅ ፡ ተቀድሷል ።

17 ፤ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ በማሰማሪያቸው ፡ ውስጥ ፡ ይሰማራሉ ፥ እንግዳዎችም ፡ የሰቡትን ፡ ባድማ ፡ ይበላሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

18 ፤ በደልን ፡ በምናምንቴ ፡ ገመድ ፥ ኀጢአትንም ፡ በሠረገላ ፡ ማሰሪያ ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ለሚስቡ ፦ እናይ ፡ ዘንድ ፡
ይቸኵል ፥

19 ፤ ሥራውንም ፡ ያፋጥን ፤ እናውቃትም ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ምክር ፡ ትቅረብ ፥ ትምጣ ፡ ለሚሉ ፡ ወዮላቸው!

20 ፤ ክፉውን ፡ መልካም ፡ መልካሙን ፡ ክፉ ፡ ለሚሉ ፥ ጨለማውን ፡ ብርሃን ፡ ብርሃኑንም ፡ ጨለማ ፡
ለሚያደርጉ ፥ ጣፋጩን ፡ መራራ ፡ መራራውንም ፡ ጣፋጭ ፡ ለሚያደርጉ ፡ ወዮላቸው!

21 ፤ በዐይናቸው ፡ ጥበበኛዎች ፡ በነፍሳቸውም ፡ አስተዋዮች ፡ ለኾኑ ፡ ወዮላቸው!

22 ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጣት ፡ ኀያላን ፡ የሚያሰክረውንም ፡ ለማደባለቅ ፡ ጨካኞች ፡ ለኾኑ ፤

23 ፤ በደለኛውን ፡ ስለ ፡ ጉቦ ፡ ጻድቅ ፡ ለሚያደርጉ ፥ የጻድቁንም ፡ ጽድቅ ፡ ለሚያስወግዱበት ፡ ወዮላቸው!

24 ፤ ስለዚህ ፥ የእሳት ፡ ወላፈን ፡ ቃርሚያን ፡ እንደሚበላ ፥ እብቅም ፡ በነበልባል ፡ ውስጥ ፡ እንደሚጠፋ ፥ እንዲሁ ፡
የእነርሱ ፡ ሥር ፡ የበሰበሰ ፡ ይኾናል ፥ ቡቃያቸውም ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፡ ይበናል ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡
ጥለዋልና ፥ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አቃለዋልና ።

25 ፤ ስለዚህ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ነዷል ፥ እጁንም ፡ በላያቸው ፡ ዘርግቶ ፡
መትቷቸዋል ፤ ተራራዎችም ፡ ተንቀጠቀጡ ፥ ሬሳቸውም ፡ በአደባባይ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ኾኗል ። በዚህም ፡
ኹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

26 ፤ ለአሕዛብም ፡ በሩቅ ፡ ምልክትን ፡ ያቆማል ፥ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ በፉጨት ፡ ይጠራቸዋል ፤ እንሆም ፥ እየተጣደፉ ፡
ፈጥነው ፡ ይመጣሉ ።

27 ፤ ደካማና ፡ ስንኵል ፡ የለባቸውም ፥ የሚያንቀላፋና ፡ የሚተኛም ፡ የለም ፤ የወገባቸውም ፡ መቀነት ፡
አይፈታም ፥ የጫማቸውም ፡ ማዘቢያ ፡ አይበጠስም ።

28 ፤ ፍላጻዎቻቸው ፡ ተስለዋል ፥ ቀስቶቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ተለጥጠዋል ፤ የፈረሶቻቸውም ፡ ኰቴ ፡ እንደ ፡ ቡላድ ፡
የሠረገላዎቻቸውም ፡ መንኰራኵር ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይቈጠራል ።

29 ፤ ጩኸታቸው ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ነው ፥ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ደቦሎችም ፡ ያገሣሉ ፤ ንጥቂያንም ፡ ይዘው ፡
ያገሣሉ ፥ ይወስዱትማል ፥ የሚያድንም ፡ የለም ።

30 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ መትመም ፡ ይተምሙባቸዋል ፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ ቢመለከቱ ፥ እንሆ ፥ ጨለማና ፡
መከራ ፡ አለ ፤ ብርሃንም ፡ በደመናዎቿ ፡ ውስጥ ፡ ጨልሟል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

## ምዕራፍ ፡ 6 ።

1 ፤ ንጉሡ ፡ ዖዝያን ፡ በሞተበት ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በረዥምና ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡
አየኹት ፥ የልብሱም ፡ ዘርፍ ፡ መቅደሱን ፡ ሞልቶት ፡ ነበር ።

2 ፤ ሱራፌልም ፡ ከርሱ ፡ በላይ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ ለያንዳንዱም ፡ ስድስት ፡ ክንፍ ፡ ነበረው ፤ በኹለት ፡ ክንፍ ፡ ፊቱን ፡
ይሸፍን ፡ ነበር ፥ በኹለቱም ፡ ክንፍ ፡ እግሮቹን ፡ ይሸፍን ፡ ነበር ፥ በኹለቱም ፡ ክንፍ ፡ ይበር ፡ ነበር ።

3 ፤ አንዱም ፡ ለአንዱ ፦ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ከክብሩ ፡
ተሞልታለች ፡ እያለ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ።

4 ፤ የመድረኩም ፡ መሠረት ፡ ከጯኺው ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ተናወጠ ፥ ቤቱንም ፡ ጢስ ፡ ሞላበት ።

5 ፤ እኔም ፦ ከንፈሮቼ ፡ የረከሱብኝ ፡ ሰው ፡ በመኾኔ ፥ ከንፈሮቻቸውም ፡ በረከሱባቸው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡
በመቀመጤ ፡ ዐይኖቼ ፡ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ ንጉሡን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ አዩ ፡ ጠፍቻለኹና ፡ ወዮልኝ! አልኹ ።

6 ፤ ከሱራፌልም ፡ አንዱ ፡ እየበረረ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፥ በእጁም ፡ ከመሠዊያው ፡ በጕጠት ፡ የወሰደው ፡ ፍም ፡ ነበረ ።

7 ፤ አፌንም ፡ ዳሰሰበትና ፦ እንሆ ፥ ይህ ፡ ከንፈሮችኽን ፡ ነክቷል ፤ በደልኽም ፡ ከአንተ ፡ ተወገደ ፥ ኀጢአትኽም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ተሰረየልኽ ፡ አለኝ ።

8 ፤ የጌታንም ፡ ድምፅ ፦ ማንን ፡ እልካለኹ ፧ ማንስ ፡ ይኼድልናል ፧ ሲል ፡ ሰማኹ ። እኔም ፦ እንሆኝ ፥ እኔን ፡ ላከኝ ፡
አልኹ ።

9 ፤ ርሱም ፦ ኺድ ፥ ይህን ፡ ሕዝብ ፦ መስማትን ፡ ትሰማላችኹ ፡ አታስተውሉምም ፤ ማየትንም ፡ ታያላችኹ ፡
አትመለከቱምም ፡ በላቸው ።

10 ፤ በዐይናቸው ፡ እንዳያዩ ፥ በዦሯቸውም ፡ እንዳይሰሙ ፥ በልባቸውም ፡ እንዳያስተውሉ ፥ ተመልሰውም ፡
እንዳይፈወሱ ፥ የዚህን ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ አደንድን ፥ ዦሯቸውንም ፡ አደንቍር ፥ ዐይናቸውንም ፡ ጨፍን ፡ አለኝ ።

11 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፧ አልኹ ። ርሱም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ከተማዎች ፡
የሚኖርባቸውን ፡ ዐጥተው ፡ እስኪፈርሱ ፡ ድረስ ፥ ቤቶችም ፡ ሰው ፡ አልቦ ፡ እስኪኾኑ ፡ ምድርም ፡ ፈጽሞ ፡ ባድማ ፡ ኾና ፡
እስክትቀር ፡ ድረስ ፥

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰዎችን ፡ እስኪያርቅ ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡ ውድማው ፡ መሬት ፡ እስኪበዛ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

13 ፤ በርሷም ፡ ዘንድ ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይቃጠላል ፤ በተቈረጡ ፡ ጊዜ ፡ ጕቶቻቸው ፡
እንደ ፡ ቀሩ ፡ እንደ ፡ ግራርና ፡ እንደ ፡ ኮምበል ፡ ዛፍ ፡ ኾኖ ፥ ጕቶው ፡ የተቀደሰ ፡ ዘር ፡ ይኾናል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ምዕራፍ ፡ 7 ።

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዖዝያን ፡ ልጅ ፡ በኢዮአታም ፡ ልጅ ፡ በአካዝ ፡ ዘመን ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡
ረአሶን ፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ሊወጉ ፡ ወጡ ፥ ሊያሸንፏትም ፡ አልቻሉም ።

2 ፤ ለዳዊትም ፡ ቤት ፦ ሶርያ ፡ ከኤፍሬም ፡ ጋራ ፡ ተባብረዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ተነገረ ፤ የርሱም ፡ ልብ ፡ የሕዝቡም ፡
ልብ ፡ የዱር ፡ ዛፍ ፡ በነፋስ ፡ እንድትናወጥ ፡ ተናወጠ ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢሳይያስን ፡ አለው ፦ አንተና ፡ ልጅኽ ፡ ያሱብ ፡ አካዝን ፡ ትገናኙት ፡ ዘንድ ፡ በልብስ ፡ ዐጣቢው ፡
ዕርሻ ፡ መንገድ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ የኵሬ ፡ መስኖ ፡ ጫፍ ፡ ውጡ ፤

4 ፤ እንዲህም ፡ በለው ፦ ተጠበቅ ፥ ዝምም ፡ በል ፤ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ስለሚጤሱ ፡ ስለ ፡ ኹለት ፡ የዕንጨት ፡
ጠለሸቶች ፥ ስለ ፡ ሶርያና ፡ ስለ ፡ ረአሶን ፡ ስለ ፡ ሮሜልዩም ፡ ልጅ ፡ ቍጣ ፡ አትፍራ ፥ ልብኽም ፡ አይድከም ።

5 ፤ 6 ፤ ሶርያና ፡ ኤፍሬም ፣ የሮሜልዩም ፡ ልጅ ፦ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ እንውጣ ፡
እናስጨንቀውም ፥ እንስበረውም ፥ የጣብኤልንም ፡ ልጅ ፡ እናንግሥበት ፡ ብለው ፡ ክፉት ፡ ስለ ፡ መከሩብኽ ፤

7 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ምክር ፡ አይጸናምና ፥ አይኾንም ።

8 ፤ የሶርያ ፡ ራስ ፡ ደማስቆ ፡ ነው ፥ የደማስቆም ፡ ራስ ፡ ረአሶን ፡ ነው ፤ በስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ኤፍሬም ፡
ይሰባበራልና ፥ ሕዝብ ፡ አይኾንም ፤

9 ፤ የኤፍሬምም ፡ ራስ ፡ ሰማርያ ፡ ነው ፥ የሰማርያም ፡ ራስ ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ባታምኑ ፡ አትጸኑም ።

10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ አካዝን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

11 ፤ ከጥልቁ ፡ ወይም ፡ ከከፍታው ፡ ቢኾን ፡ ከአምላክኽ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ምልክትን ፡ ለምን ።

12 ፤ አካዝም ፦ አልለምንም ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አልፈ̇ታተንም ፡ አለ ።

13 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ እናንተ ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ስሙ ፤ በእውኑ ፡ ሰውን ፡ ማድከማችኹ ፡ ቀላል ፡
ነውን ፧ አምላኬን ፡ ደግሞ ፡ የምታደክሙ ፤

14 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ ራሱ ፡ ምልክት ፡ ይሰጣችኋል ፤ እንሆ ፥ ድንግል ፡ ትፀንሳለች ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡
ትወልዳለች ፥ ስሙንም ፡ ዐማኑኤል ፡ ብላ ፡ ትጠራዋለች ።

15 ፤ ክፉን ፡ ለመጥላት ፡ መልካሙንም ፡ ለመምረጥ ፡ ሲያውቅ ፡ ቅቤና ፡ ማር ፡ ይበላል ።



www.ethiopianorthodox.org

16 ፤ ሕፃኑ ፡ ክፉን ፡ ለመጥላት ፡ መልካሙን ፡ ለመምረጥ ፡ ሳያውቅ ፡ የፈራኻቸው ፡ የኹለቱ ፡ ነገሥታት ፡ አገር ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ።

17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኤፍሬም ፡ ከይሁዳ ፡ ከተለየበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ያልመጣውን ፡ ዘመን ፡ በአንተና ፡ በሕዝብኽ ፡ በአባትኽም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ያመጣል ፤ ርሱም ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ መምጣት ፡ ነው ።

18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ዳርቻ ፡ ያለውን ፡ ዝምብ ፡ በአሶርም ፡ አገር ፡ ያለውን ፡ ንብ ፡ በፉጨት ፡ ይጠራል ።

19 ፤ ይመጡማል ፥ እነርሱም ፡ ኹሉ ፡ በበረሓ ፡ ሸለቆ ፡ በድንጋይም ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ በሾኽ ፡ ቍጥቋጦ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በማሰማሪያውም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይሰፍራሉ ።

20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከወንዙ ፡ ማዶ ፡ በተከራየው ፡ ምላጭ ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የራሱንና ፡ የእግሩን ፡ ጠጕር ፡ ይላጨዋል ፤ ምላጩም ፡ ጢሙን ፡ ደግሞ ፡ ይበላል ።

21 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ሰው ፡ አንዲት ፡ ጊደርን ፡ ኹለት ፡ በጎችንም ፡ ያሳድጋል ፤

22 ፤ ከሚሰጡት ፡ ወተት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ቅቤ ፡ ይበላል ፤ በአገሪቱም ፡ መካከል ፡ የቀረ ፡ ኹሉ ፡ ቅቤና ፡ ማር ፡ ይበላል ።

23 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ሺሕ ፡ ብር ፡ የተገመተ ፡ ሺሕ ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ በነበረበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ለኵርንችትና ፡ ለሾኽ ፡ ይኾናል ።

24 ፤ ኵርንችትና ፡ ሾኽ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ በፍላጻና ፡ በቀስት ፡ ወደዚያ ፡ ይገባሉ ።

25 ፤ በመቈፈሪያም ፡ ወደተቈፈሩ ፡ ኰረብታዎች ፡ ኹሉ ፡ ከኵርንችትና ፡ ሾኽ ፡ ፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ ወደዚያ ፡ አትኼድም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የበሬ ፡ ማሰማሪያና ፡ የበግ ፡ መራገጫ ፡ ይኾናል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ታላቅ ፡ሰሌዳ ፡ ወስደኽ ፦ ምርኮ ፡ ፈጠነ ፥ ብዝበዛ ፡ ቸኰለ ፡ ብለኽ ፡ በሰው ፡ ፊደል ፡ ጻፍበት ።

2 ፤ የታመኑትን ፡ ሰዎች ፡ ካህኑን ፡ ኦርዮንና ፡ የበራክዩን ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስን ፡ ምስክሮች ፡ አድርግልኝ ፡ አለኝ ።

3 ፤ ወደ ፡ ነቢዪቱም ፡ ቀረብኹ ፤ ርሷም ፡ ፀነሰች ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ሕፃኑ ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ መጥራት ፡ ሳያውቅ ፡ የደማስቆን ፡ ሀብትና ፡ የሰማርያን ፡ ምርኮ ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ ይወስዳልና ፥ ስሙን ፦ ምርኮ ፡ ፈጠነ ፥ ብዝበዛ ፡ ቸኰለ ፡ ብለኽ ፡ ጥራው ፡ አለኝ ።

5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ተናገረኝ ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ።

6 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በቀስታ ፡ የሚኼደውን ፡ የሰሊሖምን ፡ ውሃ ፡ ጠልቷልና ፥ ረአሶንንና ፡ የሮሜልዩንም ፡ ልጅ ፡ ወዷልና ፥ ስለዚህ ፥

7 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ብርቱና ፡ ብዙ ፡ የኾነውን ፡ የወንዝ ፡ ውሃ ፥ የአሶርን ፡ ንጉሥና ፡ ክብሩን ፡ ኹሉ ፥ ያመጣባቸዋል ፤ መስኖውንም ፡ ኹሉ ፡ ሞልቶ ፡ ይወጣል ፥ በዳሩም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይፈሳል ፤

8 ፤ እየጐረፈም ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ይገባል ፤ እያጥለቀለቀም ፡ ያልፉል ፥ እስከ ፡ ዐንገትም ፡ ይደርሳል ፤ ዐማኑኤል ፡ ሆይ ፥ የክንፉ ፡ መዘርጋት ፡ የአገርኽን ፡ ስፋት ፡ ትሞላለች ።

9 ፤ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ዕወቁና ፡ ደንግጡ ፤ እናንተም ፡ ምድራችኹ ፡ የራቀ ፡ ኹሉ ፥ አድምጡ ፤ ታጠቁም ፥ ደንግጡ ፤ ታጠቁ ፤ ደንግጡ ።

10 ፤ ተመካከሩ ፥ ምክራችኹም ፡ ይፈታል ፤ ቃሉን ፡ ተናገሩ ፥ ቃሉም ፡ አይጸናም ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነውና ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ተናገረኝ ፥ በዚህም ፡ ሕዝብ ፡ መንገድ ፡ እንዳልኼድ ፡ አስጠንቀቀኝ ፥ እንዲህም ፡ አለኝ ።



www.ethiopianorthodox.org

12 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፦ ዱለት ፡ ነው ፡ በሚሉት ፡ ኹሉ ፦ ዱለት ፡ ነው ፡ አትበሉ ፤ መፈራታቸውንም ፡
አትፍሩ ፥ አትደንግጡ ።

13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቀድሱት ፤ የሚያስፈራችኹና ፡ የሚያስደነግጣችኹም ፡ ርሱ ፡
ይኹን ።

14 ፤ ርሱም ፡ ለመቅደስ ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለኹለቱ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤቶች ፡ ለዕንቅፋት ፡ ድንጋይና ፡ ለማሰናከያ ፡
አለት ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለወጥመድና ፡ ለአሽክላ ፡ ይኾናል ።

15 ፤ ብዙዎችም ፡ በርሱ ፡ ይሰናከላሉ ፥ ይወድቁማል ፥ ይሰበሩማል ፥ ይጠመዱማል ፥ ይያዙማል ።

16 ፤ ምስክሩን ፡ እሰር ፤ በደቀ ፡ መዛሙርቴም ፡ መካከል ፡ ሕጉን ፡ ዐትም ።

17 ፤ ከያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ፊቱን ፡ የመለሰውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጠብቃለኹ ፥ እተማመንበትማለኹ ።

18 ፤ እንሆ ፥ እኔና ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝ ፡ ልጆች ፡ ለእስራኤል ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ከሚኖረው ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምልክትና ፡ ተኣምራት ፡ ነን ።

19 ፤ እነርሱም ፦ የሚጮኹትንና ፡ ድምፃቸውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ የሚናገሩትን ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡
ጠንቋዮችን ፡ ጠይቁ ፡ ባሏችኹ ፡ ጊዜ ፥ ሕዝቡ ፡ ከአምላኩ ፡ መጠየቅ ፡ አይገባውምን ፤ ወይስ ፡ ለሕያዋን ፡ ሲሉ ፡
ሙታንን ፡ ይጠይቃሉን ፤

20 ፤ ወደ ፡ ሕግና ፡ ወደ ፡ ምስክር ፡ ኺዱ! እንዲህም ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ባይናገሩ ፡ ንጋት ፡ አይበራላቸውም ።

21 ፤ እነርሱም ፡ ተጨንቀውና ፡ ተርበው ፡ ያልፋሉ ፤ በተራቡም ፡ ጊዜ ፡ ተቈጥተው ፡ ንጉሣቸውንና ፡ አምላካቸውን ፡
ይረግማሉ ፥ ወደ ፡ ላይም ፡ ይመለከታሉ ፤

22 ፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ ይመለከታሉ ፥ እንሆም ፥ መከራና ፡ ጨለማ ፡ የሚያስጨንቅም ፡ ጭጋግ ፡ አለ ፤ ወደ ፡ ድቅድቅም ፡
ጨለማ ፡ ይሰደዳሉ ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተጨንቃ ፡ ለነበረች ፡ ጨለማ ፡ አይኾንም ። በመዠመሪያው ፡ ዘመን ፡ የዛብሎንንና ፡ የንፍታሌምን ፡
ምድር ፡ አቃለለ ፤ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በባሕር ፡ መንገድ ፡ ያለውን ፡ የአሕዛብን ፡ ገሊላ ፡
ያከብራል ።

2 ፤ በጨለማ ፡ የኼደ ፡ ሕዝብ ፡ ብርሃን ፡ አየ ፤ በሞት ፡ ጥላ ፡ አገርም ፡ ለኖሩ ፡ ብርሃን ፡ ወጣላቸው ።

3 ፤ ሕዝብን ፡ አብዝተኻል ፥ ደስታንም ፡ ጨምረኽላቸዋል ፤ በመከር ፡ ደስ ፡ እንደሚላቸው ፥ ሰዎችም ፡ ምርኮን ፡
ሲካፈሉ ፡ ደስ ፡ እንደሚላቸው ፡ በፊትኽ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

4 ፤ በምድያም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሸክሙን ፡ ቀንበር ፡ የጫንቃውንም ፡ በትር ፡ የአስጨናቂውንም ፡ ዘንግ ፡ ሰብረኻል ።

5 ፤ የሚረግጡ ፡ የሰልፈኞዎች ፡ ጫማ ፡ ኹሉ ፥ በደምም ፡ የተለወሰ ፡ ልብስ ፡ ለቃጠሎ ፡ ይኾናል ፥ እንደ ፡ እሳት ፡
ማቃጠያም ፡ ኾኖ ፡ ይቃጠላል ።

6 ፤ ሕፃን ፡ ተወልዶልናልና ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ተሰጥቶናልና ፤ አለቅነትም ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ስሙም ፡
ድንቅ ፡ መካር ፥ ኀያል ፡ አምላክ ፥ የዘለዓለም ፡ አባት ፥ የሰላም ፡ አለቃ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

7 ፤ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ በፍርድና ፡ በጽድቅ ፡ ያጸናውና ፡ ይደግፈው ፡ ዘንድ ፡ በዳዊት ፡ ዙፋንና ፡
በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ አለቅነቱ ፡ ይበዛል ፥ ለሰላሙም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ። የእግዚአብሔር ፡ ቅንአት ፡ ይህን ፡ ያደርጋል ።

8 ፤ ጌታ ፡ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ቃልን ፡ ሰደደ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ወደቀ ።

9 ፤ 10 ፤ በትዕቢትና ፡ በልብ ፡ ኵራት ፦ ጡቡ ፡ ወድቋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በተወቀረ ፡ ድንጋይ ፡ እንሠራለን ፤ የሾላ ፡
ዛፎች ፡ ተቈርጠዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ዝግባን ፡ እንተካባቸዋለን ፡ የሚሉ ፡ በኤፍሬምና ፡ በሰማርያ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሹሉ ፡ ያውቃሉ ።

11 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ተቋቋሚ ፡ ያስነሣበታል ፥

12 ፤ ጠላቶቹን ፡ ሶርያውያንንም ፡ ከምሥራቅ ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ ከምዕራብ ፡ ያንቀሳቅስበታል ፤ እስራኤልንም ፡ በተከፈተ ፡ አፍ ፡ ይበሉታል ። በዚህም ፡ ሹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

13 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ወደቀሠፋቸው ፡ አልተመለሱም ፥ የሰራዊትንም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አልፈለጉም ።

14 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ራስና ፡ ዥራትን ፥ የሰሌኑን ፡ ቅርንጫፍና ፡ እንግጫውን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ከእስራኤል ፡ ይቈርጣል ።

15 ፤ ሽማግሌውና ፡ ከበርቴው ፡ ርሱ ፡ ራስ ፡ ነው ፤ በሐሰትም ፡ የሚያስተምር ፡ ነቢይ ፡ ርሱ ፡ ዥራት ፡ ነው ።

16 ፤ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመሩ ፡ ያስቷቸዋል ፤ ተመሪዎቹም ፡ ይጠፋሉ ።

17 ፤ ሰው ፡ ሹሉ ፡ ዝንጉና ፡ ክፉ ፡ ሠሪ ፡ ነውና ፥ አፍም ፡ ሹሉ ፡ ስንፍናን ፡ ይናገራልና ፥ ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ በጕልማሳዎቻቸው ፡ ደስ ፡ አይለውም ፥ ለድኻ ፡ አደጎቻቸውና ፡ ለመበለቶቻቸውም ፡ አይራራም ። በዚህም ፡ ሹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

18 ፤ ክፋት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይቃጠላል ፤ ኵርንችቱንና ፡ ሾኹን ፡ ይበላል ፤ ጭፍቅ ፡ የኾነውንም ፡ ዱር ፡ ያቃጥላል ፥ ጢሱም ፡ ተትጕልጕሎ ፡ እንደ ፡ ዐምድ ፡ ይወጣል ።

19 ፤ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ምድር ፡ ተቃጥላለች ፤ ሕዝቡም ፡ እሳት ፡ እንደሚበላው ፡ ዕንጨት ፡ ኾኗል ፤ ሰውም ፡ ለወንድሙ ፡ አይራራም ።

20 ፤ ሰው ፡ በቀኙ ፡ በኩል ፡ ይነቅላል ፡ ይራብማል ፤ በግራም ፡ በኩል ፡ ይበላል ፡ አይጠግብምም ፤ እያንዳንዱም ፡ የክንዱን ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ፤

21 ፤ ምናሴ ፡ ኤፍሬምን ፡ ኤፍሬምም ፡ ምናሴን ፡ ይበላል ፤ እነርሱ ፡ በአንድነት ፡ የይሁዳ ፡ ጠላቶች ፡ ይኾናሉ ። በዚህም ፡ ሹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ 2 ፤ መበለቶችም ፡ ቅሚያቸው ፡ እንዲኾኑ ፥ ድኻ ፡ አደጎችንም ፡ ብዝበዛቸው ፡ እንዲያደርጉ ፥ የድኻውን ፡ ፍርድ ፡ ያጣምሙ ፡ ዘንድ ፥ የችግረኛውንም ፡ ሕዝቤን ፡ ፍርድ ፡ ያጐድሉ ፡ ዘንድ ፡ የግፍን ፡ ትእዛዛት ፡ ለሚያዙ ፥ ክፉንም ፡ ጽሕፈት ፡ ለሚጽፉ ፡ ወዮላቸው!

3 ፤ በተጐበኛችኹበት ፡ ቀን ፥ መከራም ፡ ከሩቅ ፡ በሚመጣበት ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ታደርጉ ፡ ይኾን ፧ ለረድኤትስ ፡ ወደ ፡ ማን ፡ ትሸሻላችኹ ፧ ክብራችኹንስ ፡ ወዴት ፡ ትተዉታላችኹ ፧

4 ፤ ከእስረኛዎች ፡ በታች ፡ ይጐነበሳሉ ፥ ከተገደሉትም ፡ በታች ፡ ይወድቃሉ ። በዚህም ፡ ሹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

5 ፤ ለቍጣዬ ፡ በትር ፡ ለኾነ ፥ የመዓቴም ፡ ጨንገር ፡ በእጁ ፡ ላለ ፡ ለአሶር ፡ ወዮለት!

6 ፤ ርሱንም ፡ በዝንጉ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እልካለኹ ፥ ምርኮውንና ፡ ብዝበዛውንም ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አደባባይም ፡ ጭቃ ፡ የተረገጡ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ በምቈጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አዝዋለኹ ።

7 ፤ ርሱ ፡ እንዲሁ ፡ አያስብም ፥ በልቡም ፡ እንዲህ ፡ አይመስለውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ማጥፋት ፥ ጥቂት ፡ ያይደሉትንም ፡ አሕዛብን ፡ መቍረጥ ፡ በልቡ ፡ አለ ።

8 ፤ እንዲህ ፡ ይላል ፡— መሳፍንቴ ፡ ሹሉ ፡ ነገሥታት ፡ አይደሉምን ፧

9 ፤ ካልኖ ፡ እንደ ፡ ከርከሚሽ ፡ አይደለችምን ፧ ሐማትስ ፡ እንደ ፡ አርፋድ ፡ አይደለችምን ፧ ሰማርያስ ፡ እንደ ፡ ደማስቆ ፡


www.ethiopianorthodox.org

አይደለችምን ፧

10 ፤ የተቀረጹ ፡ ምስሎቻቸው ፡ ከኢየሩሳሌምና ፡ ከሰማርያ ፡ ምስሎች ፡ የበለጡትን ፡ የጣዖቶችን ፡ መንግሥታት ፡ እጄ ፡ እንዳገኘች ፥

11 ፤ በሰማርያና ፡ በጣዖቶቿም ፡ እንዳደረግኹ ፥ እንዲሁስ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በጣዖቶቿ ፡ አላደርግምን ፧

12 ፤ ስለዚህ ፥ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ጌታ ፡ ሥራውን ፡ ኹሉ ፡ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ የኵሩ ፡ ልብ ፡ ፍሬን ፡ የዐይኑንም ፡ ከፍታ ፡ ትምክሕት ፡ ይጐበኛል ።

13 ፤ ርሱ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ፦ አስተዋይ ፡ ነኝና ፡ በእጄ ፡ ኀይልና ፡ በጥበቤ ፡ አደረግኹት ፤ የአሕዛብን ፡ ድንበሮች ፡ አራቅኹ ፥ ሀብታቸውንም ፡ ዘረፍኹ ፥ እንደ ፡ ዠግናም ፡ ኾኜ ፡ በምድር ፡ የተቀመጡትን ፡ አዋረድኹ ፤

14 ፤ እጄም ፡ የአሕዛብን ፡ ኀይል ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ቤት ፡ አገኘች ፤ የተተወም ፡ ዕንቍላል ፡ እንደሚሰበሰብ ፡ እንዲሁ ፡ እኔ ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰብኹ ፤ ክንፉን ፡ የሚያራግብ ፡ አፉንም ፡ የሚከፍት ፡ የሚጮኽም ፡ የለም ።

15 ፤ በእውኑ ፡ መጥረቢያ ፡ በሚቈርጥበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይመካልን ፧ ወይስ ፡ መጋዝ ፡ በሚስበው ፡ ላይ ፡ ይኳደዳልን ፧ ይህስ ፥ በትር ፡ የሚያነሣውን ፡ እንደ ፡ መነቅነቅ ፡ ዘንግም ፡ ዕንጨት ፡ ያይደለውን ፡ እንደ ፡ ማንሣት ፡ ያኽል ፡ ነው ።

16 ፤ ስለዚህም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወፍራሞች ፡ ላይ ፡ ክሳትን ፡ ይልካል ፤ ከክብሩም ፡ በታች ፡ ቃጠሎው ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ መቃጠል ፡ ይነዳል ።

17 ፤ የእስራኤልም ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ቅዱስም ፡ እንደ ፡ ነበልባል ፡ ይኾናል ፤ ሾኹንና ፡ ኵርንችቱን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ያቃጥላል ፡ ይበላውማል ።

18 ፤ ከነፍስም ፡ እስከ ፡ ሥጋ ፡ ድረስ ፡ የዱሩንና ፡ የሚያፈራውን ፡ ዕርሻ ፡ ክብር ፡ ይበላል ፤ ይህም ፡ የታመመ ፡ ሰው ፡ እንደሚሰለስል ፡ ይኾናል ።

19 ፤ የቀሩትም ፡ የዱር ፡ ዛፎች ፡ በቍጥር ፡ ጥቂት ፡ ይኾናሉ ፥ ታናሽ ፡ ብላቴናም ፡ ይጽፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ይችላል ።

20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ የእስራኤል ፡ ቅሬታ ፡ ከያዕቆብም ፡ ቤት ፡ የዳኑት ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በመቷቸው ፡ ላይ ፡ አይደገፉም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በእውነት ፡ ይደገፋሉ ።

21 ፤ የያዕቆብም ፡ ቅሬታ ፡ ወደ ፡ ኀያል ፡ አምላክ ፡ ይምለሳሉ ።

22 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ የሕዝብኽ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ቢኾን ፡ ቅሬታው ፡ ይመለሳል ። ጽድቅ ፡ የተትረፈረፈበትም ፡ ጥፋት ፡ ተወስኗል ።

23 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያለቀ ፡ የተቈረጠ ፡ ነገርን ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ይፈጽማል ።

24 ፤ ስለዚህ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በጽዮን ፡ የምትኖር ፡ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ አሶር ፡ በበትር ፡ ቢመታኽ ፥ ግብጽም ፡ እንዳደረገ ፡ ዘንጉን ፡ ቢያነሣብኽ ፥ አትፍራው ።

25 ፤ ቍጣዬ ፡ እስኪፈጸም ፡ መዓቴም ፡ እስኪያጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቀርቷልና ።

26 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ምድያምን ፡ በሔሬብ ፡ አለት ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ መታው ፡ ጅራፍ ፡ ያነሣበታል ፤ በትሩም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ በግብጽም ፡ እንዳደረገ ፡ ያነሣዋል ።

27 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሸክሙ ፡ ከጫንቃኽ ፡ ቀንበሩም ፡ ከዐንገትኽ ፡ ላይ ፡ ይወርዳል ፤ ቀንበሩም ፡ ከውፍረት ፡ የተነሣ ፡ ይሰበራል ።

28 ፤ ወደ ፡ አንጋይ ፡ መጥቷል ፤ በመጌዶን ፡ በኩል ፡ ዐልፏል ፤ በማክማስ ፡ ውስጥ ፡ ዕቃውን ፡ አኑሯል ፤

29 ፤ በመተላለፊያ ፡ ዐልፏል ፤ በጌባ ፡ ማደሪያው ፡ ነው ፤ ራማ ፡ ደንግጣለች ፤ የሳኦል ፡ ጊብዓ ፡ ኰብላለች ።

30 ፤ አንቺ ፡ የጋሊም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በታላቅ ፡ ድምፅሽ ፡ ጩኺ ፤ ላይሳ ፡ ሆይ ፥ አድምጪ ፤ ዐናቶት ፡ ሆይ ፥ መልሺላት ።



www.ethiopianorthodox.org

31 ፤ መደቤና ፡ ሸሸታለች ፤ በግቤርም ፡ የሚኖሩ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸውን ፡ አሸሸተዋል ።

32 ፤ ዛሬ ፡ በኖብ ፡ ይቆማል ፤ በጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተራራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ያንቀሳቅሳል ።

33 ፤ እንሆ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ በሚያስፈራ ፡ ኀይል ፡ ይቈርጣል ፤ በቁመት ፡
የረዘሙትም ፡ ይቈረጣሉ ፥ ከፍ ፡ ያሉትም ፡ ይዋረዳሉ ።

34 ፤ ጭፍቅ ፡ የኾነውንም ፡ ዱር ፡ በብረት ፡ ይቈርጣል ፥ ሊባኖስም ፡ በኀያሉ ፡ እጅ ፡ ይወድቃል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፤ ከእሴይ ፡ ግንድ ፡ በትር ፡ ይወጣል ፥ ከሥሩም ፡ ቍጥቋጥ ፡ ያፈራል ።

2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፥ የጥበብና ፡ የማስተዋል ፡ መንፈስ ፥ የምክርና ፡ የኀይል ፡ መንፈስ ፥ የዕውቀትና ፡
እግዚአብሔርን ፡ የመፍራት ፡ መንፈስ ፡ ያርፍበታል ።

3 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ደስታውን ፡ ያያል ። ዐይኑም ፡ እንደምታይ ፡ አይፈርድም ፥ ዦሮውም ፡ እንደምትሰማ ፡
አይበይንም ፤

4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለድኻዎች ፡ በጽድቅ ፡ ይፈርዳል ፥ ለምድርም ፡ የዋሆች ፡ በቅንነት ፡ ይበይናል ፤ በአፉም ፡ በትር ፡
ምድርን ፡ ይመታል ፥ በከንፈሩም ፡ እስትንፋስ ፡ ክፉዎችን ፡ ይገድላል ።

5 ፤ የወገቡ ፡ መታጠቂያ ፡ ጽድቅ ፥ የጐኑም ፡ መቀነት ፡ ታማኝነት ፡ ይኾናል ።

6 ፤ ተኵላ ፡ ከበግ ፡ ጠቦት ፡ ጋራ ፡ ይቀመጣል ፥ ነብርም ፡ ከፍየል ፡ ጠቦት ፡ ጋራ ፡ ይተኛል ፤ ጥጃና ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡
ፍሪዳም ፡ በአንድነት ፡ ያርፋሉ ፤ ታናሽም ፡ ልጅ ፡ ይመራቸዋል ።

7 ፤ ላምና ፡ ድብ ፡ ዐብረው ፡ ይሰማራሉ ፥ ግልገሎቻቸውም ፡ በአንድነት ፡ ያርፋሉ ፤ አንበሳም ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ገለባ ፡
ይበላል ።

8 ፤ የሚጠባውም ፡ ሕፃን ፡ በእባብ ፡ ጕድጓድ ፡ ላይ ፡ ይጫወታል ፥ ጡት ፡ የጣለውም ፡ ሕፃን ፡ በእፍኝት ፡ ቤት ፡ ላይ ፡
እጁን ፡ ይጭናል ።

9 ፤ በተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አይጐዱም ፡ አያጠፉምም ፤ ውሃ ፡ ባሕርን ፡ እንደሚከድን ፡ ምድር ፡
እግዚአብሔርን ፡ በማወቅ ፡ ትሞላለችና ።

10 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ለአሕዛብ ፡ ምልክት ፡ ሊኾን ፡ የቆመውን ፡ የእሴይን ፡ ሥር ፡ አሕዛብ ፡
ይፈልጉታል ፤ ማረፊያውም ፡ የተከበረ ፡ ይኾናል ።

11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ የቀረውን ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ከአሶርና ፡ ከግብጽ ፥ ከጳትሮስና ፡
ከኢትዮጵያ ፥ ከዔላምና ፡ ከሰናዖር ፡ ከሐማትም ፥ ከባሕርም ፡ ደሴቶች ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እጁን ፡
ይገልጣል ።

12 ፤ ለአሕዛብም ፡ ምልክትን ፡ ያቆማል ፥ ከእስራኤልም ፡ የተጣሉትን ፡ ይሰበስባል ፥ ከይሁዳም ፡ የተበተኑትን ፡ ከአራቱ ፡
የምድር ፡ ማእዘኖች ፡ ያከማቻል ።

13 ፤ የኤፍሬምም ፡ ምቀኝነት ፡ ይርቃል ፥ ይሁዳንም ፡ የሚያስጨንቁ ፡ ይጠፋሉ ፤ ኤፍሬምም ፡ በይሁዳ ፡
አይቀናም ፥ ይሁዳም ፡ ኤፍሬምን ፡ አያስጨንቅም ።

14 ፤ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ እየበረሩ ፡ ይወርዳሉ ፥ የምሥራቅንም ፡ ልጆች ፡
በአንድነት ፡ ይበዘብዛሉ ፤ በኤዶምያስና ፡ በሞዐብም ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ይዘረጋሉ ፥ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ለእነርሱ ፡
ይታዘዛሉ ።

15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የግብጽን ፡ ባሕር ፡ ያጠፋል ፤ በትኵሱም ፡ ነፋስ ፡ እጁን ፡ በወንዙ ፡ ላይ ፡ ያነሣል ፥ ሰባት ፡
ፈሳሾችንም ፡ አድርጎ ፡ ይመታዋል ፥ ሰዎችም ፡ በጫማቸው ፡ እንዲሻገሩ ፡ ያደርጋቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

16 ፤ ከግብጽም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ ለቀረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ቅሬታ ፡ ከአሶር ፡ ጐዳና ፡ ይኾናል ።

________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 12 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ አቤቱ ፥ ተቈጥተኸኛልና ፥ ቍጣኽንም ፡ ከእኔ ፡ መልሰኻልና ፥ አጽናንተኸኛልምና ፡
አመሰግንኻለኹ ።

2 ፤ እንሆ ፥ አምላክ ፡ መድኀኒቴ ፡ ነው ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀይሌና ፡ዝማሬዬ ፡ ነውና ፥ መድኀኒቴም ፡
ኾኗልና ፥ በርሱ ፡ ታምኜ ፡ አልፈራም ፡ ትላለኽ ።

3 ፤ ውሃውንም ፡ ከመድኀኒት ፡ ምንጮች ፡ በደስታ ፡ ትቀዳላችኹ ።

4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ትላላችኹ ። እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፥ ስሙንም ፡ ጥሩ ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡
ሥራውን ፡ አስታውቁ ፤ ስሙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተናገሩ ።

5 ፤ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀኙ ፤ ይህንም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አስታውቁ ።

6 ፤ አንቺ ፡ በጽዮን ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ በመካከልሽ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፡
እልልም ፡ በዪ ።

________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 13 ።

1 ፤ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ያየው ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ።

2 ፤ ምድረ ፡ በዳ ፡ በኾነ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ምልክትን ፡ አቁሙ ፥ ድምፅንም ፡ ከፍ ፡ አድርጉባቸው ፤ በአለቃዎችም ፡ ደጆች ፡
እንዲገቡ ፡ በእጅ ፡ ጥቀሱ ።

3 ፤ ቍጣዬን ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ ቅዱሳኔን ፡ አዝዣለኹ ፥ እኔ ፡ ኀያላኔንና ፡ በታላቅነቴ ፡ ደስ ፡ የሚላቸውን ፡
ጠርቻለኹ ።

4 ፤ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ የኾነ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ አለ ። የከተማቹት ፡ የአሕዛብ ፡
መንግሥታት ፡ የውካታ ፡ ጫጫታ ፡ አለ ። የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰራዊትን ፡ ለሰልፍ ፡ አሰልፏል ።

5 ፤ እግዚአብሔርና ፡ የቍጣው ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ያጠፉት ፡ ዘንድ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ከሰማይ ፡ ዳርቻ ፡
ይመጣሉ ።

6 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቀርቧልና ፥ አልቅሱ ፤ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚመጣ ፡ ጥፋት ፡
ይመጣል ።

7 ፤ ስለዚህ ፥ እጅ ፡ ኹሉ ፡ ትዝላለች ፥ የሰውም ፡ ኹሉ ፡ ልብ ፡ ይቀልጣል ።

8 ፤ ይደነግጣሉ ፤ ምጥና ፡ ሕማም ፡ ይይዛቸዋል ፥ እንደምትወልድ ፡ ሴትም ፡ ያምጣሉ ፤ አንዱም ፡ በሌላው ፡
ይደነቃል ፥ ፊታቸውም ፡ የነበልባል ፡ ፊት ፡ ነው ።

9 ፤ እንሆ ፥ ምድሪቱን ፡ ባድማ ፡ ሊያደርግ ፥ ኀጢአተኛዎቿንም ፡ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ ሊያጠፋ ፡ ጨካኝ ፡ ኾኖ ፡ በመዓትና ፡
በጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ተሞልቶ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ይመጣል ።

10 ፤ የሰማይም ፡ ከዋክብትና ፡ ሰራዊቱ ፡ ብርሃናቸውን ፡ አይሰጡም ፥ ፀሓይም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡
ትጨልማለች ፥ ጨረቃም ፡ በብርሃኑ ፡ አያበራም ።

11 ፤ ዓለሙን ፡ ስለ ፡ ክፋታቸው ፡ ክፉዎቹንም ፡ ስለ ፡ በደላቸው ፡ እቀጣለኹ ፤ የትዕቢተኛዎችንም ፡ ኵራት ፡ አዋርዳለኹ ።

12 ፤ የቀሩትም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ይልቅ ፡ የከበሩ ፡ ይኾናሉ ፥ ሰውም ፡ ከኦፊር ፡ ወርቅ ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ይኾናል ።

13 ፤ ስለዚህ ፥ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ በጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ቀንም ፡ ሰማያትን ፡ አነቃንቃለኹ ፥ ምድርም ፡
ከስፍራዋ ፡ ትናወጣለች ።



www.ethiopianorthodox.org

14 ፤ እንደ ፡ ተባረረም ፡ ሚዳቋ ፥ ማንም ፡ እንደማይሰበስበው ፡ እንደ ፡ በግ ፡ መንጋ ፥ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይመለሳል ፥ ኹሉም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሸሻል ።

15 ፤ የተገኘ ፡ ኹሉ ፡ የተወጋ ፡ ይኾናል ፥ የተያዘም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃል ።

16 ፤ ሕፃናታቸውም ፡ በፊታቸው ፡ ይጨፈጨፋሉ ፥ ቤቶቻቸውም ፡ ይበዘበዛሉ ፥ ሚስቶቻቸውም ፡ ይነወራሉ ።

17 ፤ እንሆ ፥ ብር ፡ የማይሹትን ፥ ወርቅም ፡ የማያምራቸውን ፡ ሜዶናውያንን ፡ በላያቸው ፡ አስነሣለኊ ።

18 ፤ ፍላጻዎቻቸውም ፡ ጕበዞችን ፡ ይጨፈጭፋሉ ፥ የማሕፀንንም ፡ ፍሬ ፡ አይምሩም ፥ ዐይኖቻቸውም ፡ ለሕፃናት ፡ አይራሩም ።

19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰዶምንና ፡ ገሞራን ፡ ባፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፥ የመንግሥታት ፡ክብር ፡ የከለዳውያንም ፡ ትዕቢት ፡ ጌጥ ፡ ባቢሎን ፡ እንዲሁ ፡ ትኾናለች ።

20 ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚቀመጥባት ፡ አይገኝም ፥ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡
አይኖርባትም ፤ ዐረባውያንም ፡ ድንኳንን ፡ በዚያ ፡ አይተክሉም ፥ እረኞዎችም ፡ መንጋዎቻቸውን ፡ በዚያ ፡ አያሳርፉም ።

21 ፤ በዚያም ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ያርፋሉ ፥ ጕጕቶችም ፡ በቤቶቻቸው ፡ ይሞላሉ ፤ ሰጎኖችም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ፥ በዚያም ፡ አጋንንት ፡ ይዘፍናሉ ።

22 ፤ ተኵላዎችም ፡ በግንቦቻቸው ፥ ቀበሮዎችም ፡ በሚያማምሩ ፡ አዳራሾቻቸው ፡ ይጮኻሉ ፤ ጊዜዋም ፡ ለመምጣት ፡ ቀርቧል ፥ ቀኗም ፡ አይዘገይም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ምዕራፍ ፡ 14 ።

1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያዕቆብን ፡ ይምረዋል ፥ እስራኤልንም ፡ ደግሞ ፡ ይመርጠዋል ፥ በአገራቸውም ፡ ያኖራቸዋል ፤ መጻተኛም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይተባበራል ፥ ከያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ይጣበቃል ።

2 ፤ አሕዛብም ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ያመጧቸዋል ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ሎሌዎችና ፡ እንደ ፡ ገረዶች ፡ አድርገው ፡ ይገዟቸዋል ፤ የማረኳቸውን ፡ ይማርካሉ ፥ አስጨናቂዎችንም ፡ ይገዛሉ ።

3 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሐዘንኽና ፡ ከመከራኽ ፡ ከተገዛኽለትም ፡ ከጽኑ ፡ ባርነት ፡ ያሳርፍኻል ።

4 ፤ ይህንም ፡ ምሳሌ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ታነሣለኽ ፡ እንዲህም ፡ ትላለኽ ፦ አስጨናቂ ፡ እንዴት ፡ ዐረፈ! አስገባሪም ፡ እንዴት ፡ ጸጥ ፡ አለ!

5 ፤ 6 ፤ አሕዛብንም ፡ በመዓትና ፡ በማያቋርጥ ፡ መምታት ፡ የመታውን ፥ አሕዛብንም ፡ ባልተከለከለ ፡ መከራ ፡ በቍጣው ፡ የገዛውን ፡ የኃጥኣንን ፡ በትር ፡ የአለቃዎችንም ፡ ዘንግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰብሯል ።

7 ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ ዐርፋ ፡ በጸጥታ ፡ ተቀምጣለች ፡ እልልም ፡ ብላለች ።

8 ፤ ጥድና ፡ የሊባኖስ ፡ ዝግባ ፦ አንተ ፡ ከተዋረድኽ ፡ ዠምሮ ፡ ማንም ፡ ይቈርጠን ፡ ዘንድ ፡ አልወጣብንም ፡ ብለው ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

9 ፤ ሲኦል ፡ በመምጣትኽ ፡ ልትገናኝኽ ፡ በታች ፡ ታወከች ፤ የሞቱትንም ፥ የምድርን ፡ ታላላቆች ፡ ኹሉ ፥ ለአንተ ፡ አንቀሳቀሰች ፥ የአሕዛብንም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ከዙፋኖቻቸው ፡ አስነሣች ።

10 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ደክመኻልን ፡ ፧ እኛንስ ፡ መስለኻልን ፡ ፧ ጌጥኽና ፡ የበገናኽ ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወረደ ፤

11 ፤ በበታችኽም ፡ ብል ፡ ተነጥፏል ፥ ትልም ፡ መደረቢያኽ ፡ ኾኗል ፡ ብለው ፡ ይመልሱልኻል ።

12 ፤ አንተ ፡ የንጋት ፡ ልጅ ፡ አጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ ከሰማይ ፡ ወደቅኽ! አሕዛብንም ፡ ያዋረድኽ ፡ አንተ ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ድረስ ፡ ተቈረጥኽ!



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ አንተን ፡ በልብኽ ፦ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐርጋለኹ ፣ ዙፋኔንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከዋክብት ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
አደርጋለኹ ፣ በሰሜንም ፡ ዳርቻ ፡ በመሰብሰቢያ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ እቀመጣለኹ ፤

14 ፤ ከዳመናዎች ፡ ከፍታ ፡ በላይ ፡ ዐርጋለኹ ፣ በልዑልም ፡ እመሰላለኹ ፡ አልኽ ።

15 ፤ ነገር ፡ ግን ፣ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወደጕድጓዱም ፡ ጥልቅ ፡ ትወርዳለኽ ።

16 ፤ የሚያዩኽ ፡ ይመለከቱኻልና ፦ በእውኑ ፡ ምድርን ፡ ያንቀጠቀጠ ፣ መንግሥታትንም ፡ ያናወጠ ፣

17 ፤ ዓለሙን ፡ ኹሉ ፡ ባድማ ፡ ያደረገ ፣ ከተማዎችንም ፡ ያፈረሰ ፣ ምርኮኛዎቹንም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ያልሰደደ ፡ ሰው ፡
ይህ ፡ ነውን ፧ ብለው ፡ ያስተውሉኻል ።

18 ፤ የአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በየቤታቸው ፡ በክብር ፡ አንቀላፍተዋል ።

19 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተጠላ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ከመቃብርኽ ፡ ተጥለኻል ፤ በሰይፍም ፡ የተወጉት ፣ ተገድለውም ፡
ወደጕድጓዱ ፡ ድንጋዮች ፡ የወረዱት ፡ ከድነውኻል ፤ እንደ ፡ ተረገጠም ፡ ሬሳ ፡ ኾነኻል ።

20 ፤ ምድርኽን ፡ አጥፍተኻልና ፣ ሕዝብኽንም ፡ ገድለኻልና ፣ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በመቃብር ፡ በአንድነት ፡
አትኾንም ፤ የክፉዎች ፡ ዘር ፡ ለዘለዓለም ፡ የተጠራ ፡ አይኾንም ።

21 ፤ እንዳይነሡም ፣ ምድርንም ፡ እንዳይወርሱ ፣ የዓለሙንም ፡ ፊት ፡ በከተማዎች ፡ እንዳይሞሉ ፡ ስላባቶቻቸው ፡ በደል ፡
ለልጆቹ ፡ ሞትን ፡ አዘጋጁላቸው ።

22 ፤ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እነሣለኹ ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ከባቢሎን ፡ ስምንና ፡ ቅሬታን ፣ ዘርንና ፡
ትውልድንም ፡ እቈርጣለኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

23 ፤ የዣርት ፡ መኖሪያ ፡ የውሃም ፡ መቋሚያ ፡ አደርጋታለኹ ፤ በጥፋትም ፡ መጥረጊያ ፡ እጠርጋታለኹ ፡ ይላል ፡
የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

24 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ምሏል ። እንደ ፡ ተናገርኹ ፡ በርግጥ ፡ ይኾናል ፣ እንደ ፡
ዐሰብኹም ፡ እንዲሁ ፡ ይቆማል ።

25 ፤ አሶርን ፡ በምድሬ ፡ ላይ ፡ እሰብረዋለኹ ፣ በተራራዬም ፡ ላይ ፡ እረግጠዋለኹ ፤ ቀንበሩም ፡ ከነርሱ ፡ ላይ ፡
ይነሣል ፣ ሸክሙም ፡ ከጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ ይወገዳል ።

26 ፤ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሰበው ፡ ዐሳብ ፡ ይህ ፡ ነው ፣ በአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተዘረጋች ፡ እጅ ፡
ይህች ፡ ናት ።

27 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ዐስቧል ፤ የሚያስጥለውስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እጁም ፡
ተዘርግታለች ፤ የሚመልሳትስ ፡ ማን ፡ ነው ፧

28 ፤ ንጉሡ ፡ አካዝ ፡ በሞተበት ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ ሸክም ፡ ኾነ ።

29 ፤ ፍልስጥኤም ፡ ሆይ ፣ ከእባቡ ፡ ሥር ፡ እፍኝት ፡ ይወጣልና ፣ ፍሬውም ፡ የሚበርና ፡ እሳት ፡ የሚመስል ፡ እባብ ፡
ይኾናልና ፣ የመታሽ ፡ በትር ፡ ስለ ፡ ተሰበረ ፡ ኹላችኹም ፡ ደስ ፡ አይበላችኹ ።

30 ፤ የድኻዎችም ፡ የበኵር ፡ ልጆች ፡ ይሰማራሉ ፣ ችግረኛዎችም ፡ ተዘልለው ፡ ይተኛሉ ፤ ሥርኽንም ፡ በራብ ፡
እገድላለኹ ፣ ቅሬታኽም ፡ ይገደላል ።

31 ፤ አንተ ፡ በር ፡ ሆይ ፣ ወዮ ፡ በል ፡ አንቺም ፡ ከተማ ፡ ሆይ ፣ ጩኺ ፤ ፍልስጥኤም ፡ ሆይ ፣ ኹላችኹም ፡
ቀልጣችኋል ፤ ጢስ ፡ ከሰሜን ፡ ይመጣል ፡ ከጭፍራውም ፡ ተለይቶ ፡ የሚቀር ፡ የለም ።

32 ፤ ለሕዝቡም ፡ መልእክተኛዎች ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ መመለስ ፡ ይገባል ፧ እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ እንደ ፡
መሠረተ ፣ የሕዝቡም ፡ ችግረኛዎች ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚጠጉ ፡ ነው ።

__________________ትንቢት ፡ ኢሳይያስ ፣ ምዕራፍ ፡ 15 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 15 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ ስለ ፡ ሞዐብ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። የሞዐብ ፡ ዔር ፡ በሌሊት ፡ ፈርሶ ፡ ጠፋ ፤ ቂር ፡ የሚባልም ፡ የሞዐብ ፡ ምሽግ ፡ በሌሊት ፡ ፈርሶ ፡ ጠፋ ።

2 ፤ ወደ ፡ ባይት ፡ ወደ ፡ ዲቦንም ፡ ወደኰረብታ ፡ መስገጃዎችም ፡ ለልቅሶ ፡ ወጥተዋል ፤ ሞዐብ ፡ በናባው ፡ በሜድባ ፡ ላይ ፡ ታለቅሳለች ፤ ራሳቸው ፡ ኹሉ ፡ ተላጭቷል ፥ ጢማቸውም ፡ ኹሉ ፡ ተላጭቷል ።

3 ፤ በየመንገዳቸውም ፡ በማቅ ፡ ታጥቀዋል ፤ በየሰገነቶቻቸውና ፡ በያደባባዮቻቸው ፡ እንባ ፡ እጅግ ፡ እያፈሰሱ ፡ ኹሉም ፡ አልቅሰዋል ።

4 ፤ ሐሴቦንና ፡ ኤልያሊ ፡ ጮኹ ፤ ድምፃቸው ፡ እስከ ፡ ያሀጽ ፡ ድረስ ፡ ይሰማል ፤ ስለዚህ ፥ የሞዐብ ፡ ሰልፈኞች ፡ ጮኹ ፤ ነፍሷ ፡ በውስጧ ፡ ተንቀጠቀጠች ።

5 ፤ ልቤ ፡ ስለ ፡ ሞዐብ ፡ ጮኸ ፤ ከርሷም ፡ የሚሸሹ ፡ ወደ ፡ ዞዓር ፡ ወደ ፡ ዔግላት[258] ፡ ሺሊሺያ[259] ፡ ኰበለሉ ፤ በሉሒት ፡ ዐቀበት ፡ ላይ ፡ እያለቀሱ ፡ ይወጣሉ ፥ በሖሮናይምም ፡ መንገድ ፡ የዋይታ ፡ ጩኸት ፡ ያነሣሉ ።

6 ፤ የኔምሬም ፡ ውሃዎች ፡ ይደርቃሉ ፤ ሣሩም ፡ ደርቋል ፥ ለጋውም ፡ ጠውልጓል ፥ ልምላሜውም ፡ ኹሉ ፡ የለም ።

7 ፤ ስለዚህ ፥ የሰበሰቡትን ፡ ሀብትና ፡ መዝገባቸውን ፡ ወደአሖያ ፡ ዛፍ ፡ ወንዝ ፡ ማዶ ፡ ይወስዱታል ።

8 ፤ ጩኸት ፡ የሞዐብን ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ ዞረ ፤ ልቅሶዋም ፡ ወደ ፡ ኤግላይምና ፡ ወደ ፡ ብኤርኢሊም ፡ ደረሰ ።

9 ፤ የዲሞንም ፡ ውሃ ፡ ደም ፡ ተሞልታለች ፤ በዲሞንም ፡ ላይ ፡ ሥቃይን ፡ እጨምራለኹ ፥ ከሞዐባውያንም ፡ በሚያመልጡ ፥ ከምድርም ፡ በሚቀሩ ፡ ላይ ፡ አንበሳን ፡ አመጣለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ምዕራፍ ፡ 16 ።

1 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ለሠለጠነው ፡ አለቃ ፡ የበግ ፡ ጠቦቶችን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ካለችው ፡ ከሴላ ፡ ወደጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተራራ ፡ ስደዱ ።

2 ፤ እንደሚበር ፡ ወፍ ፡ እንደ ፡ ተበተኑም ፡ ጫጩቶች ፡ እንዲሁ ፡ የሞዐብ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በአርኖን ፡ መሻገሪያዎች ፡ ይኾናሉ ።

3 ፤ ምክርን ፡ ምከሪ ፥ ፍርድን ፡ አድርጊ ፥ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ጥላሽን ፡ እንደ ፡ ሌሊት ፡ አድርጊ ፤ የተሰደዱትን ፡ ሸሽጊ ፥ የሸሹትን ፡ አትግለጪ ።

4 ፤ ከሞዐብ ፡ የተሰደዱት ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጡ ፤ ከሚያጠፋቸው ፡ ፊት ፡ መጋረጃ ፡ ኹኛቸው ። የሚያስጨንቁ ፡ አልቀዋል ፥ ጥፋትም ፡ ቀርቷል ፤ ይጨቀኑ ፡ የነበሩ ፡ ከምድር ፡ ጠፍተዋል ።

5 ፤ ዙፋንም ፡ በምሕረት ፡ ይቀናል ፥ በዚያም ፡ ላይ ፡ በዳዊት ፡ ድንኳን ፡ ፍርድን ፡ የሚሻ ፡ ጽድቅንም ፡ የሚያፈጥን ፡ ፈራጅ ፡ በእውነት ፡ ይቀመጣል ፡

6 ፤ ስለሞዐብ ፡ ትዕቢት ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ መታበዩ ፥ ስለ ፡ ኩራቱና ፡ ስለ ፡ ትዕቢቱ ፡ ስለ ፡ ቍጣውም ፡ ሰምተናል ፤ ትምክሕቱ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

7 ፤ ስለዚህ ፥ ሞዐብ ፡ ስለ ፡ ሞዐብ ፡ ዋይ ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ዋይ ፡ ይላል ፤ ስለቂርሐራሴት ፡ መሠራት ፡ በጥልቅ ፡ ሐዘን ፡ ታለቅሳላችኹ ።

8 ፤ የሐሴቦን ፡ ዕርሻዎችና ፡ የሴባማ ፡ ወይን ፡ ግንዶች ፡ አዝነዋል ። የአሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ የሰባበሯቸው ፡ ቅርንጫፎች ፡ እስከ ፡ ኢያዜር ፡ ደርሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጥተው ፡ ነበር ፤ ቍጥቋጦቹም ፡ ተዘርግተው ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ ነበር ።

9 ፤ ስለዚህ ፥ በኢያዜር ፡ ልቅሶ ፡ ስለሴባማ ፡ ወይን ፡ ግንድ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ሐሴቦንና ፡ ኤልያሊ ፡ ሆይ ፥ በዛፍሽ ፡ ፍሬና ፡ በወይንሽ ፡ መከር ፡ የጦር ፡ ጩኸት ፡ ወድቋልና ፥ በእንባዬ ፡ አረካሻለኹ ።

258 ዕብ. ፥ ዔግላ ፡ (ዕጕል • ግልገል ፥ እንቦሳ ፥ ጥጃ) ።

259 ዕብ. ፥ ሸሊሺ ፡ (ሣልስት • ሦስተኛት) ።



www.ethiopianorthodox.org

10 ፤ ደስታና ፡ ሐሤትም ፡ ከፍሬያማው ፡ ዕርሻ ፡ ተወስዷል ፥ በወይኑም ፡ ቦታዎች ፡ ዝማሬና ፡ እልልታ ፡ የለም ፤ በመጥመቂያም ፡ ወይን ፡ የሚረግጥ ፡ የለም ፤ የረጋጮቹን ፡ እልልታ ፡ አጥፍቻለኹ ።

11 ፤ ስለዚህ ፥ ልቤ ፡ ስለ ፡ ሞዐብ ፥ አንዠቴም ፡ ስለ ፡ ቂርሔሬስ ፡ እንደ ፡ መሰንቆ ፡ ትጮኻለች ።

12 ፤ ሞዐብም ፡ መጥቶ ፡ በኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ ላይ ፡ በደከመና ፡ ለጸሎት ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አያሸንፍም ፡

13 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ በድሮ ፡ ዘመን ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ።

14 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፦ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ዓመት ፡ የሞዐብ ፡ ክብርና ፡ የሕዝቡ ፡ ዅሉ ፡ ብዛት ፡ ይዋረዳል ፥ ቅሬታውም ፡ እጅግ ፡ ያነሰና ፡ የተጠቃ ፡ ይኾናል ፡ ይላል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ምዕራፍ ፡ 17 ።

1 ፤ ስለ ፡ ደማስቆ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፦ እንሆ ፥ ደማስቆ ፡ ከተማ ፡ ከመኾን ፡ ተቋርጣለች ፤ ባድማና ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ ትኾናለች ።

2 ፤ ከተማዎቿ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተፈቱ ፡ ይኾናሉ ፤ ለመንጋ ፡ ማሰማሪያ ፡ ይኾናሉ ፤ መንጋዎች ፡ በዚያ ፡ ያርፋሉ ፡ የሚያስፈራቸውም ፡ የለም ።

3 ፤ ምሽግም ፡ ከኤፍሬም ፥ መንግሥትም ፡ ከደማስቆ ፡ ተወገደች ፤ የሶርያም ፡ ቅሬታ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ክብር ፡ ይኾናል ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ የያዕቆብ ፡ ክብር ፡ ይደከማል ፡ የሥጋውም ፡ ውፍረት ፡ ይከሳል ።

5 ፤ ዐጫጅ ፡ የቆመውን ፡ እኽል ፡ በእጁ ፡ ሰብስቦ ፡ ዛላውን ፡ እንደሚያጭድ ፡ ይኾናል ፤ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ቃርሚያ ፡ እንደሚለቅም ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

6 ፤ ወይራ ፡ በተመታ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ፍሬ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እንደሚቀር ፥ አራት ፡ ወይም ፡ ዐምስት ፡ በዛፊቱ ፡ ጫፍ ፡ እንደሚገኝ ፥ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቃርሚያ ፡ ይቀራል ፡ ይላል ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ።

7 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ ይመለከታል ፥ ዐይኖቹም ፡ ወደእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ያያሉ ።

8 ፤ እጁም ፡ የሠራቸውን ፡ መሠዊያ ፡ አይመለከትም ፤ ጣቶቹም ፡ ወዳበጇቸው ፥ ወደማምለኪያ ፡ ዐጸዶች ፡ ወይም ፡ ወደፀሓይ ፡ ምስሎች ፥ አያይም ።

9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የአሞራውያንና ፡ የኤውያውያን ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ ተፈቱ ፥ እንዲሁ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ይፈታሉ ፥ ባድማም ፡ ይኾናሉ ።

10 ፤ የደኅንነትኽን ፡ አምላክ ፡ ረስተኻል ፥ የረድኤትኽንም ፡ ጌታ ፡ አላሰብኽም ፤ ስለዚህ ፥ ያማረውን ፡ ተክል ፡ ተክለኻል ፥ እንግዳንም ፡ ዘር ፡ ዘርተኻል ።

11 ፤ በተከልኽበት ፡ ቀን ፡ ታበቅለዋለኽ ፥ በነጋውም ፡ ዘርኽን ፡ እንዲያብብ ፡ ታደርገዋለኽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሐዘንና ፡ በትካዜ ፡ ቀን ፡ መከሩ ፡ ይሸሻል ።

12 ፤ እንደ ፡ ባሕር ፡ ሞገድ ፡ ድምፅ ፡ ለሚተምሙ ፡ ለወገኖች ፡ ብዛት ፥ እንደ ፡ ኀይለኛም ፡ ውሃ ፡ ጩኸት ፡ ለሚጮኹ ፡ አሕዛብ ፡ ወዮላቸው!

13 ፤ አሕዛብ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ጩኸት ፡ ይጮኻሉ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ይገሥጻቸዋል ፥ እነርሱም ፡ እየሸሹ ፡ ይርቃሉ ፥ በተራራም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ እብቅ ፡ በነፋስ ፡ ፊት ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚያዞረው ፡ ትቢያ ፡ ይበተናሉ ።

14 ፤ በመሸ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ድንጋጤ ፡ አለ ፤ ከማለዳም ፡ በፊት ፡ አይገኙም ። የዘረፉን ፡ ሰዎች ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፥ የበዘበዙን ፡ ዕጣ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ምዕራፍ ፡ 18 ።


www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ በኢትዮጵያ ፡ ወንዞች ፡ ማዶ ፡ ላለች ፥ ክንፍ ፡ ያላቸው ፡ መርከቦች ፡ ላሉባት ፥

2 ፤ መልእክተኛዎችን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የደንገል ፡ መርከቦችንም ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ለምትልክ ፡ ምድር ፡ ወዮላት! እናንተ ፡
ፈጣኖች ፡ መልእክተኛዎች ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ረዥምና ፡ ወደ ፡ ለስላሳ ፡ ሕዝብ ፥ ከመዠመሪያው ፡ አስደንጋጭ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡
ወገን ፥ ወደሚሰፍርና ፡ ወደሚረግጥ ፥ ወንዞችም ፡ ምድራቸውን ፡ ወደሚከፍሉት ፡ ሕዝብ ፡ ኺዱ ።

3 ፤ በዓለም ፡ የምትኖሩ ፡ ኹሉና ፡ በምድር ፡ የምትቀመጡ ፡ ሆይ ፥ ምልክት ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡
እዩ ፤ መለከትም ፡ በተነፋ ፡ ጊዜ ፡ ስሙ ።

4 ፤ እግዚአብሔር ፦ በፀሓይ ፡ ጮራ ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ትኵሳት ፥ በዐጨዳም ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ጠል ፡ ደመና ፡ ኾኜ ፡
በማደሪያዬ ፡ በጸጥታ ፡ ተቀምጬ ፡ እመለከታለኹ ፡ ብሎኛልና ።

5 ፤ ርሱ ፡ ከመከር ፡ በፊት ፡ አበባ ፡ በረገፈ ፡ ጊዜ ፡ የወይንም ፡ ፍሬ ፡ ጨርቋ ፡ ሲይዝ ፡ የወይኑን ፡ ዘንግ ፡ በማጭድ ፡
ይቈርጣል ፥ ጫሮቹንም ፡ ይመለምላል ፤ ያስወግድማል ።

6 ፤ በተራራ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ነጣቂዎች ፡ ወፎች ፥ ለምድርም ፡ አውሬዎች ፡ በአንድነት ፡ ይቀራሉ ፤ ነጣቂዎችም ፡ ወፎች ፡
ይባጁባቸዋል ፥ የምድርም ፡ አውሬዎች ፡ ኹሉ ፡ ይከርሙባቸዋል ።

7 ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፥ ከረዥምና ፡ ከለስላሳ ፡ ሕዝብ ፥ ከመዠመሪያው ፡ አስደንጋጭ ፡
ከኾነ ፡ ወገን ፥ ከሚሰፍርና ፡ ከሚረግጥ ፥ ወንዞችም ፡ ምድራቸውን ፡ ከሚከፍሉት ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡
የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ወደሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ ወደጽዮን ፡ ተራራ ፡ ይቀርባል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ምዕራፍ ፡ 19 ።

1 ፤ ስለ ፡ ግብጽ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በፈጣን ፡ ደመና ፡ እይበረረ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
ይመጣል ፤ የግብጽም ፡ ጣዖታት ፡ በፊቱ ፡ ይርዳሉ ፥ የግብጽም ፡ ልብ ፡ በውስጧ ፡ ይቀልጣል ።

2 ፤ ግብጻውያንን ፡ በግብጻውያን ፡ ላይ ፡ አስነሣለኹ ፤ ወንድምም ፡ ወንድሙን ፥ ሰውም ፡ ባልንጀራውን ፥ ከተማም ፡
ከተማን ፥ መንግሥትም ፡ መንግሥትን ፡ ይወጋል ።

3 ፤ የግብጽም ፡ መንፈስ ፡ በውስጧ ፡ ባዶ ፡ ይኾናል ፥ ምክራቸውንም ፡ አጠፋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡
በድግምት ፡ የሚጠነቍሉትንም ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎቻቸውንም ፡ ጠንቋዮቻቸውንም ፡ ይጠይቃሉ ።

4 ፤ ግብጻውያንንም ፡ በጨካኝ ፡ ጌታ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፤ ጨካኝ ፡ ንጉሥም ፡ ይገዛቸዋል ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

5 ፤ ውሃዎችም ፡ ከባሕር ፡ ይደርቃሉ ፥ ወንዙም ፡ ያንሳል ፡ ደረቅም ፡ ይኾናል ።

6 ፤ ወንዞቹም ፡ ይገማሉ ፥ የግብጽም ፡ መስኖች ፡ ያንሳሉ ፡ ይደርቃሉም ፤ ደንገልና ፡ ቄጤማ ፡ ይጠወልጋሉ ።

7 ፤ በአባይ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ያለው ፡ መስክ ፡ በአባይም ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ የተዘራ ፡ ዕርሻ ፡ ኹሉ ፡
ይደርቃል ፥ ይበተንማል ፥ አይገኝምም ።

8 ፤ ዓሣ ፡ አጥማጆቹ ፡ ያዝናሉ ፥ በአባይም ፡ ወንዝ ፡ መቃጥን ፡ የሚጥሉት ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሳሉ ፥ በውሃዎችም ፡ ላይ ፡
መረብ ፡ የሚዘረጉት ፡ ይዝላሉ ።

9 ፤ የተበጠረውንም ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ የሚሠሩ ፥ ነጩንም ፡ ልብስ ፡ የሚሠሩ ፡ ሸማኔዎች ፡ ያፍራሉ ።

10 ፤ ደገፋዎቿም ፡ ኹሉ ፡ ይሰባበራሉ ፥ የደመ ፡ ወዘኛዎችም ፡ ነፍስ ፡ ትተክዛለች ።

11 ፤ የጣኔዎስ ፡ አለቃዎች ፡ ፍጹም ፡ ሰነፎች ፡ ናቸው ፤ ፈርዖንን ፡ የሚመክሩ ፡ ጥበበኛዎች ፡ ምክራቸው ፡ ድንቍርና ፡
ኾነች ። ፈርዖንን ፦ እኛ ፡ የጥበበኛዎች ፡ ልጆች ፡ የቀደሙም ፡ ነገሥታት ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ እንዴት ፡ ትሉታላችኹ ፧

12 ፤ አኹንሳ ፡ ጥበበኛዎችኽ ፡ የት ፡ አሉ ፧ አኹን ፡ ይንገሩኽ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡
ያሰበውን ፡ ይወቁ ።



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ የጣኔዎስ ፡ አለቃዎች ፡ ሰነፎች ፡ ኾነዋል ፥ የሜምፎስም ፡ አለቃዎች ፡ ተሸንግለዋል ፤ የነገዶቿ ፡ የማእዘን ፡
ድንጋዮች ፡ የኾኑ ፡ ግብጽን ፡ አሳቱ ።

14 ፤ እግዚአብሔር ፡ የጠማምነትን ፡ መንፈስ ፡ በውስጧ ፡ ደባልቋል ፤ ሰካር ፡ በትፋቱ ፡ እንዲስት ፡ እንዲሁ ፡ ግብጽን ፡
በሥራዋ ፡ ኹሉ ፡ አሳቱ ።

15 ፤ ራስ ፡ ወይም ፡ ዥራት ፡ የሰሌን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ እንግጫ ፡ ቢኾን ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ ሥራ ፡ ለግብጽ ፡
አይኾንላትም ።

16 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ግብጻውያን ፡ እንደ ፡ ሴቶች ፡ ይኾናሉ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡
ከሚያንቀሳቅሳት ፡ ከእጁ ፡ መንቀሳቀስ ፡ የተነሣ ፡ ይሸበራሉ ፡ ይፈሩማል ።

17 ፤ የይሁዳም ፡ ምድር ፡ ግብጽን ፡ የምታስደነግጥ ፡ ትኾናለች ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመከረባት ፡ ምክር ፡
የተነሣ ፡ ወሬዋን ፡ የሚሰማ ፡ ኹሉ ፡ ይፈራል ።

18 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በከነዓን ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፥ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ የሚምሉ ፡
ዐምስት ፡ ከተማዎች ፡ ይኾናሉ ፤ ከነዚህም ፡ አንዲቱ ፡ የጥፋት ፡ ከተማ ፡ ተብላ ፡ ትጠራለች ።

19 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ መካከል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፥ በዳርቻዋም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዐምድ ፡
ይኾናል ።

20 ፤ ይህም ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ምልክትና ፡ ምስክር ፡ ይኾናል ፤ ከሚያስጨንቋቸው ፡
የተነሣ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጮኻሉና ፥ ርሱም ፡ መድኀኒትንና ፡ ኀያልን ፡ ሰዶ ፡ ያድናቸዋልና ።

21 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ የታወቀ ፡ ይኾናል ፥ ግብጻውያንም ፡ እግዚአብሔርን ፡
ያውቃሉ ፤ በመሥዋዕትና ፡ በቍርባን ፡ ያመልካሉ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ስእለት ፡ ይሳላሉ ፡ ይፈጽሙትማል ።

22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ግብጽን ፡ ይመታታል ፤ ይመታታል ፡ ይፈውሳታልም ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመለሳሉ ፡
ርሱም ፡ ይለመናቸዋል ፡ ይፈውሳቸውማል ።

23 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከግብጽ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ መንገድ ፡ ይኾናል ፥ አሶራዊውም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፥ ግብጻዊውም ፡ ወደ ፡
አሶር ፡ ይገባል ፤ ግብጻውያንም ፡ ከአሶራውያን ፡ ጋራ ፡ ይሰግዳሉ ።

24 ፤ 25 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡— ሕዝቤ ፡ ግብጽ ፥ የእጄም ፡ ሥራ ፡ አሶር ፥ ርስቴም ፡ እስራኤል ፡ የተባረከ ፡
ይኹን ፡ ብሎ ፡ ይባርካቸዋልና ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ እስራኤል ፡ ለግብጽና ፡ ለአሶር ፡ ሦስተኛ ፡ ይኾናል ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡
በረከት ፡ ይኾናል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 20 ።

1 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሳርጎን ፡ ተርታንን ፡ በሰደደ ፡ ጊዜ ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ አዛጦን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ አዛጦንንም ፡ ወግቶ ፡
በያዛት ፡ ጊዜ ፥

2 ፤ በዚያ ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓሞጽን ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስን ፡— ኺድ ፥ ማቅኽን ፡ ከወገብኽ ፡
አውጣ ፥ ጫማኽንም ፡ ከእግርኽ ፡ አውልቅ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። እንዲህም ፡ አደረገ ፥ ዕራቍቱንም ፡ ባዶ ፡ እግሩንም ፡
ኼደ ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፡— ባሪያዬ ፡ ኢሳይያስ ፡ በግብጽና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለምልክትና ፡
ለተኣምራት ፡ ሊኾን ፡ ዕራቍቱንና ፡ ባዶ ፡ እግሩን ፡ እንደ ፡ ኼደ ፥

4 ፤ እንዲሁ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የግብጽንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምርኮ ፥ ጐበዛዝቱንና ፡ ሽማግሌዎቹን ፥ ዕራቍታቸውንና ፡
ባዶ ፡ እግራቸውን ፡ አድርጎ ፥ ገላቸውንም ፡ ገልጦ ፥ ለግብጽ ፡ ጕስቍልና ፡ ይነዳቸዋል ።

5 ፤ እነርሱም ፡ ከተስፋቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ከትምክሕታቸውም ፡ ከግብጽ ፡ የተነሣ ፡ ይፈራሉ ፡ ያፍሩማል ፤

6 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በዚች ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ የሚቀመጡ ፡— እንሆ ፥ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንድን ፡ ዘንድ ፥ ለርዳታ ፡ ወደ ፡



www.ethiopianorthodox.org

እነርሱ ፡ የሸሸንበት ፡ ተስፋችን ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ እኛስ ፡ እንዴት ፡ እናመልጣለን ፧ ይላሉ ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ምዕራፍ ፡ 21 ።

1 ፤ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ስላለው ፡ ስለ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከደቡብ ፡
እንደሚወጣ ፥ እንዲሁ ፡ ከሚያስፈራ ፡ አገር ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ይወጣል ።

2 ፤ ከባድ ፡ ራእይ ፡ ተነገረኝ ፤ ወንጀለኛው ፡ ይወነጅላል ፥ አጥፊውም ፡ ያጠፋል ። ዔላም ፡ ሆይ ፥ ውጪ ፤ ሜዶን ፡
ሆይ ፥ ክበቢ ፤ ትካዜውን ፡ ሁሉ ፡ አስቀርቻለሁ ።

3 ፤ ስለዚህ ፥ ወገቤ ፡ ሕመም ፡ ተሞላ ፤ እንደምትወልድ ፡ ሴት ፡ ምጥ ፡ ያዘኝ ፤ ከሕመሜ ፡ የተነሣ ፡
አልሰማም ፥ ከድንጋጤም ፡ የተነሣ ፡ አላይም ።

4 ፤ ልቤ ፡ ተንበደበደ ፥ ድንጋጤ ፡ አስፈራኝ ፥ ተስፋ ፡ ያደረግሁትም ፡ ድንግዝግዝታ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ኾነብኝ ።

5 ፤ ማዕዱን ፡ ያዘጋጃሉ ፥ ምንጣፉንም ፡ ይዘረጋሉ ፥ ይበሉማል ፥ ይጠጡማል ፤ እናንተ ፡ መሳፍንት ፡
ሆይ ፥ ተነሡ ፥ ጋሻውን ፡ አዘጋጁ ።

6 ፤ ጌታ ፡ እንዲህ ፡ ብሎኛልና ፦ ኺድ ፥ ጉበኛም ፡ አቁም ፥ የሚያየውንም ፡ ይናገር ።

7 ፤ በከብት ፡ የሚቀመጡትን ፥ ኹለት ፡ ኹለት ፡ እየኾኑ ፡ የሚኼዱት ፡ ፈረሰኛዎች ፥ በአህያዎች ፡ የሚቀመጡትንና ፡
በግመሎች ፡ የሚቀመጡትን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ ትጋት ፡ አስተውሎ ፡ ተግቶም ፡ ያድምጥ ።

8 ፤ ያየውም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ዘወትር ፡ በማማ ፡ ላይ ፡ ቆሜያለኹ ፥ ሌሊቱንም ፡ ኹሉ ፡ በመጠበቂያዬ ፡
ላይ ፡ ተተክያለኹ ፥

9 ፤ እንሆም ፥ በፈረሶች ፡ የሚቀመጡ ፥ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ኹነው ፡ የሚኼዱ ፡ ፈረሰኛዎች ፡ ይመጣሉ ፡ ብሎ ፡
ጮኸ ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ባቢሎን ፡ ወደቀች ፡ ወደቀች ፥ የተቀረጹም ፡ የአማልክቷ ፡ ምስሎች ፡ ኹሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ተጥለው ፡ ደቀቁ ፡ አለ ።

10 ፤ እናንተ ፡ በዐውድማዬ ፡ ላይ ፡ የተወቃችኹ ፡ የዐውድማዬ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ፡ የሰማኹትን ፡ ነገርኋችኹ ።

11 ፤ ስለ ፡ ኤዶምያስ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። አንዱ ፡ ከሴይር ። ጉበኛ ፡ ሆይ ፥ ሌሊቱ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፧ ጉበኛ ፡
ሆይ ፥ ሌሊቱ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠራኝ ።

12 ፤ ጉበኛውም ፦ ይነጋል ፡ ድግሞም ፡ ይመሻል ፤ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ ብትወዱ ፡ ጠይቁ ፤ ተመልሳችኹም ፡ ኑ ፡ አለ ።

13 ፤ ስለ ፡ ዐረብ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። የድዳናውያን ፡ ነጋዴዎች ፡ ሆይ ፥ በዐረብ ፡ ዱር ፡ ውስጥ ፡ ታድራላችኹ ።

14 ፤ በቴማን ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ወደተጠሙት ፡ ሰዎች ፡ ውሃ ፡ አምጡ ፡ እንጀራ ፡ ይዛችኹ ፡ የሸሹትን ፡ ሰዎች ፡
ተቀበሏቸው ።

15 ፤ ከሰይፍ ፥ ከተመዘዘው ፡ ሰይፍ ፥ ከተለጠጠውም ፡ ቀስት ፡ ከጽኑም ፡ ሰልፍ ፡ ሸሽተዋልና ።

16 ፤ ጌታ ፡ እንዲህ ፡ ብሎኛልና ፦ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ዓመት ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የቄዳር ፡ ክብር ፡ ኹሉ ፡
ይጠፋል ፤

17 ፤ ከቀስተኛዎች ፡ ቍጥር ፡ የቀሩት ፥ የቄዳር ፡ ልጆች ፡ ኀያላን ፥ ያንሳሉ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
ተናግሯልና ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ምዕራፍ ፡ 22 ።

1 ፤ ስለራእይ ፡ ሸለቆ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። እናንተ ፡ ኹላችኹ ፡ ወደ ፡ ሰገነት ፡ መውጣታችኹ ፡ ምን ፡ ኾናችኋል ፧

2 ፤ ጩኸትና ፡ ፍጅት ፡ የተሞላብሽ ፡ ከተማ ፥ ደስታ ፡ ያለሽ ፡ ከተማ ፡ ሆይ ፥ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ የተገደሉት ፡ በሰይፍ ፡



www.ethiopianorthodox.org

የተገደሉ ፡ አይደሉም ፥ በሰልፍም ፡ የሞቱ ፡ አይደሉም ።

3 ፤ አለቃዎችሽ ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ሸሹ ፥ ያለቀስትም ፡ ተማረኩ ፤ ከሩቅ ፡ ሸሽተው ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ የተገኙት ፡
ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ታሰሩ ።

4 ፤ ስለዚህ ፦ ፊታችኹን ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አርቁ ፤ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ስለ ፡ ሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጥፋት ፡
ታጽናኑኝ ፡ ዘንድ ፡ አትድከሙ ፡ አልኹ ።

5 ፤ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የድንጋጤና ፡ የመረገጥ ፡ የድብልቅልቅም ፡ ቀን ፥ የቅጥርም ፡ መፍረስ ፡
ወደ ፡ ተራራም ፡ መጮኽ ፡ በራእይ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ኾኗል ።

6 ፤ ዔላምም ፡ ከሠረገለኛዎችና ፡ ከፈረሰኛዎች ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ አፎቱን ፡ ተሸከመ ፥ ቂርም ፡ ጋሻውን ፡ ገለጠ ።

7 ፤ መልካሞቹንም ፡ ሸለቆዎችሽን ፡ ሠረገላዎች ፡ ሞሉባቸው ፥ ፈረሰኛዎችም ፡ መቆሚያቸውን ፡ በበር ፡ ላይ ፡ አደረጉ ።

8 ፤ የይሁዳንም ፡ መጋረጃ ፡ ገለጠ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በዱር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ ተመለከትኽ ፥

9 ፤ የዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ፍራሾች ፡ እንደ ፡ በዙ ፡ አይታችኋል ፥ የታችኛውንም ፡ ኵሬ ፡ ውሃ ፡ አከማችታችኋል ፥

10 ፤ የኢየሩሳሌምን ፡ ቤቶች ፡ ቈጠራችኹ ፡ ቅጥሩንም ፡ ለማጥናት ፡ ቤቶችን ፡ አፈረሳችኹ ።

11 ፤ በአሮጌው ፡ ኵሬ ፡ ላለው ፡ ውሃ ፡ በኹለቱ ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ መከማቻ ፡ ሠራችኹ ፤ ይህን ፡ ያደረገውን ፡ ግን ፡
አልተመለከታችኹም ፥ ቀድሞ ፡ የሠራውንም ፡ አላያችኹም ።

12 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ልቅሶና ፡ ወደ ፡ ዋይታ ፡ ራስን ፡ ወደ ፡ መንጨትና ፡
ማቅንም ፡ ወደ ፡ መልበስ ፡ ጠራ ።

13 ፤ እንሆም ፥ ሐሤትና ፡ ደስታ ፡ በሬውንና ፡ በጉንም ፡ ማረድ ፡ ሥጋንም ፡ መብላት ፡ የወይን ፡ ጠጅንም ፡ መጠጣት ፡
ኾነዋል ፤ እናንተ ፦ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ብላችኋል ።

14 ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጆሮ ፡ ተሰማ ፦ እስክትሞቱ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ በደል ፡ በእውነት ፡
አይሰረይላችኹም ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

15 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ተሾመው ፡ ወደዚህ ፡ አዛዥ ፡ ወደ ፡
ሳምናስ ፡ ኺድ ፥ እንዲህም ፡ በለው ፦

16 ፤ መቃብር ፡ በዚህ ፡ ያስወቀርኽ ፥ ከፍ ፡ ባለው ፡ ስፍራ ፡ መቃብር ፡ ያሠራኽ ፥ በድንጋይም ፡ ውስጥ ፡ ለራስኽ ፡
መኖሪያ ፡ ያሳነጽኽ ፥ በዚህ ፡ ምን ፡ አለኽ ፤ በዚህስ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ አለ ፤

17 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በኀይል ፡ ወርውሮ ፡ ይጥልኻል ፥ አጠንክሮም ፡ ይጨብጥኻል ።

18 ፤ ጠቅልሎም ፡ ያንከባልልኻል ፥ ወደ ፡ ሰፊዱቱም ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ኳስ ፡ ይጥልኻል ፤ አንተ ፡ የጌታኽ ፡ ቤት ፡ ዕፍረት!
በዚያ ፡ ትሞታለኽ ፥ በዚያም ፡ የክብርኽ ፡ ሠረገላዎች ፡ ይኾናሉ ።

19 ፤ ከአዛዥነት ፡ ሥራኽ ፡ አሳድድኻለኹ ፥ ከሹመትኽም ፡ ትሻራለኽ ።

20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ባሪያዬን ፡ የኬልቅያስን ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄምን ፡ እጠራለኹ ፥

21 ፤ መጐናጸፊያኽንም ፡ አለብሰዋለኹ ፥ በመታጠቂያኽም ፡ አስታጥቀዋለኹ ፥ ሹመትኽንም ፡ በእጁ ፡ አሳልፌ ፡
እሰጠዋለኹ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለይሁዳም ፡ ቤት ፡ አባት ፡ ይኾናል ።

22 ፤ የዳዊትንም ፡ ቤት ፡ መክፈቻ ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ አኖራለኹ ፤ ርሱም ፡ ይከፍታል ፡ የሚዘጋም ፡ የለም ፡ ርሱም ፡
ይዘጋል ፡ የሚከፍትም ፡ የለም ።

23 ፤ በታመነም ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ችንካር ፡ እተክለዋለኹ ፥ ለአባቱም ፡ ቤት ፡ የክብር ፡ ዙፋን ፡ ይኾናል ።

24 ፤ የአባቱንም ፡ ቤት ፡ ክብር ፡ ኹሉ ፡ ልጆቹንም ፡ የልጅ ፡ ልጆቹንም ፥ ከጽዋ ፡ ዕቃ ፡ ዠምሮ ፡ እስከማድጋ ፡ ዕቃ ፡
ድረስ ፥ ታናናሹን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ይሰቅሉበታል ።

25 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ በታመነው ፡ ስፍራ ፡ የተከለው ፡ ችንካር ፡ ይወልቃል ፡



www.ethiopianorthodox.org

ተሰብሮም ፡ ይወድቃል ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተሰቀለው ፡ ሸክም ፡ ይጠፋል ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ምዕራፍ ፡ 23 ።

1 ፤ ስለ ፡ ጢሮስ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ሆይ ፥ አልቅሱ ፤ ፈርሷልና ፥ ቤት ፡ የለም ፥ መግባትም ፡ የለም ፤ ከኪቲም ፡ አገር ፡ ዝምድ ፡ ተገልጦላቸዋል ።

2 ፤ እናንተ ፡ በደሴት ፡ የምትኖሩ ፡ በባሕርም ፡ የምትሻገሩ ፡ የሲዶና ፡ ነጋዴዎች ፡ ንግድ ፡ የሞሉባችኹ ፡ ሆይ ፥ ጸጥ ፡ በሉ ።

3 ፤ የሺሖር ፡ ዘርና ፡ የአባይ ፡ ወንዝ ፡ መከር ፡ በብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ላይ ፡ ገቢዋ ፡ ነበረ ፤ ርሷም ፡ የአሕዛብ ፡ መናገሻ ፡ ነበረች ።

4 ፤ ሲዶና ፡ ሆይ ፥ ባሕር ፥ የባሕር ፡ ምሽግ ፦ አላማጥኹም ፥ አልወለድኹም ፤ ጕበዛዝትንም ፡ አላሳደግኹም ፥ ደናግልንም ፡ አላሳደግኹም ፡ ብሎ ፡ ተናግሯልና ፥ ዕፈሪ ።

5 ፤ ወሬዋ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በጢሮስ ፡ ወሬ ፡ ምጥ ፡ ይይዛቸዋል ።

6 ፤ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ተሻገሩ ፤ እናንተ ፡ በደሴት ፡ የምትኖሩ ፡ አልቅሱ ።

7 ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ተመሥርታ ፡ የነበረችው ፥ በዚያም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ኾና ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ እግሮቿ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ያፈለሷት ፡ የደስታችኹ ፡ ከተማ ፡ ይህች ፡ ናትን ፧

8 ፤ አክሊል ፡ ባስጫነች ፡ ከተማ ፡ በጢሮስ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ የወሰነ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ነጋዴዎቿ ፡ አለቃዎች ፡ ናቸው ፥ በርሷም ፡ የሚሸጡና ፡ የሚለውጡ ፡ የምድር ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

9 ፤ የክብርን ፡ ኹሉ ፡ ትዕቢት ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ የምድርንም ፡ ክቡራን ፡ ኹሉ ፡ ያስንቅ ፡ ዘንድ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወስኖታል ።

10 ፤ የተርሴስ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የሚከለክልሽ ፡ የለምና ፡ እንደ ፡ አባይ ፡ ወንዝ ፡ በአገርሽ ፡ ላይ ፡ ጕርፈሽ ፡ ዕለፊ ።

11 ፤ በባሕር ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፡ መንግሥታትንም ፡ አናወጠ ፤ ምሽጎቿንም ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለከነዓን ፡ አገር ፡ አዘዘ ።

12 ፤ ርሱም ፦ አንቺ ፡ የተበደልሽ ፡ የሲዶና ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ከእንግዲህ ፡ወዲህ ፡ ደስ ፡ አይበልሽ ፤ ተነሥተሽ ፡ ወደ ፡ ኪቲም ፡ ተሻገሪ ፥ በዚያም ፡ ደግሞ ፡ አታርፊም ፡ አለ ።

13 ፤ እንሆ ፥ የከለዳውያን ፡ አገር! ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ኾኖ ፡ አይገኝም ፤ አሶራውያን ፡ ለምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ሰጥተውታል ፤ ግንቦቻቸውን ፡ ሠሩ ፥ አዳራሾቿንም ፡ አፈረሱ ፥ ባድማም ፡ አደረጓት ።

14 ፤ እናንተ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ሆይ ፥ ምሽጋችኹ ፡ ፈርሷልና ፥ ዋይ ፡ በሉ ።

15 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ጢሮስ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ የተረሳች ፡ ትኾናለች ፤ ከሰባ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለጢሮስ ፡ በጋለሞታ ፡ ዘፈን ፡ እንደሚኾን ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

16 ፤ አንቺ ፡ የተረሳሽ ፡ ጋለሞታ ፡ ሆይ ፥ መሰንቆ ፡ ያዝ ፡ በከተማ ፡ ላይም ፡ ዙሪ ፤ መታሰቢያም ፡ ይኾንልሽ ፡ ዘንድ ፡ ዜማን ፡ አሳምሪ ፡ ዘፈንሽንም ፡ አብዢ ።

17 ፤ ከሰባ ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጢሮስን ፡ ይጐበኛታል ፥ ወደ ፡ ዋጋዋም ፡ ትመለሳለች ፥ ደግሞም ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ከኾኑ ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ትገለሙታለች ።

18 ፤ ንግዷና ፡ ዋጋዋ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ፤ ንግዷም ፡ በልተው ፡ ይጠግቡ ፡ ዘንድ ፡ ማለፊያም ፡ ልብስ ፡ ይለብሱ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለሚኖሩ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ በዕቃ ፡ ቤትና ፡ በግምጃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አይከተትም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 24 ።

1 ፤ እነሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ምድርን ፡ ባዶ ፡ ያደርጋታል ፥ ባድማም ፡ ያደርጋታል ፥ ይገለብጣትማል ፥ በርሷም ፡ የተቀመጡትን ፡ ይበትናል ።

2 ፤ እንደ ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲሁ ፡ ካህኑ ፥ እንደ ፡ ባሪያውም ፡ እንዲሁ ፡ ጌታው ፥ እንደ ፡ ባሪያዪቱም ፡ እንዲሁ ፡ እመቤቷ ፥ እንደሚገዛም ፡ እንዲሁ ፡ የሚሸጠው ፥ እንደ ፡ አበዳሪውም ፡ እንዲሁ ፡ ተበዳሪው ፥ እንደ ፡ ዕዳ ፡ አስከፋዩም ፡ እንዲሁ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ይኾናል ።

3 ፤ ምድር ፡ መፈታትን ፡ ትፈታለች ፥ ፈጽማም ፡ ትበላሻለች ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሯልና ።

4 ፤ ምድርም ፡ አለቀሰች ፥ ረገፈችም ፤ ዓለም ፡ ደከመች ፥ ረገፈችም ፤ የምድርም ፡ ሕዝብ ፡ ታላላቆች ፡ ደከሙ ።

5 ፤ ምድርም ፡ ከሚቀመጡባት ፡ በታች ፡ ረክሳለች ፥ ሕጉን ፡ ተላልፈዋልና ፥ ሥርዐቱንም ፡ ለውጠዋልና ፥ የዘለዓለሙንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርሰዋልና ።

6 ፤ ስለዚህ ፥ መርገም ፡ ምድርን ፡ ትበላለች ፥ በርሷም ፡ የተቀመጡ ፡ ይቀጣሉ ፤ ስለዚህ ፥ የምድር ፡ ሰዎች ፡ ይቃጠላሉ ፥ ጥቂት ፡ ሰዎችም ፡ ይቀራሉ ።

7 ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አለቀሰች ፥ የወይን ፡ ንግድ ፡ ደከመች ፥ ልባቸው ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ተከዙ ።

8 ፤ የከበሮው ፡ ሐሤት ፡ ቀርቷል ፥ የደስተኛዎች ፡ ድምፅ ፡ ዝም ፡ ብሏል ፥ የመሰንቆ ፡ ደስታ ፡ ቀርቷል ።

9 ፤ እየዘፈኑም ፡ የወይን ፡ ጠጅን ፡ አይጠጡትም ፥ የሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ ለሚጠጡት ፡ መራራ ፡ ይኾናል ።

10 ፤ ባድማ ፡ የኾነችው ፡ ከተማ ፡ ፈረሰች ፤ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ማንም ፡ እንዳይገባበት ፡ ተዘጋ ።

11 ፤ ስለወይኑም ፡ ጠጅ ፡ በአደባባይ ፡ ጩኸት ፡ ይኾናል ፤ ደስታ ፡ ኹሉ ፡ ጨልሟል ፥ የምድርም ፡ ሐሤት ፡ ፈርሷል ።

12 ፤ ከተማዪቱም ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፥ በሯም ፡ በጥፋት ፡ ተመትቷል ።

13 ፤ የወይራን ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ መምታት ፥ ከወይንም ፡ መከር ፡ በኋላ ፡ ቃርሚያውን ፡ እንደ ፡ መልቀም ፥ እንዲሁ ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ይኾናል ።

14 ፤ እነዚህ ፡ ድምፃቸውን ፡ ያነሣሉ ፥ እልልም ፡ ይላሉ ፥ ስለእግዚአብሔር ፡ ክብርም ፡ ከባሕር ፡ ይጣራሉ ።

15 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔርን ፡ በምሥራቅ ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ በባሕር ፡ ደሴቶች ፡ አክብሩ ።

16 ፤ ለጻድቁ ፡ ክብር ፡ ይኹን ፡ የሚለውን ፡ ዝማሬ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ሰምተናል ። እኔ ፡ ግን ፦ ከሳኹ ፥ ከሳኹ ፥ ወዮልኝ! ወንጀለኛዎች ፡ ወንጅለዋል ፤ ወንጀለኛዎች ፡ እጅግ ፡ ወንጅለዋል ፡ አልኹ ።

17 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የምትኖር ፡ ሆይ ፥ ፍርሀትና ፡ ገደል ፡ ወጥመድም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አሉ ።

18 ፤ የሰማይ ፡ መስኮቶች ፡ ተከፍተዋልና ፥ የምድርም ፡ መሠረት ፡ ተናውጣለችና ፥ ከፍርሀት ፡ ድምፅ ፡ የሸሸ ፡ በገደል ፡ ይወድቃል ፥ ከገደልም ፡ የወጣ ፡ በወጥመድ ፡ ይያዛል ።

19 ፤ ምድር ፡ ተሰባበረች ፥ ምድር ፡ ፈጽማ ፡ ደቀቀች ፥ ምድር ፡ ተነዋወጠች ።

20 ፤ ምድር ፡ እንደ ፡ ሰካር ፡ ሰው ፡ ትንገዳገዳለች ፥ እንደ ፡ ዳስም ፡ ትወዛወዛለች ፤ መተላለፏ ፡ ይከብድባታል ፥ ትወድቅማለች ፥ ደግማም ፡ አትነሣም ።

21 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንደዚህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ በከፍታ ፡ ያለውን ፡ ሰራዊት ፡ በከፍታ ፡ ላይ ፥ በምድርም ፡ ያሉትን ፡ ነገሥታት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይቀጣቸዋል ።

22 ፤ ግዞተኛዎች ፡ በጕድጓድ ፡ እንደሚከማቹ ፡ በአንድነት ፡ ይከማቻሉ ፥ በግዞት ፡ ቤትም ፡ ውስጥ ፡ ተዘግተው ፡ ይኖራሉ ፥ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ይጐበኛሉ ።

23 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ይነግሣልና ፥ በሽማግሌዎቹም ፡ ፊት ፡ ክብር ፡ ይኾናልና ፥ ጨረቃ ፡ ይታወካል ፡ ፀሓይም ፡ ያፍራል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ምዕራፍ ፡ 25 ።

1 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፤ ድንቅን ፡ ነገር ፡ የዱሮ ፡ ምክርን ፡ በታማኝነትና ፡ በእውነት ፡ አድርገኻልና ፥ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግኻለኹ ፥ ስምኽንም ፡ አመሰግናለኹ ።

2 ፤ ከተማዪቱን ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፥ የተመሸገችውን ፡ ከተማ ፡ ውድማ ፡ እንድትኾን ፥ የኃጥአንንም ፡ አዳራሽ ፡ ከተማ ፡ እንዳትኾን ፡ አድርገኻል ፤ ከቶ ፡ አትሠራም ።

3 ፤ ስለዚህ ፥ ኀያላኑ ፡ ወገኖች ፡ ያከብሩኻል ፥ የጨካኞች ፡ አሕዛብ ፡ ከተማም ፡ ትፈራኻለች ።

4 ፤ የጨካኞችም ፡ ቍጣ ፡ እስትንፋስ ፡ ቅጥርን ፡ እንደሚመታ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ ለድኻው ፡ መጠጊያ ፥ ለችግረኛው ፡ በጭንቁ ፡ ጊዜ ፡ መጠጊያ ፥ ከውሽንፍር ፡ መሸሸጊያ ፡ ከሙቀትም ፡ ጥላ ፡ ኾነኻል ።

5 ፤ እንደ ፡ ሙቀት ፡ በደረቅ ፡ ስፍራ ፡ የኃጥአንን ፡ ጩኸት ፡ ዝም ፡ ታሠኛለኽ ፤ ሙቀትም ፡ በደመና ፡ ጥላ ፡ እንዲበርድ ፡ እንዲሁ ፡ የጨካኞች ፡ ዝማሬ ፡ ይዋረዳል ።

6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ የሰባ ፡ ግብዣ ፥ ያረጀ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ ቅልጥም ፡ የሞላባቸው ፡ የሰቡ ፡ ነገሮች ፥ የጥሩና ፡ ያረጀ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ግብዣ ፡ ያደርጋል ።

7 ፤ በዚህም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተጣለውን ፡ መጋረጃ ፥ በአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተዘረጋውን ፡ መሸፈኛ ፡ ያጠፋል ።

8 ፤ ሞትን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይውጣል ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከፊት ፡ ኹሉ ፡ እንባን ፡ ያብሳል ፥ የሕዝቡን ፡ ስድብ ፡ ከምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያስወግዳል ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ።

9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ እንሆ ፥ አምላካችን ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ተስፋ ፡ አድርገነዋል ፥ ያድነንማል ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ጠብቀነዋል ፤ በማዳኑ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ ሐሤትም ፡ እናደርጋለን ፡ ይባላል ።

10 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ታርፋለች ፥ ጭድም ፡ በጭቃ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚረገጥ ፡ እንዲሁ ፡ ሞዐብ ፡ በስፍራው ፡ ይረገጣል ።

11 ፤ ዋናተኛም ፡ ሲዋኝ ፡ እጁን ፡ እንደሚዘረጋ ፥ እንዲሁ ፡ በመካከሉ ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ትዕቢቱን ፡ ከእጁ ፡ ተንኰል ፡ ጋራ ፡ ያዋርዳል ።

12 ፤ የተመሸገውንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለውንም ፡ ቅጥርኽን ፡ ዝቅ ፡ ያደርገዋል ፥ ያዋርደውማል ፥ ወደ ፡ መሬትም ፡ እስከ ፡ ዐፈር ፡ ድረስ ፡ ይጥለዋል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ምዕራፍ ፡ 26 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ቅኔ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ይዘመራል ። የጸናች ፡ ከተማ ፡ አለችን ፤ ለቅጥርና ፡ ለምሽግ ፡ መድኀኒትን ፡ ያኖርባታል ።

2 ፤ እውነትን ፡ የሚጠብቅ ፡ ጻድቅ ፡ ሕዝብ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ በሮችን ፡ ክፈቱ ።

3 ፤ ባንተ ፡ ታምናለችና ፡ ባንተ ፡ ለምትደገፍ ፡ ነፍስ ፡ ፈጽመኽ ፡ በሰላም ፡ ትጠብቃታለኽ ።

4 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ ዐምባ ፡ ነውና ፥ ለዘለዓለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመኑ ።

5 ፤ በከፍታ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ዝቅ ፡ ያደርጋል ፤ ከፍ ፡ ያለችውን ፡ ከተማ ፡ ያዋርዳል ፥ እስከ ፡ መሬትም ፡ ድረስ ፡ ያዋርዳታል ፥ እስከ ፡ ዐፈርም ፡ ድረስ ፡ ይጥላታል ።

6 ፤ እግር ፥ የድኻ ፡ እግርም ፡ የችግረኛም ፡ አረጋገጥ ፥ ትረግጣታለች ።

7 ፤ የጻድቃን ፡ መንገድ ፡ ቅን ፡ ናት ፤ አንተ ፡ ቅን ፡ የኾንኽ ፡ የጻድቃንን ፡ መንገድ ፡ ታቃናለኽ ።

8 ፤ አቤቱ ፥ በፍርድኽ ፡ መንገድ ፡ ተስፋ ፡ አድርገንኻል ፥ ስምኽም ፡ መታሰቢያኽም ፡ የነፍሳችን ፡ ምኞት ፡ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ ፍርድኽን ፡ በምድር ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ የሚኖሩት ፡ ጽድቅን ፡ ይማራሉና ፡ ነፍሴ ፡ በሌሊት ፡ ትናፍቅኻለች ፥ መንፈሴም ፡ በውስጤ ፡ ወዳንተ ፡ ትገሠግሣለች ፡፡

10 ፤ ለኀጢአተኛ ፡ ሞገስ ፡ ቢደረግለት ፡ ጽድቅን ፡ አይማርም ፤ በቅኖች ፡ ምድር ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ያደርጋል ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ግርማ ፡ አያይም ፡፡

11 ፤ አቤቱ ፥ እጅኽ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለች ፡ አላዩምም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ያለኽን ፡ ቅንአት ፡ አይተው ፡ ያፍራሉ ፤ እሳትም ፡ ጠላቶችኽን ፡ ትበላለች ፡፡

12 ፤ አቤቱ ፥ ሥራችንን ፡ ዅሉ ፡ ሠርተኽልናልና ፥ ሰላምን ፡ ትሰጠናለኽ ፡፡

13 ፤ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ሌላዎች ፡ ጌታዎች ፡ ገዝተውናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባንተ ፡ ብቻ ፡ ስምኽን ፡ እናስባለን ፡፡

14 ፤ እነርሱ ፡ ሞተዋል ፥ በሕይወት ፡ አይኖሩም ፤ ጠፍተዋል ፥ አይነሡም ፤ ስለዚህ ፥ አንተ ፡ ጐብኝተኻቸዋል ፥ አጥፍተኻቸውማል ፥ መታሰቢያቸውንም ፡ ዅሉ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አድርገኻል ፡፡

15 ፤ ሕዝብን ፡ አበዛኽ ፥ አቤቱ ፥ ሕዝብን ፡ አበዛኽ ፤ አንተም ፡ ተከበርኽ ፥ የአገሪቱንም ፡ ዳርቻ ፡ ዅሉ ፡ አሰፋኽ ፡፡

16 ፤ አቤቱ ፥ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ፈለጉኽ ፥ በገሰጽኻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ልመናቸውን ፡ ወዳንተ ፡ አፈሰሱ ፡፡

17 ፤ የፀነሰች ፡ ሴት ፡ ለመውለድ ፡ ስትቀርብ ፡ እንደምትጨነቅና ፡ በምጥ ፡ እንደምትጮኽ ፥ አቤቱ ፥ እንዲሁ ፡ በፊትኽ ፡ ኾነናል ፡፡

18 ፤ እኛ ፡ ፀንሰናል ፡ ምጥም ፡ ይዞናል ፥ ነፋስንም ፡ እንደምንወልድ ፡ ኾነናል ፤ በምድርም ፡ ደኅንነት ፡ አላደረግነም ፤ በዓለምም ፡ የሚኖሩ ፡ ይወድቃሉ ፡፡

19 ፤ ሙታንኽ ፡ ሕያዋን ፡ ይኾናሉ ፥ ሬሳዎችም ፡ ይነሣሉ ፡፡ በምድር ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ጠልኽ ፡ የብርሃን ፡ ጠል ፡ ነውና ፥ ምድርም ፡ ሙታንን ፡ ታወጣለችና ፡ ንቁ ፡ ዘምሩም ፡፡

20 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ና ፡ ወደ ፡ ቤትኽም ፡ ግባ ፥ ደጅኽን ፡ በኋላኽ ፡ ዝጋ ፡ ቍጣ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተሸሸግ ፡፡

21 ፤ በምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ በበደላቸው ፡ ምክንያት ፡ ቍጣውን ፡ ያመጣባቸው ፡ ዘንድ ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከስፍራው ፡ ይወጣል ፤ ምድርም ፡ ደሟን ፡ ትገልጣለች ፥ ሙታኗንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትከድንም ፡፡

____________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ፡፡ ____________________

ምዕራፍ ፡ 27 ፡፡

1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣኑን ፡ እባብ ፡ ሌዋታንን ፡ ጠማማውንም ፡ እባብ ፡ ሌዋታንን ፡ በጠንካራ ፡ በታላቅም ፡ በብርቱም ፡ ሰይፍ ፡ ይቀጣል ፥ በባሕርም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዘንዶ ፡ ይገድላል ፡፡

2 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ለተወደደው ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ተቀኙለት ፡፡

3 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠባቂው ፡ ነኝ ፤ ዅልጊዜ ፡ አጠጣዋለኹ ፤ ማንም ፡ እንዳይጐዳው ፡ በሌሊትና ፡ በቀን ፡ እጠብቀዋለኹ ፡፡

4 ፤ አልቈጣም ፤ ሾኽና ፡ ኵርንችት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ምነው ፡ በሰልፍ ፡ በነበሩ! በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተራምጄ ፡ በአንድነት ፡ ባቃጠልኋቸው ፡ ነበር ፡፡

5 ፤ ወይም ፡ ጕልበቴን ፡ ይያዝ ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ ያድርግ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ ያድርግ ፡፡

6 ፤ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ያዕቆብ ፡ ሥር ፡ ይሰዳል ፥ እስራኤልም ፡ ያብባል ፡ ይጨበጭብማል ፤ በፍሬያቸውም ፡ የዓለሙን ፡ ፊት ፡ ይሞላሉ ፡፡

7 ፤ በእውኑ ፡ የመቱትን ፡ እንደ ፡ መታ ፡ እንዲሁ ፡ ርሱን ፡ መታውን ፧ ወይስ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ተገደሉበት ፡ መገደል ፡ ርሱ ፡ ተገድሏልን ፧



www.ethiopianorthodox.org

8 ፤ ነዳቸው ፡ ሰደዳቸው ፡ ቀሠፋቸው ፤ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚነፍስበት ፡ ቀን ፡ በጠንካራ ፡ ዐውሎ ፡ አስወገዳቸው ።

9 ፤ ስለዚህም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችና ፡ የፀሓይ ፡ ምስሎች ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይነሡ ፡ የመሠዊያውን ፡ ድንጋይ ፡ ኹሉ ፡
እንደ ፡ ደቀቀ ፡ እንደ ፡ ኖራ ፡ ድንጋይ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፥ እንዲሁ ፡ የያዕቆብ ፡ በደል ፡ ይሰረያል ፥ ይህም ፡ ኀጢአትን ፡
የማስወገድ ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ ነው ።

10 ፤ የተመሸገችው ፡ ከተማ ፡ ብቻዋን ፡ ኾነች ፤ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾና ፡ የተፈታችና ፡ የተተወች ፡ መኖሪያ ፡
ናት ፤ በዚያም ፡ ጥጃ ፡ ይሰማራል ፡ በዚያም ፡ ይተኛል ፡ ቅርንጫፏንም ፡ ይበላል ።

11 ፤ ጫፎቿ ፡ በደረቁ ፡ ጊዜ ፡ ይሰበራሉ ፥ ሴቶችም ፡ መጥተው ፡ ያቃጥሏቸዋል ፤ የማያስተውል ፡ ሕዝብ ፡
ነውና ፥ ስለዚህ ፡ ፈጣሪው ፡ አይራራለትም ፡ ሠሪውም ፡ ምሕረት ፡ አያደርግለትም ።

12 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ ከወንዝ ፡ ፈሳሽ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡
እኽሉን ፡ ይወቃል ፥ እናንተም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ አንድ ፡ ባንድ ፡ ትሰበሰባላችኹ ።

13 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ታላቅ ፡ መለከት ፡ ይነፋል ፥ በአሶርም ፡ የጠፉ ፥ በግብጽ ፡ ምድርም ፡ የተሰደዱ ፡
ይመጣሉ ፥ በተቀደሰውም ፡ ተራራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰግዳሉ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ምዕራፍ ፡ 28 ።

1 ፤ ለኤፍሬም ፡ ሰካሮች ፡ ትዕቢት ፡ አክሊል ፥ በወይን ፡ ጠጅ ፡ ለተሸነፉ ፡ በወፍራም ፡ ሸለቋቸው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ላለችም ፡
ለረገፈች ፡ ለክብሩ ፡ ጌጥ ፡ አበባ ፡ ወዮ!

2 ፤ እንሆ ፥ በጌታ ፡ ዘንድ ፡ ኀያል ፡ ብርቱ ፡ የኾነ ፡ አለ ። እንደ ፡ በረዶ ፡ ወጨፎ ፥ እንደሚያጠፋም ፡ ዐውሎ ፡
ነፋስ ፥ እንደሚያጥለቀልቅም ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ውሃ ፡ ፈሳሽ ፡ በጠነከረ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ይጥላል ።

3 ፤ የኤፍሬም ፡ ሰካሮች ፡ ትዕቢት ፡ አክሊል ፡ በእግር ፡ ይረገጣል ፤

4 ፤ በወፍራሙ ፡ ሸለቆ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያለች ፡ የረገፈች ፡ የክብሩ ፡ ጌጥ ፡ አበባ ፡ ከመከር ፡ በፊት ፡ አስቀድማ ፡
እንደምትበስል ፡ በለስ ፡ ትኾናለች ፤ ሰው ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ በእጁ ፡ እንዳለች ፡ ይበላታል ።

5 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቀሩት ፡ ሕዝቡ ፡ የክብር ፡ ዘውድና ፡ የጌጥ ፡ አክሊል ፡ ይኾናል ፤

6 ፤ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ለሚቀመጥም ፡ የፍርድ ፡ መንፈስ ፥ ሰልፉን ፡ ወደ ፡ በር ፡ ለሚመልሱም ፡ ኀይል ፡ ይኾናል ።

7 ፤ እነዚህም ፡ ደግሞ ፡ ከወይን ፡ ጠጅ ፡ የተነሣ ፡ ይስታሉ ፥ ከሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ የተነሣ ፡ ይፋንናሉ ፤ ካህኑና ፡
ነቢዩ ፡ ከሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ የተነሣ ፡ ይስታሉ ፥ በወይን ፡ ጠጅም ፡ ይዋጣሉ ፥ ከሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ የተነሣ ፡
ይፋንናሉ ፤ በራእይ ፡ ይስታሉ ፥ በፍርድም ፡ ይሰናከላሉ ።

8 ፤ ማእዱ ፡ ኹሉ ፡ ትፋትንና ፡ ርኵሰትን ፡ ተሞልቷታል ፤ ንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ እንኳ ፡ የለም ።

9 ፤ ዕውቀትን ፡ ለማን ፡ ያስተምረዋል ፥ ወይስ ፡ ወሬ ፡ ማስተዋልን ፡ ለማን ፡ ይሰጣል ፥ ወተትን ፡ ለተዉ ፡ ወይስ ፡
ጡትን ፡ ለጣሉ ፡ ነውን ፥

10 ፤ ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ጥቂት ፡ በዚህ ፡ ጥቂት ፡
በዚያ ፡ ነው ።

11 ፤ በባዕድ ፡ አፍ ፡ በልዩም ፡ ልሳን ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ይናገራል ፤ ርሱም ፦ ዕረፍት ፡ ይህች ፡ ናት ፥

12 ፤ የደከመውን ፡ አሳርፉ ፤ ይህችም ፡ ማረፊያ ፡ ናት ፡ አላቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ መስማትን ፡ እንቢ ፡ አሉ ።

13 ፤ ስለዚህ ፥ ኼደው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲወድቁ ፥ እንዲሰበሩም ፥ ተጠምደውም ፡ እንዲያዙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ጥቂት ፡ በዚህ ፡ ጥቂት ፡ በዚያ ፡
ይኾንላቸዋል ።

14 ፤ ስለዚህ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ የምትገዙ ፡ ፌዘኞዎች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።



www.ethiopianorthodox.org

15 ፤ እናንተም ፦ ከሞት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርገናል ፥ ከሲኦልም ፡ ጋራ ፡ ተማምለናል ፤ ሐሰትን ፡ መሸሸጊያችን ፡
አድርገናልና ፥ በሐሰትም ፡ ተሰውረናልና ፥ የሚትረፈረፍ ፡ መቅሠፍት ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ አይደርስብንም ፡ ስላላችኹ ፥

16 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በጽዮን ፡ ድንጋይን ፡ ለመሠረት ፡
አስቀምጣለኹ ፤ የተፈተነውን ፥ የከበረውን ፥ መሠረቱ ፡ የጸናውን ፡ የማእዘን ፡ ድንጋይ ፤ የሚያምን ፡ አያፍርም ።

17 ፤ ለገመድ ፡ ፍርድን ፡ ለቱንቢም ፡ ጽድቅን ፡ አደርጋለኹ ፤ በረዶውም ፡ የሐሰትን ፡ መሸሸጊያ ፡
ይጠርጋል ፥ ውሃዎችም ፡ መሰወሪያውን ፡ ያሰጥማሉ ።

18 ፤ ከሞትም ፡ ጋራ ፡ ያደረጋችኹት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይፈርሳል ፥ ከሲኦልም ፡ ጋራ ፡ የተማማላችኹት ፡ መሐላ ፡
አይጸናም ፤ የሚትረፈረፍ ፡ መቅሠፍት ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ትረገጡበታላችኹ ።

19 ፤ ባለፈም ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳች኿ል ፤ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ያልፋል ፤ ወሬውንም ፡ ማስተዋል ፡ ድንጋጤ ፡
ይኾናል ።

20 ፤ ሰው ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ ቢተኛ ፡ ዐልጋው ፡ ዐጪር ፡ ነው ፤ ሰውም ፡ ሰውነቱን ፡ መሸፈን ፡ ቢወድ ፡
መጐናጸፊያ ፡ ጠባብ ፡ ነው ።

21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሥራውን ፡ ማለት ፡ እንግዳ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፥ አድራጎቱንም ፡ ማለት ፡ ያልታወቀውን ፡
አድራጎቱን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ በፐራሲም ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይነሣል ፥ በገባዖንም ፡ ሸለቆ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይቈጣል ።

22 ፤ አኹንም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚጸናውን ፡ የጥፋት ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ሰምቻለኹና ፥ እስራት ፡ እንዳይጸናባችኹ ፡ አታፌዙ ።

23 ፤ አድምጡ ፥ ድምፄንም ፡ ስሙ ፤ ልብ ፡ አድርጉ ፥ ንግግሬንም ፡ ስሙ ።

24 ፤ በእውኑ ፡ ገበሬ ፡ ሊዘራ ፡ ኹልጊዜ ፡ ያርሳልን ፧ ወይስ ፡ ኹልጊዜ ፡ ዕርሻውን ፡ ይገለግላልን ፧

25 ፤ ጓሉንስ ፡ ይከሰክሳልን ፧ ዕርሻውን ፡ ባስተካከለ ፡ ጊዜ ፡ ጥቍሩን ፡ አዝሙድ ፥ ከሙኑንም ፥ ስንዴውንም ፡
በተርታ ፥ ገብሱንም ፡ በስፍራው ፥ ዐጃንም ፡ በደረጃው ፡ የሚዘራ ፡ አይደለምን ፧

26 ፤ ይህንም ፡ ብልኀት ፡ አምላኩ ፡ ያስታውቀዋል ፡ ያስተምረውማል ።

27 ፤ ጥቍሩ ፡ አዝሙድ ፡ በተሳለች ፡ መኼጃ ፡ አያኼድም ፥ የሠረገላም ፡ መንኰራኵር ፡ በከሙን ፡ ላይ ፡
አይዞርም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጥቍሩ ፡ አዝሙድ ፡ በሽመል ፥ ከሙኑም ፡ በበትር ፡ ይወቃል ።

28 ፤ የእንጀራ ፡ እኽል ፡ ይደቃልን ፧ ለዘለዓለም ፡ አያኼደውም ፤ የሠረገላውን ፡ መንኰራኵርና ፡ ፈረሶቹን ፡ ምንም ፡
ቢያስኬድበት ፡ አያደቀውም ።

29 ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ድንቅ ፡ ምክር ፡ ከሚመክር ፡ በግብሩም ፡ ማለፊያ ፡ ከኾነው ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ወጥቷል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ምዕራፍ ፡ 29 ።

1 ፤ ዳዊት ፡ ለሰፈረባት ፡ ከተማ ፡ ለአርኤል ፡ ወዮላት! ዓመት ፡ በዓመት ፡ ላይ ፡ ጨምሩ ፥ በዓላትም ፡ ይመለሱ ።

2 ፤ አርኤልንም ፡ አስጨንቃለኹ ፥ ልቅሶና ፡ ዋይታም ፡ ይኾንባታል ፤ እንደ ፡ አርኤልም ፡ ትኾንልኛለች ።

3 ፤ በዙሪያሽም ፡ እሰፍራለኹ ፥ በቅጥርም ፡ ከብቤ ፡ አስጨንቅሻለኹ ፥ ዐምባም ፡ በላይሽ ፡ አቆማለኹ ።

4 ፤ ትዋረጂማለሽ ፥ በመሬትም ፡ ላይ ፡ ኾነሽ ፡ ትናገሪያለሽ ፥ ቃልሽም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ከዐፈር ፡ ይወጣል ፤ ድምፅሽም ፡
ከመሬት ፡ እንደሚወጣ ፡ እንደ ፡ መናፍስት ፡ ጠሪ ፡ ድምፅ ፡ ይኾናል ፥ ቃልሽም ፡ ከዐፈር ፡ ወጥቶ ፡ ይጮኻል ።

5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የጠላቶችሽ ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ደቀቀ ፡ ትቢያ ፥ የጨካኞችም ፡ ብዛት ፡ እንደሚያልፍ ፡ ገለባ ፡ ይኾናል ።

6 ፤ ድንገትም ፡ ፈጥኖ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነጐድጓድ ፥ በምድርም ፡ መናወጥ ፥ በታላቅም ፡
ድምፅ ፥ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፥ በወጨፎም ፥ በምትበላም ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ይጐበኛታል ።



www.ethiopianorthodox.org

7 ፤ በአርኤልም ፡ ላይ ፡ የሚዋጉ ፥ ርሷንና ፡ ምሽጓንም ፡ የሚወጉ ፡ የሚያስጨንቋትም ፥ የአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ሕልምና ፡ እንደ ፡ ሌሊት ፡ ራእይ ፡ ይኾናል ።

8 ፤ ተርቦም ፡ እንደሚያልም ፡ ሰው ፡ ይኾናል ፤ በሕልሙም ፥ እንሆ ፥ ይበላል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ይነቃል ፡ ሰውነቱም ፡ ባዶ ፡ ነው ፤ ተጠምቶም ፡ እንደሚያልም ፡ ሰው ፡ ይኾናል ፤ በሕልሙም ፥ እንሆ ፥ ይጠጣል ፥ ነገር ፡
ግን ፥ ይነቃል ፥ እንሆም ፥ ይዝላል ፡ ሰውነቱም ፡ አምሮት ፡ አለው ፤ እንዲሁ ፡ የጽዮንን ፡ ተራራ ፡ የሚወጉ ፡ የአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ብዛት ፡ ይኾናል ።

9 ፤ ተደነቁ ፡ ደንግጡም ፤ ተጨፈኑም ፡ ዕውሮችም ፡ ኹኑ ፤ በወይን ፡ ጠጅ ፡ አይኹን ፡ እንጂ ፡ ሰከሩ ፤ በሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ አይኹን ፡ እንጂ ፡ ተንገደገዱ ።

10 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእንቅልፍ ፡ መንፈስ ፡ አፍሶባችኋል ፡ ዐይኖቻችኹን ፡ ነቢያትንም ፡ ጨፍኖባችኋል ፡ ራሶቻችኹን ፡ ባለራእዮችን ፡ ሸፍኖባችኋል ።

11 ፤ ራእዩም ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ ታተመ ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ኾኖባችኋል ፤ ማንበብንም ፡ ለሚያውቅ ፦ ይህን ፡ አንብ ፡ ብለው ፡ በሰጡት ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፦ ታትሟልና ፥ አልችልም ፡ ይላቸዋል ፤

12 ፤ ደግሞም ፡ መጽሐፉን ፡ ማንበብን ፡ ለማያውቅ ፦ ይህን ፡ አንብ ፡ ብለው ፡ በሰጡት ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፦ ማንበብ ፡ አላውቅም ፡ ይላቸዋል ።

13 ፤ ጌታም ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በአፉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይቀርባልና ፥ በከንፈሮቹም ፡ ያከብረኛልና ፥ ልቡ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ የራቀ ፡ ነውና ፥ በሰዎች ፡ ሥርዐትና ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ ይፈራኛልና ፥

14 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ድንቅ ፡ ነገርን ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፥ ድንቅ ፡ ነገርን ፡ ተኣምራትንም ፥ እንደ ፡ ገና ፡ አደርጋለኹ ፤ የጥበበኛዎችም ፡ ጥበብ ፡ ትጠፋለች ፥ የአስተዋዮችም ፡ ማስተዋል ፡ ትሰወራለች ።

15 ፤ ምክራቸውን ፡ ጥልቅ ፡ አድርገው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ለሚሰውሩ ፥ ሥራቸውንም ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ አድርገው ። ማን ፡ ያየናል ፤ ወይስ ፡ ማን ፡ ያውቀናል ፤ ለሚሉ ፡ ወዮላቸው!

16 ፤ ይህ ፡ የእናንተ ፡ ጠማምነት ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ጭቃ ፡ የምትቈጠሩ ፡ አይደላችኹምን ፤ በእውኑ ፡ ሥራ ፡ ሠሪውን ፦ አልሠራኸኝም ፡ ይለዋልን ፤ ወይስ ፡ የተደረገው ፡ አድራጊውን ፦ አታስተውልም ፡ ይለዋልን ፤

17 ፤ ሊባኖስ ፡ እንደ ፡ ፍሬያማ ፡ ዕርሻ ፡ ሊለወጥ ፡ ፍሬያማውም ፡ ዕርሻ ፡ እንደ ፡ ዱር ፡ ሊቈጠር ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ የቀረ ፡ አይደለምን ፤

18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ደንቈሮዎች ፡ የመጽሐፍን ፡ ቃል ፡ ይሰማሉ ፥ የዕውሮችም ፡ ዐይኖች ፡ ከጭጋግና ፡ ከጨለማ ፡ ተለይተው ፡ ያያሉ ።

19 ፤ የዋሃን ፡ ደስታቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያበዛሉ ፥ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡ ችግረኛዎችም ፡ ሐሤትን ፡ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ያደርጋሉ ።

20 ፤ ጨካኙ ፡ ሰው ፡ አልቋልና ፥ ፌዘኛውም ፡ ጠፍቷልና ፥ ለኀጢአትም ፡ የደፈጡ ፡ ዅሉ ፡ ይቈረጣሉና ፤

21 ፤ እነዚህም ፡ ሰውን ፡ በነገር ፡ በደለኛ ፡ የሚያደርጉ ፥ በበርም ፡ ለሚገሥጸው ፡ አሽክላ ፡ የሚያኖሩ ፥ ጻድቁንም ፡ በከንቱ ፡ ነገር ፡ የሚያስቱ ፡ ናቸው ።

22 ፤ ስለዚህ ፥ አብርሃምን ፡ የተቤዠ ፡ እግዚአብሔር ፥ ስለያዕቆብ ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያዕቆብ ፡ አኹን ፡ አያፍርም ፥ ፊቱም ፡ አኹን ፡ አይለወጥም ።

23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእጄን ፡ ሥራ ፡ ልጆቹን ፡ በመካከሉ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ስሜን ፡ ይቀድሳሉ ፤ የያዕቆብንም ፡ ቅዱስ ፡ ይቀድሳሉ ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ ይፈራሉ ።

24 ፤ በመንፈስም ፡ የሳቱ ፡ ማስተዋልን ፡ ያውቃሉ ፥ የሚያጕረመርሙም ፡ ትምህርትን ፡ ይቀበላሉ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ምዕራፍ ፡ 30 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ ለዐመፀኛዎች ፡ ልጆች ፡ ወዮላቸው! ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ያልኾነን ፡ ምክር ፡
ይመክራሉ ፥ ኀጢአትንም ፡ በኀጢአት ፡ ላይ ፡ ይጨምሩ ፡ ዘንድ ፡ ከመንፈሴ ፡ ዘንድ ፡ ያልኾነውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ያደርጋሉ ።

2 ፤ ከአፌም ፡ ነገርን ፡ ሳይጠይቁ ፡ በፈርዖን ፡ ኀይል ፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ በግብጽም ፡ ጥላ ፡ ይታመኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
እንዲወርዱ ፡ ይኼዳሉ ።

3 ፤ ስለዚህ ፥ የፈርዖን ፡ ኀይል ፡ ዕፍረት ፥ በግብጽም ፡ ጥላ ፡ መታመን ፡ ስድብ ፡ ይኾንባችኋል ።

4 ፤ አለቃዎች ፡ ምንም ፡ በጣኔዎስ ፡ ቢኾኑ ፥ መልክተኛዎችም ፡ ምንም ፡ ወደ ፡ ሓኔስ ፡ ቢደርሱ ፥

5 ፤ ሾላቸው ፡ ይጠቅሟቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለማይችሉ ፥ ዕፍረትና ፡ ስድብ ፡ እንጂ ፡ ረድኤትና ፡ ረብ ፡ ስለማይኾኑ ፡ ሕዝብ ፡
ያፍራሉ ።

6 ፤ በደቡብ ፡ ስላሉ ፡ እንስሳዎች ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። ተባትና ፡ እንስት ፡ አንበሳ ፡ እፍኝትም ፡ ነዘር ፡ እባብም ፡
በሚወጡባት ፡ በመከራና ፡ በጭንቀት ፡ ምድር ፡ በኩል ፡ ብልጥግናቸውን ፡ በአህያዎች ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡
መዛግብቶቻቸውንም ፡ በግመሎች ፡ ሻኛ ፡ ላይ ፡ እየጫኑ ፡ ወደማይጠቅሟቸው ፡ ሕዝብ ፡ ይኼዳሉ ።

7 ፤ የግብጽ ፡ ርዳታ ፡ ከንቱና ፡ ምናምን ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ ስሙን ፦ በቤት ፡ የሚቀመጥ ፡ ረዓብ ፡ ብዬ ፡ ጠርቼዋለኹ ።

8 ፤ አኹንም ፡ ኺድ ፥ ለሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኾን ፡ በሰሌዳ ፡ ላይ ፡ በመጽሐፍም ፡ ውስጥ ፡
ጻፍላቸው ።

9 ፤ ዐመፀኛ ፡ ወገንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ለመስማት ፡ የማይወዱ ፡ የሐሰት ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ፤

10 ፤ ባለራእዮችን ፦ አትመልከቱ ፡ ይላሉ ፥ ነቢያትንም ፦ ጣፋጩንና ፡ አታላዩን ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ቅኑን ፡ ነገር ፡
አትንገሩን ፡ ከመንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፥

11 ፤ ከጐዳናውም ፡ ዘወር ፡ በሉ ፥ የእስራኤልንም ፡ ቅዱስ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ አስወግዱ ፡ ይሏቸዋል ።

12 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህችን ፡ ቃል ፡ አቃላችኋልና ፥ በግፍና ፡ በጠማምነት ፡
ታምናችኋልና ፥ በርሱም ፡ ተደግፋችኋልና ፥

13 ፤ ስለዚህ ፥ ይህ ፡ በደል ፡ አዘብዝቦ ፡ ለመፍረስ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፥ አፈራረሱም ፡ ፈጥኖ ፡ ድንገት ፡ እንደሚመጣ ፡
እንደ ፡ ረዥም ፡ ቅጥር ፡ ይኾንባችኋል ።

14 ፤ የሸክለኛ ፡ ማድጋ ፡ እንደሚሰበር ፡ ይሰብረዋል ፥ ሳይራራም ፡ ያደቀዋል ፤ ከስባሪውም ፡ እሳት ፡ ከማንደጃ ፡
የሚወስዱበት ፡ ወይም ፡ ውሃ ፡ ከጕድጓድ ፡ የሚቀዱበት ፡ ገል ፡ አይገኝም ።

15 ፤ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በመመለስና ፡ በማረፍ ፡ ትድናላችኹ ፤ በጸጥታና ፡
በመታመን ፡ ኀይል ፡ ይኾንላችኋል ፤ እናንተም ፡ እንቢ ፡ አላችኹ ፥

16 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠን ፡ እንሸሻለን ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ አይኾንም ፡ አላችኹ ፥ ስለዚህም ፡
ትሸሻላችኹ ፤ ደግሞም ፦ በፈጣን ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ እንቀመጣለን ፡ አላችኹ ፥ ስለዚህም ፡ የሚያሳድዷችኹ ፡ ፈጣኖች ፡
ይኾናሉ ።

17 ፤ ካንድ ፡ ሰው ፡ ዛቻ ፡ የተነሣ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ይሸሻሉ ፤ እናንተም ፡ በተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡
ምሰሶ ፥ በኰረብታም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ምልክት ፡ ኾናችኹ ፡ እስክትቀሩ ፡ ድረስ ፥ ከዐምስት ፡ ሰዎች ፡ ዛቻ ፡ የተነሣ ፡
ትሸሻላችኹ ።

18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የፍርድ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይራራላችኹ ፡ ዘንድ ፡
ይታገሣል ፥ ይምራችኹም ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ ርሱን ፡ በመተማመን ፡ የሚጠባበቁ ፡ ኹሉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

19 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ በጽዮን ፡ የምትኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታለቅስም ፤ በጩኸትም ፡
ድምፅ ፡ ይራራልኻል ፥ በሰማኸም ፡ ጊዜ ፡ ይመልስልኻል ።

20 ፤ ጌታም ፡ የጭንቀትን ፡ እንጀራና ፡ የመከራን ፡ ውሃ ፡ ቢሰጥኽም ፡ አስተማሪኽ ፡ እንግዲህ ፡ ከአንተ ፡

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

አይሰወርም ፤ ዐይኖችኽ ፡ ግን ፡ አስተማሪኽን ፡ ያያሉ ፥

21 ፤ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ፈቀቅ ፡ ብትል ፡ ዦሮዎችኽ ፡ በኋላኽ ፦ መንገዱ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ በርሷም ፡ ኺድ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ይሰማሉ ።

22 ፤ በብርም ፡ የተለበጡትን ፡ የተቀረጹትን ፡ ምስሎችኽን ፡ በወርቅም ፡ የተለበጡትን ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎችኽን ፡ ታረክሳለኽ ፤ እንደ ፡ ርኩስም ፡ ነገር ፡ ትጥላቸዋለኽ ፦ ወግዱ ፡ ትላቸውማለኽ ።

23 ፤ በምድርም ፡ ለተዘራው ፡ ዘርኽ ፡ ዝናብ ፡ ይሰጣል ፥ ከምድርም ፡ ፍሬ ፡ የሚወጣ ፡ እንጀራ ፡ ወፍራምና ፡ ብዙ ፡ ይኾናል ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ከብቶችኽ ፡ በሰፊ ፡ መስክ ፡ ይሰማራሉ ፤

24 ፤ መሬትንም ፡ የሚያርሱ ፡ በሬዎችና ፡ አህያዎች ፡ በመንሽና ፡ በወንፊት ፡ የነጻውን ፡ ጨው ፡ ጨው ፡ የሚለውን ፡ ገፈራ ፡ ይበላሉ ።

25 ፤ በታላቅም ፡ እልቂት ፡ ቀን ፡ ግንቦች ፡ በወደቁ ፡ ጊዜ ፡ በረዦሙ ፡ ተራራ ፡ ዂሉ ፡ ከፍ ፡ ባለውም ፡ ኰረብታ ፡ ዂሉ ፡ ላይ ፡ ወንዞችና ፡ የውሃ ፡ ፈሳሾች ፡ ይኾናሉ ።

26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሕዝቡን ፡ ስብራት ፡ በጠገነ ፡ ዕለት ፥ መቅሠፍቱ ፡ የቈሰለውንም ፡ በፈወሰ ፡ ዕለት ፥ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ ብርሃን ፥ የፀሓይም ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ብርሃን ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ ይኾናል ።

27 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከሚነድ ፡ ቍጣ ፡ ከሚትጐለጐልም ፡ ጢስ ፡ ጋራ ፡ ከሩቅ ፡ ይመጣል ፤ ከንፈሮቹም ፡ ቍጣን ፡ የሞሉ ፡ ናቸው ፥ ምላሱም ፡ እንደምትበላ ፡ እሳት ፡ ናት ፤

28 ፤ እስትንፋሱም ፡ አሕዛብን ፡ በአጥፊ ፡ ወንፊት ፡ ሊነፋቸው ፡ እንደሚያጥለቀልቅ ፡ እስከ ፡ ዐንገትም ፡ እንደሚደርስ ፡ ወንዝ ፡ ነው ፥ በሕዝብም ፡ መንጋጋ ፡ የሚያስት ፡ ልጓም ፡ ይኾናል ።

29 ፤ ዝማሬ ፡ በተቀደሰች ፡ የዐውደ ፡ ዓመት ፡ ሌሊት ፡ እንደሚኾን ፡ ዝማሬ ፡ ይኾንላችኋል ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ተራራ ፡ ወደእስራኤል ፡ ዐምባ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንቢልታ ፡ ይዞ ፡ እንደሚኼድ ፡ ሰው ፡ የልብ ፡ ደስታ ፡ ይኾንላችኋል ።

30 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ክቡር ፡ ድምፁን ፡ ያሰማል ፥ የክንዱንም ፡ መውረድ ፡ በሚነድ ፡ ቍጣውና ፡ በምትበላ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ በወጨፎም ፡ በበረዶ ፡ ጠጠርም ፡ ይገልጣል ።

31 ፤ አሶርም ፡ በበትር ፡ ከመታው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣል ።

32 ፤ እግዚአብሔር ፡ በላዩ ፡ በሚያወርድበት ፡ የታዘዘበቱ ፡ የበትር ፡ ድብደባ ፡ ዂሉ ፡ በከበሮና ፡ በመሰንቆ ፡ ይኾናል ፤ በጦርነትም ፡ ክንዱን ፡ አንሥቶ ፡ ይዋጋቸዋል ።

33 ፤ ከቀድሞም ፡ ዦምሮ ፡ የማቃጠያ ፡ ስፍራ ፡ ተዘጋጅታለች ፥ ለንጉሥም ፡ ተበጅታለች ፤ ጥልቅና ፡ ሰፊም ፡ አድርጓታል ፤ እሳትና ፡ ብዙ ፡ ማገዶ ፡ ተከምሯል ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እስትንፋስ ፡ እንደ ፡ ዲን ፡ ፈሳሽ ፡ ያቃጥለዋል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ምዕራፍ ፡ 31 ።

1 ፤ ስለ ፡ ርዳታ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ለሚወርዱ ፡ በፈረሶችም ፡ ለሚደገፉ ፥ ስለ ፡ ብዛታቸውም ፡ በሠረገላዎች ፥ እጅግ ፡ ብርቱዎችም ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በፈረሰኛዎች ፡ ለሚታመኑ ፥ ወደእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ ለማይመለከቱ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ለማይፈልጉ ፡ ወዮላቸው!

2 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ ጠቢብ ፡ ነው ፥ ክፉንም ፡ ነገር ፡ ያመጣል ፥ ቃሉንም ፡ አይመልስም ፥ በክፉም ፡ አድራጊዎች ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ በደልንም ፡ በሚሠሩ ፡ ረዳት ፡ ላይ ፡ ይነሣል ።

3 ፤ ግብጻውያን ፡ ሰዎች ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ አይደሉም ፥ ፈረሶቻቸውም ፡ ሥጋ ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ አይደሉም ፤ እግዚአብሔርም ፡ እጁን ፡ በዘረጋ ፡ ጊዜ ፥ ረጂው ፡ ይሰናከላል ፡ ተረጂውም ፡ ይወድቃል ፥ ዂሉም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይጠፋሉ ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይለኛልና ፦ አንበሳ ፡ ወይም ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ በንጥቂያው ፡ ላይ ፡ሲያገሣ ፥ ብዙ ፡ እረኛዎች ፡ ቢከማቹበት ፡ ከቃላቸው ፡ እንደማይፈራ ፡ ከድምፃቸውም ፡ እንደማይዋረድ ፥ እንዲሁ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኰረብታዋ ፡ ላይ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ይወርዳል ።

5 ፤ እንደሚበር ፡ ወፍ ፡ እንዲሁ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡
ይጋርዳታል ፤ ይከልላታል ፥ ይታደጋታል ፥ ዐልፎም ፡ ያድናታል ።

6 ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ አጥብቃችኹ ፡ ወደዐመፃችኹበት ፡ ተመለሱ ።

7 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ እጆቻቸው ፡ ለኀጢአት ፡ የሠሩላቸውን ፡ የብሩንና ፡ የወርቁን ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡
ይጥላሉ ።

8 ፤ አሶርም ፡ የሰው ፡ ባልኾነ ፡ ሰይፍ ፡ ይወድቃል ፥ የሰውም ፡ ያልኾነ ፡ ሰይፍ ፡ ይበላዋል ፤ ከሰይፍም ፡ ይሸሻሉ ፡
ጕበዛዝቱም ፡ ገባሮች ፡ ይኾናሉ ።

9 ፤ ዐምባው ፡ ከፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ ያልፋል ፥ መሳፍንቱም ፡ ከዐላማው ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣሉ ፥ ይላል ፡ እሳቱ ፡ በጽዮን ፡
እቶኑም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የኾነ ፡ እግዚአብሔር ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ምዕራፍ ፡ 32 ።

1 ፤ እንሆ ፥ ንጉሥ ፡ በጽድቅ ፡ ይነግሣል ፥ መሳፍንትም ፡ በፍርድ ፡ ይገዛሉ ።

2 ፤ ሰውም ፡ ከነፋስ ፡ እንደ ፡ መሸሸጊያ ፡ ከዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ እንደ ፡ መጠጊያ ፥ በጥም ፡ ቦታም ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡
ፈሳሽ ፥ በበረሓም ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ጥላ ፡ ይኾናል ።

3 ፤ የሚያዩትም ፡ ሰዎች ፡ ዐይኖች ፡ አይጨፈኑም ፥ የሚሰሙትም ፡ ዦሮዎች ፡ ያደምጣሉ ።

4 ፤ ጥንቃቄ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ዕውቀትን ፡ ታስተውላለች ፥ የተብታቦችም ፡ ምላስ ፡ ደኅና ፡ አድርጋ ፡
ትናገራለች ።

5 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሰነፍ ፡ ከበርቴ ፡ ተብሎ ፡ አይጠራም ፥ ንፉግም ፡ ለጋስ ፡ አይባልም ።

6 ፤ ሰነፍ ፡ ግን ፡ ስንፍናን ፡ ይናገራል ፥ ልቡም ፡ ዝንጉነትን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ስሕተትን ፡
ይናገር ፡ ዘንድ ፡ የተራበችውንም ፡ ሰውነት ፡ ባዶ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከተጠማም ፡ ሰው ፡ መጠጥን ፡ ይቈርጥ ፡ ዘንድ ፡
በደልን ፡ ይሠራል ።

7 ፤ የንፉግም ፡ ዕቃ ፡ ክፉ ፡ ናት ፤ ችግረኛ ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ርሱ ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ ድኻውን ፡
ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ክፉን ፡ ዐሳብ ፡ ያስባል ።

8 ፤ ከበርቴ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ለመከበር ፡ ያስባል ፥ በመከበርም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

9 ፤ እናንተ ፡ ዓለመኛዎች ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፥ ተነሡ ፡ ድምፄንም ፡ ስሙ ፤ እናንተ ፡ ተማምናችኹ ፡ የምትቀመጡ ፡ ሴቶች ፡
ልጆች ፡ ሆይ ፥ ንግግሬን ፡ አድምጡ ።

10 ፤ እናንተ ፡ ተማምናችኹ ፡ የምትቀመጡ ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፥ ወይኑን ፡ መቍረጥ ፡ ይጠፋልና ፥ ፍሬም ፡ ማከማቸት ፡
አይመጣምና ፡ ከዓመትና ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ትንቀጠቀጣላችኹ ።

11 ፤ እናንተ ፡ ዓለመኛዎች ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፥ ተጠንቀቁ ፤ ተማምናችኹም ፡ የምትቀመጡ ፡
ሆይ ፥ ተንቀጥቀጡ ፤ ልብሳችኹን ፡ አውልቁ ፥ ዕራቍታችኹን ፡ ኹኑ ፥ ወገባችኹንም ፡ በማቅ ፡ ታጠቁ ።

12 ፤ ስለተወደደችውም ፡ ዕርሻ ፡ ስለሚያፈራውም ፡ ወይን ፡ ደረታችኹን ፡ ድቁ ።

13 ፤ በሕዝቤ ፡ ምድር ፡ ላይ ፥ በደስታ ፡ ከተማ ፡ ባሉት ፡ በደስታ ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሾኽና ፡ ኵርንችት ፡
ይወጣባቸዋል ፤

14 ፤ አዳራሹ ፡ ወና ፡ ትኾናለችና ፥ የብዙ ፡ ሰውም ፡ ከተማ ፡ ትለቀቃለችና ፥ ዐምባውና ፡ ግንቡም ፡ ለዘለዓለም ፡
ዋሻ ፥ የምድረ ፡ በዳም ፡ አህያ ፡ ደስታ ፥ የመንጋዎችም ፡ ማሰማሪያ ፡ ይኾናልና ።

15 ፤ ይህም ፥ መንፈስ ፡ ከላይ ፡ እስኪፈስልን ፥ ምድረ ፡ በዳውም ፡ ፍሬያማ ፡ ዕርሻ ፡ እስኪኾን ፥ ፍሬያማውም ፡ ዕርሻ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ዱር ፡ ተብሎ ፡ እስኪቈጠር ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ።

16 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኖራል ፥ ጽድቅም ፡ በፍሬያማው ፡ ዕርሻ ፡ ያድራል ።

17 ፤ የጽድቅም ፡ ሥራ ፡ ሰላም ፥ የጽድቅም ፡ ፍሬ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸጥታና ፡ መታመን ፡ ይኾናል ።

18 ፤ ሕዝቤም ፡ በሰላም ፡ ማደሪያ ፡ በታመነም ፡ ቤት ፡ በጸጥተኛ ፡ ማረፊያ ፡ ይቀመጣል ።

19 ፤ በረዶ ፡ ግን ፡ በዱር ፡ ላይ ፡ ይወርዳል ፥ ከተማም ፡ ፈጽማ ፡ ትዋረዳለች ።

20 ፤ እናንተ ፡ የበሬና ፡ የአህያ ፡ እግር ፡ እየነዳችኹ ፡ በውሃ ፡ ኹሉ ፡ አጠገብ ፡ የምትዘሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ምዕራፍ ፡ 33 ።

1 ፤ አንተ ፡ ሳትጠፋ ፡ የምታጠፋ ፥ ባንተም ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ሳይደረግ ፡ ወንጀል ፡ የምታደርግ ፡ ወዮልኽ! ማጥፋትን ፡ በተውኽ ፡ ጊዜ ፡ ትጠፋለኽ ፤ መወንጀልንም ፡ በተውኽ ፡ ጊዜ ፡ ይወነጅሉኻል ።

2 ፤ አቤቱ ፥ ማረን ፤ አንተን ፡ ተማምነናል ፤ ጧት ፡ ጧት ፡ ክንድ ፡ በመከራም ፡ ጊዜ ፡ ማዳን ፡ ኹነን ።

3 ፤ ከፍጅት ፡ ድምፅ ፡ ወገኖች ፡ ሸሹ ፥ በመነሣትኽም ፡ አሕዛብ ፡ ተበተኑ ።

4 ፤ አንበጣ ፡ እንደሚሰበስብ ፡ ምርኳችኹ ፡ ትሰበሰባለች ፥ ኵብኵባም ፡ እንደሚዘል ፡ ሰዎች ፡ ይዘሉበታል ።

5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአርያም ፡ ተቀምጧልና ፥ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ጽዮንን ፡ በፍርድና ፡ በጽድቅ ፡ ሞላት ።

6 ፤ የዘመንኽም ፡ ጸጥታ ፥ የመድኀኒት ፡ ብዛት ፥ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ መዝገቡ ፡ ነው ።

7 ፤ እንሆ ፥ ኀይለኛዎቻቸው ፡ በሜዳ ፡ ይጮኻሉ ፤ የሰላም ፡ መልእክተኛዎች ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ ያለቅሳሉ ።

8 ፤ መንገዶች ፡ ባድማ ፡ ኾኑ ፥ ተላላፊም ፡ ቀረ ፤ ርሱም ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ አፈረሰ ፡ ከተማዎችንም ፡ ናቀ ፡ ሰውንም ፡ አልተመለከተም ።

9 ፤ ምድሪቱ ፡ አለቀሰች ፡ ከሳችም ፤ ሊባኖስ ፡ ዐፈረ ፡ ጠወለገም ፤ ሳሮን ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነ ፤ ባሳንና ፡ ቀርሜሎስ ፡ ቅጠላቸውን ፡ አረገፉ ።

10 ፤ አኹን ፡ እነሣለኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አኹን ፡ እከበራለኹ ፤ አኹን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እላለኹ ።

11 ፤ ገለባን ፡ ትፀንሳላችኹ ፥ እብቅንም ፡ ትወልዳላችኹ ፤ እስትንፋሳችኹ ፡ የምትበላችኹ ፡ እሳት ፡ ናት ።

12 ፤ አሕዛብም ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ፡ ኖራ ፥ ተቈርጦም ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ፡ ሾኽ ፡ ይኾናሉ ።

13 ፤ እናንተ ፡ በሩቅ ፡ ያላችኹ ፡ የሠራኹትን ፡ ስሙ ፥ እናንተም ፡ በቅርብ ፡ ያላችኹ ፡ ኀይሌን ፡ ዕወቁ ።

14 ፤ በጽዮን ፡ ያሉ ፡ ኀጢአተኛዎች ፡ ፈሩ ፤ መንቀጥቀጥ ፡ ዝንጉዎቹን ፡ ያዘ ፤ ከምትበላ ፡ እሳት ፡ ጋራ ፡ መኖርን ፡ የሚችል ፡ ከእኛ ፡ ማን ፡ አለ ፤ ለዘለዓለምም ፡ ከምትነድ ፡ እሳት ፡ ጋራ ፡ መኖርን ፡ የሚችል ፡ ከእኛ ፡ ማን ፡ አለ ፤

15 ፤ በጽድቅ ፡ የሚኼድ ፡ ቅን ፡ ነገርንም ፡ የሚናገር ፥ በሸንገላ ፡ የሚገኝ ፡ ትርፍን ፡ የሚንቅ ፥ መማለጃን ፡ ከመጨበጥ ፡ እጁን ፡ የሚያራግፍ ፥ ደም ፡ ማፍሰስን ፡ ከመስማት ፡ ጆሮዎቹን ፡ የሚያደነቍር ፥ ክፋትንም ፡ ከማየት ፡ ዐይኖቹን ፡ የሚጨፍን ፡ ነው ።

16 ፤ ርሱ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡ ይቀመጣል ፤ ጠንካራ ፡ ዐምባ ፡ መጠጊያው ፡ ይኾናል ፤ እንጀራም ፡ ይሰጠዋል ፥ ውሃውም ፡ የታመነች ፡ ትኾናለች ።

17 ፤ ዐይኖችኽ ፡ ንጉሥን ፡ በውበቱ ፡ ያዩታል ፤ እነርሱም ፡ በሩቅ ፡ ያለች ፡ ምድርን ፡ ያይዋታል ።

18 ፤ ልብኽም ፡— ጸሓፊ ፡ ወዴት ፡ አለ ፤ መዛኙስ ፡ ወዴት ፡ አለ ፤ ግንቦቹንስ ፡ የቈጠረ ፡ ወዴት ፡ አለ ፤ ብሎ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነገር ፡ ያስባል ።



www.ethiopianorthodox.org

19 ፤ ጨካኙን ፡ ሕዝብ ፥ ቋንቋው ፡ ለማስተዋል ፡ ጥልቅ ፡ የኾነውንና ፡ አንደበቱ ፡ ለማስተዋል ፡ ጸያፍ ፡ የኾነውን ፡ ሕዝብ ፥ አታይም ።

20 ፤ የበዓላችንን ፡ ከተማ ፡ ጽዮንን ፡ ተመልከት ፤ ዐይኖችኽ ፡ የሰላም ፡ ማደሪያ ፥ ካስማው ፡ ለዘለዓለም ፡ የማይነቀል ፡ አውታሩም ፡ ኹሉ ፡ የማይበጠስ ፥ የማይወገድ ፡ ድንኳን ፡ የኾነውን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ያያሉ ።

21 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ የሰፉ ፡ ወንዞችና ፡ የመስኖች ፡ ስፍራ ፡ ኾኖ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ በግርማ ፡ ይኾናል ፤ የሚቀዘፉ ፡ መርከቦች ፡ አይገቡባትም ፥ ታላላቆችም ፡ መርከቦች ፡ አያልፉባትም ።

22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፈራጃችን ፡ ነው ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕግን ፡ ሰጪያችን ፡ ነው ፥ እግዚአብሔር ፡ ንጉሣችን ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ያድነናል ።

23 ፤ ገመዶችኽ ፡ ላልተዋል ፥ ደቀላቸውንም ፡ አላጸኑም ፥ ሸራውንም ፡ መዘርጋት ፡ አልቻሉም ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ ምርኮ ፡ ብዝበዛ ፡ ተከፈለ ፤ ዐንካሳዎች ፡ እንኳ ፡ ብዝበዛውን ፡ በዘበዙ ።

24 ፤ በዚያም ፡ የሚቀመጥ ፦ ታምሜያለኹ ፡ አይልም ፥ በርሷም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ሰዎች ፡ በደላቸው ፡ ይቅር ፡ ይባልላቸዋል ።

______________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 34 ።

1 ፤ እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ቅረቡ ፥ ስሙ ፤ እናንተ ፡ ወገኖች ፡ ሆይ ፥ አድምጡ ፤ ምድርና ፡ መሏዋ ፥ ዓለምና ፡ ከርሷ ፡ የሚወጣ ፡ ኹሉ ፡ ይስሙ ።

2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ መዓቱም ፡ በሰራዊታቸው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ፥ ለመታረድም ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

3 ፤ ከነርሱም ፡ የተገደሉት ፡ ይጣላሉ ፥ የሬሳቸውም ፡ ግማት ፡ ይሸታል ፥ ተራራዎችም ፡ ከደማቸው ፡ የተነሣ ፡ ይርሳሉ ።

4 ፤ የሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ይበሰብሳሉ ፥ ሰማያትም ፡ እንደ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ ይጠቀለላሉ ፥ ከወይንና ፡ ከበለስም ፡ ቅጠል ፡ እንደሚረግፍ ፡ ሰራዊታቸው ፡ ኹሉ ፡ ይረግፋል ።

5 ፤ ሰይፌ ፡ በሰማይ ፡ ኾና ፡ እስክትረካ ፡ ድረስ ፡ ጠጥታለች ፤ እንሆ ፥ በኤዶምያስና ፡ በረገምኹት ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ለፍርድ ፡ ትወርዳለች ።

6 ፤ እግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ በባሶራ ፥ ታላቅም ፡ ዕርድ ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ አለውና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ በደም ፡ ተሞልታለች ፥ በስብም ፥ በበግ ፡ ጠቦትና ፡ በፍየል ፡ ደምም ፥ በአውራም ፡ በግ ፡ ኵላሊት ፡ ስብ ፡ ወፍራለች ።

7 ፤ ጐሽ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፥ ወይፈኖችም ፡ ከኰርማዎች ፡ ጋራ ፡ ይወድቃሉ ፤ ምድራቸውም ፡ በደም ፡ ትረካለች ፥ ዐፈራቸውም ፡ በስብ ፡ ትወፍራለች ።

8 ፤ የእግዚአብሔር ፡ የበቀሉ ፡ ቀን ፥ ስለጽዮንም ፡ ክርክር ፡ የብድራት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

9 ፤ የኤዶምያስም ፡ ፈሳሾች ፡ ዝፍት ፡ ኾነው ፡ ይለወጣሉ ፥ ዐፈሯም ፡ ዲን ፡ ይኾናል ፥ መሬቷም ፡ የሚቃጠል ፡ ዝፍት ፡ ትኾናለች ።

10 ፤ በሌሊትና ፡ በቀንም ፡ አትጠፋም ፥ ጢሷም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይወጣል ፤ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድም ፡ ድረስ ፡ ባድማ ፡ ኾና ፡ ትኖራለች ፤ ለዘለዓለም ፡ ዓለም ፡ ማንም ፡ አያልፍባትም ።

11 ፤ ጭልፊትና ፡ ኀርት ፡ ግን ፡ ይወርሷታል ፤ ጕጕትና ፡ ቍራም ፡ ይኖሩባታል ፤ በላይዋም ፡ የመፍረስ ፡ ገመድና ፡ የባዶነት ፡ ቱንቢ ፡ ይዘረጋባታል ።

12 ፤ መሳፍንቷን ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ይጠራሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ማንም ፡ አይገኝባትም ፤ አለቃዎቿም ፡ ኹሉ ፡ ምናምኖች ፡ ይኾናሉ ።

13 ፤ በአዳራሾቿም ፡ ሾኽ ፡ በቅጥሮቿም ፡ ሳማን ፡ አሜከላ ፡ ይበቅሉባታል ፤ የቀበሮም ፡ ማደሪያና ፡ የሰጐን ፡ ስፍራ ፡ ትኾናለች ።



www.ethiopianorthodox.org

14 ፤ የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ ከተኵላዎች ፡ ጋራ ፡ ይገናኛሉ ፥ አጋንንትም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጠራራሉ ፤ ጅን[260]ም ፡ በዚያ ፡ ትኖራለች ፥ ለርሷም ፡ ማረፊያ ፡ ታገኛለች ።

15 ፤ በዚያም ፡ ዋሊያ ፡ ቤቷን ፡ ትሠራለች ፡ ዕንቍላልም ፡ ትጥላለች ፡ ትቀፈቅፈውማለች ፡ ልጆቿንም ፡ በጥላዋ ፡ ትሰበስባለች ፤ በዚያም ፡ ደግሞ ፡ አሞራዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከባልንጀራዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይሰበሰባሉ ።

16 ፤ በእግዚአብሔር ፡ መጽሐፍ ፡ ፈልጉ ፥ አንብቡም ፤ አፌ ፡ አዟልና ፥ መንፈሱም ፡ ሰብስቧቸዋልና ፥ ከነዚህ ፡ አንዲት ፡ አትጠፋም ፥ ባልንጀራውንም ፡ የሚያጣ ፡ የለም ።

17 ፤ ርሱም ፡ ዕጣ ፡ ጣለባቸው ፥ እጁም ፡ በገመድ ፡ ከፈለችላቸው ፤ ለዘለዓለም ፡ ይገዟታል ፥ ከትውልድም ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ይቀመጡባታል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

ምዕራፍ ፡ 35 ።

1 ፤ ምድረ ፡ በዳውና ፡ ደረቁ ፡ ምድር ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ በረሓውም ፡ ሐሤት ፡ ያደርጋል ፡ እንደ ፡ ጽጌ ፡ ረዳም ፡ ያብባል ።

2 ፤ እጅግ ፡ ያብባል ፡ በደስታና ፡ በዝማሬ ፡ ሐሤትን ፡ ያደርጋል ፤ የሊባኖስ ፡ ክብር ፥ የቀርሜሎስና ፡ የሳሮን ፡ ግርማ ፡ ይሰጠዋል ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ክብር ፡ የአምላካችንንም ፡ ግርማ ፡ ያያሉ ።

3 ፤ የደከሙትን ፡ እጆች ፡ አበርቱ ፥ የላሉትንም ፡ ጕልበቶች ፡ አጽኑ ።

4 ፤ ፈሪ ፡ ልብ ፡ ላላቸው ፦ እንሆ ፥ አምላካችኹ ፡ በበቀል ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ብድራት ፡ ይመጣልና ፥ መጥቶም ፡ ያድናች኿ልና ፥ በርቱ ፥ አትፍሩ ፡ በሏቸው ።

5 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የዕውሮች ፡ ዐይን ፡ ይገለጣል ፤ የደንቈሮዎችም ፡ ጆሮ ፡ ይከፈታል ።

6 ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዐንካሳ ፡ እንደ ፡ ሚዳቋ ፡ ይዘላል ፥ የድዳም ፡ ምላስ ፡ ይዘምራል ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውሃ ፥ በበረሓም ፡ ፈሳሽ ፡ ይፈልቃልና ።

7 ፤ ደረቂቱ ፡ ምድር ፡ ኵሬ ፥ የጥማት ፡ መሬት ፡ የውሃ ፡ ምንጭ ፡ ትኾናለች ፤ ቀበሮ ፡ የተኛበት ፡ መኖሪያ ፡ ልምላሜና ፡ ሸምበቆ ፡ ደንገልም ፡ ይኾንበታል ።

8 ፤ በዚያም ፡ ጐዳናና ፡ መንገድ ፡ ይኾናል ፡ ርሱም ፡ የተቀደሰ ፡ መንገድ ፡ ይባላል ፤ ንጹሓንም ፡ ያልኾኑ ፡ አያልፉበትም ፥ ለንጹሓን ፡ ግን ፡ ይኾናል ፤ ተላላፊዎችና ፡ ሰነፎች ፡ እንኳ ፡ አይስቱበትም ።

9 ፤ አንበሳም ፡ አይኖርበትም ፥ ነጣቂ ፡ አውሬም ፡ አይወጣበትም ፥ ከዚያም ፡ አይገኙም ፤ የዳኑት ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ይኼዳሉ ፤

10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተቤዣቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ እየዘመሩም ፡ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ይመጣሉ ፤ የዘለዓለም ፡ ደስታ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ሐሤትንና ፡ ደስታን ፡ ያገኛሉ ፥ ሐዘንና ፡ ትካዜም ፡ ይሸሻሉ ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ።

ምዕራፍ ፡ 36 ።

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በንጉሡ ፡ በሕዝቅያስ ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ዓመት ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወደተመሸጉት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ወጥቶ ፡ ወሰዳቸው ።

2 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ራፋስቂስን ፡ ከብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ጋራ ፡ ከለኪሶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ላከ ፥ ርሱም ፡ በዐጣቢው ፡ ዕርሻ ፡ መንገድ ፡ ባለችው ፡ በላይኛዪቱ ፡ ኵሬ ፡ መስኖ ፡ አጠገብ ፡ ቆመ ።

3 ፤ የቤቱም ፡ አዛዥ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ጸሓፊውም ፡ ሳምናስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወጡ ።

260 ዕብ. ፥ ልይልይት ፡ (ሊሊት • የሌሊት ፡ ወፍ ፥ አለዚያም ፡ ጕጕት ፤ ግብረ ፡ አጋንንት ፥ ጥንቈላ) ።



www.ethiopianorthodox.org

4 ፤ ራፋስቂስም ፡ አላቸው ፦ ለሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦ ታላቁ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ ይህ ፡ የምትታመንበት ፡ መተማመኛ ፡ ምንድር ፡ ነው ፥

5 ፤ እኔ ፦ ለሰልፍ ፡ የኾነው ፡ ምክርኽና ፡ ኀያልኽ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አልኹ ፤ አኹንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያመፅኸው ፡
በማን ፡ ተማምነኽ ፡ ነው ፥

6 ፤ እንሆ ፥ በዚህ ፡ በተቀጠቀጠ ፡ በሸምበቆ ፡ በትር ፡ በግብጽ ፡ ትታመናለኽ ፤ ሰው ፡ ቢመረኰዘው ፡ ተሰብሮ ፡ በእጁ ፡
ይገባል ፥ ያቈስለውማል ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ለሚታመኑበት ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

7 ፤ አንተም ፦ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንታመናለን ፡ ብትለኝ ፥ ሕዝቅያስ ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፦ በዚህ ፡
መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ስገዱ ፡ ብሎ ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃዎቹንና ፡ መሠዊያዎቹን ፡ ይስፈረሰ ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፥

8 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ከጌታዬ ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ተወራረድ ፥ የሚቀመጡባቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ማግኘት ፡
ቢቻልኽ ፡ እኔ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ፈረሶች ፡ እሰጥኻለኹ ።

9 ፤ ስለ ፡ ሠረገላዎችና ፡ ስለ ፡ ፈረሰኞዎች ፡ በግብጽ ፡ ስትታመን ፥ ከጌታዬ ፡ ባሪያዎች ፡ የሚያንሰውን ፡ የአንዱን ፡
አለቃ ፡ ፊት ፡ ትቃወም ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻልኻል ፥

10 ፤ አኹንም ፡ በእውኑ ፡ ያለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይህን ፡ አገር ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡
ወጥቻለኹን ፥ እግዚአብሔር ፦ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ወጥተኽ ፡ አጥፋው ፡ አለኝ ።

11 ፤ ኤልያቄምና ፡ ሳምናስ ፡ ዮአስም ፡ ራፋስቂስን ፦ እኛ ፡ እንሰማለንና ፡ እባክኽ ፥ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፡ ለባሪያዎችኽ ፡
ተናገር ፤ በቅጥርም ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ሕዝብ ፡ ጆሮ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ አትናገረን ፡ አሉት ።

12 ፤ ራፋስቂስ ፡ ግን ፦ ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ወዳንተና ፡ ወደ ፡ ጌታኽ ፡ ልኮኛልን ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡
ኵሳቸውን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ሽንታቸውንም ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ ወደተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡
አይደለምን ፥ አላቸው ።

13 ፤ ራፋስቂስም ፡ ቆሞ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። የታላቁን ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡
ቃል ፡ ስሙ ።

14 ፤ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፡ ሕዝቅያስ ፡ አያታልላችኹ ፤

15 ፤ ሕዝቅያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ በርግጥ ፡ ያድነናል ፡ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አትሰጥም ፡ ብሎ ፡
በእግዚአብሔር ፡ እንድትታመኑ ፡ አያድርጋችኹ ።

16 ፤ ሕዝቅያስንም ፡ አትስሙ ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡
ውጡ ፤ እያንዳንዳችኹም ፡ ከወይናችኹና ፡ ከበለሳችኹ ፡ ብሉ ፥ ከጕድጓዳችኹም ፡ ውሃ ፡ ጠጡ ፤

17 ፤ ይህም ፡ መጥቼ ፡ ምድራችኹን ፡ ወደምትመስለው ፡ ምድር ፥ እኽልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ እንጀራና ፡ ወይን ፡
ወዳለበት ፡ ምድር ፡ እስካፈልሳችኹ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

18 ፤ ሕዝቅያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያድነናል ፡ ብሎ ፡ እንዳያታልላችኹ ፡ ተጠንቀቁ ። በእውኑ ፡ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡
አገሮቻቸውን ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አድነዋቸዋልን ፥

19 ፤ የሐማትና ፡ የአርፋድ ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ አሉ ፥ የሴፈርዋይም ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ አሉ ፥ ሰማርያን ፡ ከእጄ ፡
አድነዋታልን ፥

20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከእጄ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ከነዚህ ፡ አገሮች ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ አገሩን ፡ ከእጄ ፡
ያዳነ ፡ ማን ፡ ነው ፥

21 ፤ እነርሱም ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ አንዳችም ፡ አልመለሱለትም ፤ ንጉሡ ፡ እንዳይመልሱለት ፡ አዞ ፡ ነበርና ።

22 ፤ የቤቱ ፡ አዛዥ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ጸሓፊውም ፡ ሳምናስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡
ልብሳቸውን ፡ ቀደው ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጡ ፥ የራፋስቂስንም ፡ ቃል ፡ ነገሩት ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ።

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 37 ።

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ንጉሡ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፥ ማቅም ፡ ለበሰ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡
ቤት ፡ ገባ ።

2 ፤ የቤቱንም ፡ አዛዥ ፡ ኤልያቄምን ፡ ጸሓፊውንም ፡ ሳምናስን ፡ የካህናቱንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ ወደ ፡
ነቢዩ ፡ ወደዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ላካቸው ።

3 ፤ እነርሱም ፦ ሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ቀን ፡ የመከራና ፡ የተግሣጽ ፡ የዘለፋም ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ልጆች ፡
የሚወለዱበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ፡ ለመውለድም ፡ ኀይል ፡ የለም ።

4 ፤ ምናልባት ፡ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የላከውን ፡ የራፋስቂስን ፡ ቃል ፡
አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰማ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለሰማው ፡ ቃል ፡ ይገሥጸው ፡ እንደ ፡
ኾነ ፥ ስለዚህ ፡ ለቀረው ፡ ቅሬታ ፡ ጸልይ ፡ አሉት ።

5 ፤ እንዲሁ ፡ የንጉሡ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ መጡ ።

6 ፤ ኢሳይያስም ፦ ለጌታችኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ ስለ ፡
ሰደቡኝ ፥ ስለሰማኸው ፡ ቃል ፡ አትፍራ ።

7 ፤ እንሆ ፥ በላዩ ፡ መንፈስን ፡ እሰዳለኹ ፥ ወሬንም ፡ ይሰማል ፥ ወደ ፡ ምድሩም ፡ ይመለሳል ፤ በምድሩም ፡ በሰይፍ ፡
እንዲወድቅ ፡ አደርጋለኹ ፡ በሉት ፡ አላቸው ።

8 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ከለኪሶ ፡ እንደ ፡ ራቀ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፥ ራፋስቂስ ፡ ተመልሶ ፡ በልብና ፡ ሲዋጋ ፡ አገኘው ።

9 ፤ ርሱም ፦ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ቲርሐቅ ፡ ሊዋጋኽ ፡ መጥቷል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ሰማ ። በሰማም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
ሕዝቅያስ ፡ መልእክተኛዎችን ፡ ላከ ፥

10 ፤ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦ ኢየሩሳሌም ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡
እጅ ፡ አትሰጥም ፡ ብሎ ፡ የምትታመንበት ፡ አምላክኽ ፡ አያታልኽ ።

11 ፤ እንሆ ፥ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፥ እንዴትስ ፡ እንዳጠፏቸው ፡ ሰምተኻል ፤ አንተስ ፡
ትድናለኽን ፧

12 ፤ አባቶቼ ፡ ያጠፏቸውን ፡ ጎዛንን ፥ ካራንን ፥ ራፊስን ፥ በተላሳር ፡ የነበሩትንም ፡ የዔዴንን ፡ ልጆች ፡ የአሕዛብ ፡
አማልክት ፡ አዳኗቸውን ፧

13 ፤ የሐማት ፡ ንጉሥ ፥ የአርፋድ ፡ ንጉሥ ፥ የሴፈርዋይም ፡ ከተማ ፡ ንጉሥ ፥ የሄናና ፡ የዒዋ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

14 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ደብዳቤውን ፡ ከመልእክተኛዎች ፡ እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ አነበበው ፤ ሕዝቅያስም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ ወጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘረጋው ።

15 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ።

16 ፤ አቤቱ ፥ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ብቻኽን ፡ የምድር ፡
መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፤ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፈጥረኻል ።

17 ፤ አቤቱ ፥ ጕሮኽን ፡ አዘንብልና ፡ ስማ ፤ አቤቱ ፥ ዐይንኽን ፡ ክፈትና ፡ እይ ፤ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡
ዘንድ ፡ የላከውን ፡ የሰናክሬም ፡ ቃል ፡ ስማ ።

18 ፤ አቤቱ ፥ በእውነት ፡ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ ዓለሙን ፡ ኹሉ ፡ አገሮቻቸውንም ፡ አፍርሰዋል ፥

19 ፤ አማልክታቸውንም ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጥለዋል ፤ የዕንጨትና ፡ የድንጋይ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡
አማልክት ፡ አልነበሩምና ፡ ስለዚህ ፡ አጥፍተዋቸዋል ።

20 ፤ እንግዲህም ፡ አምላካችን ፡ አቤቱ ፥ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡
ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ከእጁ ፡ አድነን ።



www.ethiopianorthodox.org

21 ፤ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ላከ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለምነኸልና ፥

22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦ ድንግሊቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ቀላል ፡
አድርጋኻለች ፥ በንቀትም ፡ ሥቃብኻለች ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ ራሷን ፡ ነቅንቃብኻለች ።

23 ፤ የተገዳደርኸው ፡ የሰደብኸውስ ፡ ማን ፡ ነው ፤ ቃልኽንስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረግኽበት ፡ ዐይንኽንስ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ያነሣኽበት ፡ ማን ፡ ነው ፤ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ነው ።

24 ፤ አንተም ፦ በሠረገላዬ ፡ ብዛት ፡ ወደተራራዎች ፡ ከፍታ ፥ ወደሊባኖስ ፡ ጥግ ፡ ላይ ፡ ወጥቻለኹ ፤ ረጃጅሞቹንም ፡
ዝግባዎች ፡ የተመረጡትንም ፡ ጥዶች ፡ እቈርጣለኹ ፥ ወደከፍታውም ፡ ዳርቻ ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ዱር ፡ እገባለኹ ።

25 ፤ ቈፈርኹም ፡ ውሃም ፡ ጠጣኹ ፡ የግብጽንም ፡ ወንዞች ፡ ኹሉ ፡ በእግሬ ፡ ጫማ ፡ አደርቃለኹ ፡ ብለኽ ፡
በባሪያዎችኽ ፡ እጅ ፡ በጌታ ፡ ላይ ፡ ተገዳደርኽ ።

26 ፤ እኔ ፡ ጥንቱን ፡ እንደ ፡ ሠራኹት ፥ ቀድሞውንም ፡ እንዳደረግኹት ፡ አልሰማኽምን ፤ አኹንም ፡ የተመሸጉትን ፡
ከተማዎች ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ እስኪኾኑ ፡ ድረስ ፡ እንድታፈርስ ፡ አደረግኹኽ ።

27 ፤ ስለዚህ ፥ የሚኖሩባቸው ፡ ሰዎች ፡ እጃቸው ፡ ዝሏል ፥ ደንግጠውም ፡ ታውከዋል ፤ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ሣር ፥ እንደ ፡ ለመለመም ፡ ቡቃያ ፥ በሰገነትም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሣር ፥ ሳይሸት ፡ ዋግ ፡ እንደ ፡ መታው ፡ እኽል ፡
ኾነዋል ።

28 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ መቀመጫኽንና ፡ መውጫኽን ፡ መግቢያኽንም ፡ በእኔም ፡ ላይ ፡ የተቈጣኸውን ፡ ቍጣ ፡
ዐውቄያለኹ ።

29 ፤ ቍጣኽና ፡ ትዕቢትኽ ፡ ወደ ፡ ጆሮዬ ፡ ደርሷልና ፥ ስለዚህ ፡ ስናጋዬን ፡ በአፍንጫኽ ፡ ልጓሜንም ፡ በከንፈርኽ ፡
አደርጋለኹ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ እመልስኻለኹ ።

30 ፤ ይህም ፡ ምልክት ፡ ይኾንኻል ፤ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የገቦውን ፥ በኹለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ከገቦው ፡ የበቀለውን ፡
ትበላላችኹ ፤ በሦስተኛውም ፡ ዓመት ፡ ትዘራላችኹ ፡ ታጭዱማላችኹ ፥ ወይንም ፡ ትተክላላችኹ ፡ ፍሬውንም ፡
ትበላላችኹ ።

31 ፤ ያመለጠው ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ ሥሩን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይሰዳል ፥ ወደ ፡ ላይም ፡ ያፈራል ።

32 ፤ ከኢየሩሳሌም ፡ ቅሬታ ፡ ከጽዮንም ፡ ተራራ ፡ ያመለጡት ፡ ይወጣሉና ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅንአት ፡
ይህን ፡ ያደርጋል ።

33 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደዚች ፡ ከተማ ፡ አይመጣም ፥ ፍላጻንም ፡
አይወረውርባትም ፥ በጋሻም ፡ አይመጣባትም ፥ የዐፈርንም ፡ ድልድል ፡ አይደለድልባትም ።

34 ፤ በመጣበት ፡ መንገድ ፡ በዚያው ፡ ይመለሳል ፥ ወደዚችም ፡ ከተማ ፡ አይመጣም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

35 ፤ ስለ ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ባሪያዬም ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ አድናት ፡ ዘንድ ፡ እጋርዳታለኹ ።

36 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ወጣ ፥ ከአሶራውያንም ፡ ሰፈር ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ፤ ማለዳም ፡
በተነሡ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ኹሉ ፡ በድኖች ፡ ነበሩ ።

37 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ተነሥቶ ፡ ኼደ ፥ ተመልሶም ፡ በነነዌ ፡ ተቀመጠ ።

38 ፤ በአምላኩም ፡ በናሳራክ ፡ ቤት ፡ ሲሰግድ ፡ ልጆቹ ፡ አድራሜሌክና ፡ ሳራሳር ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ፤ ወደአራራትም ፡
አገር ፡ ኰበለሉ ። ልጁም ፡ አስራዶን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

____________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 38 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሕዝቅያስ ፡ ለሞት ፡ እስኪደርስ ፡ ታመመ ። ነቢዩም ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡
መጥቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፡ በሕይወት ፡ አትኖርምና ፡ ቤትኽን ፡ አስተካክል ፡



www.ethiopianorthodox.org

አለው ።

2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ግድግዳው ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፦

3 ፤ አቤቱ ፥ በፊትኽ ፡ በእውነትና ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ኼድኹ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝኽንም ፡ እንዳደረግኹ ፡ ታስብ ፡
ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ። ሕዝቅያስም ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ ።

4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

5 ፤ ኺድ ፥ ሕዝቅያስን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የአባትኽ ፡ የዳዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ ጸሎትኽን ፡ ሰምቻለኹ ፥ እንባኽንም ፡ አይቻለኹ ፤ እንሆ ፥ በዕድሜኽ ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡
እጨምራለኹ ።

6 ፤ አንተንና ፡ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ እታደጋለኹ ፥ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ እጋርዳታለኹ ።

7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽመው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምልክቱ ፡ ይህ ፡ ይኾንልኻል ።

8 ፤ እንሆ ፥ በአካዝ ፡ የጥላ ፡ ስፍረ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ የወረደውን ፡ በደረጃዎች ፡ ያለውን ፡ ጥላ ፡ ዐሥር ፡
ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለስ ፡ አደርጋለኹ ። ፀሓይም ፡ በጥላ ፡ ስፍረ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ የወረደበት ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሰ ።

9 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ታሞ ፡ ከደዌው ፡ በተፈወሰ ፡ ጊዜ ፡ የጻፈው ፡ ጽሕፈት ፡ ይህ ፡ ነው ፦

10 ፤ እኔ ፦ በሕይወት ፡ ዘመኔ ፡ መካከል ፡ ወደሲኦል ፡ በሮች ፡ እገባለኹ ፤ የቀረው ፡ ዘመኔ ፡ ጐደለብኝ ፡ አልኹ ።

11 ፤ ደግሞም ፦ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላይም ፤ በዓለምም ፡ ከሚኖሩ ፡ ጋራ ፡ ሰውን ፡ እንግዲህ ፡
አልመለከትም ፡ አልኹ ።

12 ፤ ማደሪያዬ ፡ ተነቀለች ፥ እንደ ፡ እረኛ ፡ ድንኳንም ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ተወገደች ፤ ሕይወቴንም ፡ እንደ ፡ ሸማኔ ፡
ጠቀለልኹ ፥ ርሱም ፡ ከመጠቅለያው ፡ ይቈርጠኛል ፤ ከማለዳም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ታጠፋኛለኽ ።

13 ፤ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ቈይቼ ፡ ነበር ፤ ርሱ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ዐጥንቴን ፡ ኹሉ ፡ ሰበረ ፤ ከማለዳ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡
ድረስ ፡ ታጠፋኛለኽ ።

14 ፤ እንደ ፡ ጨረባና ፡ እንደ ፡ ሽመላ ፡ ተንጫጫኹ ፥ እንደ ፡ ርግብም ፡ አጕረመረምኹ ፤ ዐይኖቼ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ከማየት ፡ ደከሙ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ተጨንቄያለኹና ፡ መከታ ፡ ኹነኝ ።

15 ፤ ምን ፡ እላለኹ ፦ ርሱ ፡ ተናግሮኛል ፥ ርሱ ፡ ራሱም ፡ ይህን ፡ አድርጓል ፤ በዘመኔ ፡ ኹሉ ፡ ስለነፍሴ ፡ ምሬት ፡ ቀስ ፡
ብዬ ፡ እኼዳለኹ ።

16 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ነገር ፡ ሰዎች ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ፥ በዚህም ፡ ኹሉ ፡ የመንፈሴ ፡ ሕይወት ፡ ነው ፤ አንተም ፡
ፈወስኸኝ ፡ ወደ ፡ ሕይወትም ፡ መለስኸኝ ።

17 ፤ እንሆ ፥ ታላቅ ፡ ምሬት ፡ ለደኅንነቴ ፡ ኾነ ፤ አንተም ፡ ነፍሴን ፡ ከጥፋት ፡ ጕድጓድ ፡ አዳንኻት ፥ ኀጢአቴንም ፡
ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኋላኽ ፡ ጣልኽ ።

18 ፤ ሲኦል ፡ አያመሰግንኽምና ፥ ሞትም ፡ አያከብርኽምና ፤ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ የሚወርዱ ፡ እውነትኽን ፡ ተስፋ ፡
አያደርጉም ።

19 ፤ እኔ ፡ ዛሬ ፡ እንደማደርግ ፡ ሕያዋን ፡ እነርሱ ፡ ያመሰግኑኻል ፤ አባት ፡ ለልጆች ፡ እውነትኽን ፡ ያስታውቃል ።

20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያድነኛል ፤ ስለዚህ ፥ በዕድሜያችን ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ቅኔዎችን ፡ አውታር ፡
ባለው ፡ ዕቃ ፡ እንዘምራለን ።

21 ፤ ኢሳይያስም ፦ የበለስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ አምጥተው ፡ በዕባጩ ፡ ላይ ፡ ይለብጡት ፥ ርሱም ፡ ይፈወሳል ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

22 ፤ ሕዝቅያስም ፦ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እወጣ ፡ ዘንድ ፡ ምልክቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 39 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የባልዳን ፡ ልጅ ፡ መሮዳክ ፡ ባልዳን ፡ ሕዝቅያስ ፡ ታሞ ፡ እንደ ፡ ተፈወሰ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፥ ደብዳቤና ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ላከለት ።

2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ግምጃ ፡ ቤቱንም ፥ ብሩንና ፡ ወርቁንም ፥ ቅመሙንና ፡ የከበረውንም ፡ ዘይት ፥ መሣሪያም ፡ ያለበትን ፡ ቤት ፡ ሹሉ ፥ በቤተ ፡ መዛግብቱም ፡ የተገኘውን ፡ ሹሉ ፡ አሳያቸው ፤ በቤቱና ፡ በግዛቱ ፡ ሹሉ ፡ ካለው ፡ ሕዝቅያስ ፡ ያላሳያቸው ፡ የለም ።

3 ፤ ነቢዩም ፡ ኢሳይያስ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጥቶ ፦ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ አሉ ፧ ከወዴትስ ፡ መጡልኽ ፧ አለው ። ሕዝቅያስም ፦ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ከባቢሎን ፡ መጡልኝ ፡ አለው ።

4 ፤ ርሱም ፦ በቤትኽ ፡ ያዩት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ፤ ሕዝቅያስም ፦ በቤቴ ፡ ያለውን ፡ ሹሉ ፡ አይተዋል ፤ በቤተ ፡ መዛግብቴ ፡ ካለው ፡ ያላሳየኊቸው ፡ የለም ፡ አለው ።

5 ፤ ኢሳይያስም ፡ ሕዝቅያስን ፦ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ።

6 ፤ እንሆ ፥ በቤትኽ ፡ ያለው ፡ ሹሉ ፥ አባቶችኽም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያከማቹት ፡ ሹሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሚፈልሰበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፤ ምንም ፡ አይቀርም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

7 ፤ ከአንተም ፡ ከሚወጡት ፡ ከምትወልዳቸው ፡ ልጆችኽ ፡ ማርከው ፡ ይወስዳሉ ፤ በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ይኾናሉ ፡ አለው ።

8 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ኢሳይያስን ፦ የተናገርኸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መልካም ፡ ነው ፡ አለው ። ደግሞም ፦ በዘመኔ ፡ ሰላምና ፡ እውነት ፡ ይኹን ፡ አለ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ።

ምዕራፍ ፡ 40 ።

1 ፤ አጽናኑ ፥ ሕዝቤን ፡ አጽናኑ ፡ ይላል ፡ አምላካችኹ ።

2 ፤ ለኢየሩሳሌም ፡ ልብ ፡ ተናገሩ ፡ የተቀጠረችበት ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፥ ኀጢአቷም ፡ እንደ ፡ ተሰረየ ፥ ከእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ኀጢአቷ ፡ ሹሉ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ እንደ ፡ ተቀበለች ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ጮኹ ።

3 ፤ የዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ቃል ። የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ጥረጉ ፥ ለአምላካችንም ፡ ጐዳና ፡ በበረሓ ፡ አስተካክሉ ።

4 ፤ ሸለቆው ፡ ሹሉ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፥ ተራራውና ፡ ኰረብታውም ፡ ሹሉ ፡ ዝቅ ፡ ይላል ፤ ጠማማውም ፡ ይቃናል ፥ ስርጓጕጡም ፡ ሜዳ ፡ ይኾናል ፤

5 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ይገለጣል ፥ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ሹሉ ፡ በአንድነት ፡ ያየዋል ፥ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ተናግሯልና ።

6 ፤ ጩኽ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቃል ፤ ምን ፡ ብዬ ፡ ልጩኽ ፧ አልኹ ። ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ሹሉ ፡ ሣር ፡ ነው ፥ ክብሩም ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አበባ ፡ ነው ።

7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ይነፍስበታልና ፥ ሣሩ ፡ ይደርቃል ፡ አበባውም ፡ ይረግፋል ፤ በእውነት ፡ ሕዝቡ ፡ ሣር ፡ ነው ።

8 ፤ ሣሩ ፡ ይደርቃል ፡ አበባውም ፡ ይረግፋል ፥ የአምላካችን ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ።

9 ፤ የምሥራች ፡ የምትነግሪ ፡ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ ውጪ ፡ የምሥራች ፡ የምትነግሪ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ድምፅሽን ፡ በኀይል ፡ አንሺ ፤ አንሺ ፥ አትፍሪ ፤ ለይሁዳም ፡ ከተማዎች ፦ እንሆ ፥ አምላካችኹ! ብለሽ ፡ ንገሪ ።

10 ፤ እንሆ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኀያል ፡ ይመጣል ፡ ክንዱም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ይገዛል ፤ እንሆ ፥ ዋጋው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደመ ፡ ወዙም ፡ በፊቱ ፡ ነው ።

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ መንጋውን ፡ እንደ ፡ እረኛ ፡ ያሰማራል ፥ ጠቦቶቹን ፡ በክንዱ ፡ ሰብስቦ ፡ በብብቱ ፡ ይሸከማል ፥ የሚያጠቡትንም ፡
በቀስታ ፡ ይመራል ።

12 ፤ ውሃዎችን ፡ በዕፍኙ ፡ የሰፈረ ፥ ሰማይንም ፡ በስንዝር ፡ የለካ ፥ የምድርንም ፡ ዐፈር ፡ በመስፈሪያ ፡ ሰብስቦ ፡
የያዘ ፥ ተራራዎችን ፡ በሚዛን ፡ ኰረብታዎችንም ፡ በሚዛኖች ፡ የመዘነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

13 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንፈስ ፡ ያዘዘ ፥ ወይስ ፡ አማካሪ ፡ ኾኖ ፡ ያስተማረው ፡ ማን ፡ ነው ፧

14 ፤ ወይስ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ ተመካከረ ፧ ወይስ ፡ ማን ፡ መከረው ፧ የፍርድንም ፡ መንገድ ፡ ማን ፡
አስተማረው ፧ ዕውቀትንስ ፡ ማን ፡ አስተማረው ፧ የማስተዋልንስ ፡ መንገድ ፡ ማን ፡ አሳየው ፧

15 ፤ እንሆ ፥ አሕዛብ ፡ በገንቦ ፡ እንዳለች ፡ ጠብታ ፡ ናቸው ፥ በሚዛንም ፡ እንዳለ ፡ ትንሽ ፡ ትቢያ ፡
ተቈጥረዋል ፤ እንሆ ፥ ደሴቶችን ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ያነሣል ።

16 ፤ ሊባኖስ ፡ ለማንደጃ ፡ እንስሳዎቿም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አይበቁም ።

17 ፤ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ እንዳልነበሩ ፡ ናቸው ፤ ከምናምን ፡ እንደሚያንሱ ፥ እንደ ፡ ከንቱ ፡ ነገርም ፡ ይቈጥራቸዋል ።

18 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማን ፡ ትመስሉታላችኹ ፧ ወይስ ፡ በምን ፡ ምሳሌ ፡ ታስተያዩታላችኹ ፧

19 ፤ የተቀረጸውንስ ፡ ምስል ፡ ሠራተኛ ፡ ሠርቶታል ፥ አንጥረኛም ፡ በወርቅ ፡ ለብጦታል ፥ የብሩንም ፡ ሰንሰለት ፡
አፍሶለታል ።

20 ፤ ለዚህ ፡ መባዕ ፡ ገንዘቡ ፡ ያልበቃው ፡ ድኻ ፡ የማይነቅዘውን ፡ ዕንጨት ፡ ይመርጣል ፤ ምስሉም ፡ እንዳይናወጥ ፡
ያቆመው ፡ ዘንድ ፡ ብልኅ ፡ ሠራተኛን ፡ ይፈልጋል ።

21 ፤ አላወቃችኹምን ፧ ወይስ ፡ አልሰማችኹምን ፧ ከጥንትስ ፡ አልተወራላችኹምን ፧ ወይስ ፡ ምድር ፡ ከተመሠረተች ፡
ዠምሮ ፡ አላስተዋላችኹምን ፧

22 ፤ ርሱ ፡ በምድር ፡ ክበብ ፡ ላይ ፡ ይቀምጣል ፥ በርሷም ፡ የሚኖሩት ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ ናቸው ፤ ሰማያትን ፡ እንደ ፡
መጋረጃ ፡ የሚዘረጋቸው ፡ እንደ ፡ ድንኳንም ፡ ለመኖሪያ ፡ የሚዘረጋቸው ፥

23 ፤ አለቃዎችንም ፡ እንዳልነበሩ ፥ የምድርንም ፡ ፈራጆች ፡ እንደ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

24 ፤ ገና ፡ እንደ ፡ ተተከሉና ፡ እንደ ፡ ተዘሩ ፥ በምድርም ፡ ሥር ፡ ገና ፡ እንደ ፡ ሰደዱ ፡ ወዲያውኑ ፡
ነፈሰባቸው ፥ እነርሱም ፡ ደረቁ ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ እንደ ፡ እብቅ ፡ ጠረጋቸው ።

25 ፤ እንግዲህ ፡ እተካከለው ፡ ዘንድ ፡ በማን ፡ መሰላችኹኝ ፧ ይላል ፡ ቅዱሱ ።

26 ፤ ዐይናችኹን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንሥታችኹ ፡ ተመልከቱ ፤ እነዚህን ፡ የፈጠረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ሰራዊታቸውን ፡ በቍጥር ፡
የሚያወጣ ፡ ርሱ ፡ ነው ፥ ኹሉንም ፡ በየስማቸው ፡ ይጠራቸዋል ፤ በኀይሉ ፡ ብዛትና ፡ በችሎቱ ፡ ብርታት ፡ አንድስ ፡
እንኳ ፡ አይታጣውም ።

27 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ እስራኤልም ፡ ሆይ ፦ መንገዴ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተሰውራለች ፡ ፍርዴም ፡ ከአምላኬ ፡ ዐልፋለች ፡
ለምን ፡ ትላለኽ ፧ ለምንስ ፡ እንዲህ ፡ ትናገራለኽ ፧

28 ፤ አላወቅኽምን ፧ አልሰማኽምን ፧ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ አምላክ ፥ የምድርም ፡ ዳርቻ ፡ ፈጣሪ ፡
ነው ፤ አይደክምም ፥ አይታክትም ፥ ማስተዋሉም ፡ አይመረመርም ።

29 ፤ ለደካማ ፡ ኀይልን ፡ ይሰጣል ፥ ጕልበት ፡ ለሌለውም ፡ ብርታትን ፡ ይጨምራል ።

30 ፤ ብላቴናዎች ፡ ይደክማሉ ፡ ይታክቱማል ፥ ጕበዛዝቱም ፡ ፈጽሞ ፡ ይወድቃሉ ፤

31 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በመተማመን ፡ የሚጠባበቁ ፡ ግን ፡ ኀይላቸውን ፡ ያድሳሉ ፤ እንደ ፡ ንስር ፡ በክንፍ ፡
ይወጣሉ ፤ ይሮጣሉ ፥ አይታክቱም ፤ ይኼዳሉ ፥ አይደክሙም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ።

ምዕራፍ ፡ 41 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ ደሴቶች ፡ ሆይ ፥ በፊቴ ፡ ዝም ፡ በሉ ፤ አሕዛብም ፡ ኀይላቸውን ፡ ያድሱ ፤ ይቅረቡም ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡
ይናገሩ ፤ ለፍርድ ፡ ለአንድነት ፡ እንቅረብ ።

2 ፤ ከምሥራቅ ፡ አንዱን ፡ ያስነሣ ፡ በጽድቅም ፡ ወደ ፡ እግሩ ፡ የተጠራው ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሕዛብንም ፡ አሳልፎ ፡ በፊቱ ፡
ሰጠው ፥ ነገሥታትንም ፡ አስገዛለት ፤ ለሰይፉ ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፡ ለቀስቱም ፡ እንደ ፡ ተጠረገ ፡ እብቅ ፡ አድርጎ ፡ ሰጣቸው ።

3 ፤ አሳደዳቸው ፥ እግሮቹም ፡ አስቀድመው ፡ ባልኼዱባት ፡ መንገድ ፡ በደኅንነት ፡ ዐለፈ ።

4 ፤ ይህን ፡ የሠራና ፡ ያደረገ ፥ ትውልድንም ፡ ከጥንት ፡ የጠራ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፥ ፊተኛው ፡
በኋለኛዎችም ፡ ዘንድ ፡ የምኖር ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

5 ፤ ደሴቶች ፡ አይተው ፡ ፈሩ ፥ የምድርም ፡ ዳርቻዎች ፡ ተንቀጠቀጡ ፤ ቀረቡም ፡ ደረሱም ።

6 ፤ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ ባልንጀራውን ፡ ይረዳው ፡ ነበር ፥ ወንድሙንም ፦ አይዞኽ ፡ ይለው ፡ ነበር ።

7 ፤ ዐናጢውም ፡ አንጥረኛውን ፥ በመዶሻም ፡ የሚያሣሣውን ፡ መስፍ ፡ መችውን ፡ አጽናና ፥ ስለማጣበቅ ፡
ሥራውም ፦ መልካም ፡ ነው ፡ አለ ፤ እንዳይንቀሳቀስም ፡ በችንካር ፡ አጋጠመው ።

8 ፤ ባሪያዬ ፡ እስራኤል ፥ የመረጥኹኽ ፡ ያዕቆብ ፥ የወዳጄ ፡ የአብርሃም ፡ ዘር ፡ ሆይ ፥

9 ፤ አንተ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ የያዝኹኽ ፡ ከማእዘኗም ፡ የጠራኹኽና ፦ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ነኽ ፥ መርጬኻለኹ ፡
አልጥልኽም ፡ ያልኹኽ ፡ ሆይ ፥

10 ፤ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍራ ፤ እኔ ፡ አምላክኽ ፡ ነኝና ፡
አትደንግጥ ፤ አበረታኻለኹ ፥ እረዳኽማለኹ ፥ በጽድቄም ፡ ቀኝ ፡ ደግፌ ፡ እይዝኻለኹ ።

11 ፤ እንሆ ፥ የሚቈጡኽ ፡ ኹሉ ፡ ያፍራሉ ፥ ይዋረዱማል ፤ የሚከራከሩኽም ፡ እንዳልነበሩ ፡ ይኾናሉ ፥ ይጠፉማል ።

12 ፤ የሚያጣሉኽንም ፡ ትሻቸዋለኽ ፡ አታገኛቸውምም ፥ የሚዋጉኽም ፡ እንዳልነበሩና ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ ይኾናሉ ።

13 ፤ እኔ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፦ አትፍራ ፥ እረዳኻለኹ ፡ ብዬ ፡ ቀኝኽን ፡ እይዛለኹና ።

14 ፤ አንተ ፡ ትል ፡ ያዕቆብ ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ አትፍሩ ፤ እረዳኻለኹ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፥ የሚቤዥኽም ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

15 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ተሳለች ፡ እንደ ፡ ዐዲስ ፡ ባለጥርስ ፡ ማኼጃ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ ተራራዎችንም ፡ ታኼዳለኽ ፡
ታደቅቃቸውማለኽ ፥ ኰረብታዎችንም ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ታደርጋቸዋለኽ ።

16 ፤ ታበጥራቸዋለኽ ፥ ነፋስም ፡ ይጠርጋቸዋል ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ይበትናቸዋል ፤ አንተም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡
ይልኻል ፥ በእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ ትመካለኽ ።

17 ፤ ድኻዎችና ፡ ምስኪኖችም ፡ ውሃ ፡ ይሻሉ ፡ አያገኙምም ፥ ምላሳቸውም ፡ በጥማት ፡ ደርቋል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡
እሰማቸዋለኹ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ አልተዋቸውም ።

18 ፤ በወናዎቹ ፡ ኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ወንዞችን ፥ በሸለቆዎችም ፡ መካከል ፡ ምንጮችን ፡ እከፍታለኹ ፤ ምድረ ፡
በዳውን ፡ ለውሃ ፡ መቆሚያ ፥ የጥማትንም ፡ ምድር ፡ ለውሃ ፡ መፍለቂያ ፡ አደርጋለኹ ።

19 ፤ 20 ፤ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ ሠራች ፥ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ፈጠረው ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡
ያውቁም ፡ ዘንድ ፡ ያስቡም ፡ ዘንድ ፡ በአንድነትም ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዝግባውንና ፡ ግራሩን ፡
ባርሰነቱንና ፡ የዘይቱን ፡ ዛፍ ፡ አበቅላለኹ ፥ በበረሓውም ፡ ጥዱንና ፡ አስታውን ፡ ወይራውንም ፡ በአንድነት ፡ አኖራለኹ ።

21 ፤ ክርክራችኹን ፡ አቅርቡ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ማስረጃችኹን ፡ አምጡ ፥ ይላል ፡ የያዕቆብ ፡ ንጉሥ ።

22 ፤ ያምጡ ፥ የሚኾነውንም ፡ ይንገሩን ፤ ልብም ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ ፍጻሜያቸውንም ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፥ የቀደሙት ፡
ነገሮች ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ተናገሩ ፥ የሚመጡትንም ፡ አሳዩን ።

23 ፤ አማልክትም ፡ መኾናችኹን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ በኋላ ፡ የሚመጡትን ፡ ተናገሩ ፤ እንደነግጥም ፡ ዘንድ ፡
በአንድነትም ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ መልካሙን ፡ ወይም ፡ ክፉውን ፡ አድርጉ ።



www.ethiopianorthodox.org

24 ፤ እንሆ ፣ እንዳልነበረ ፡ ናችኹ ፣ ሥራችኹም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ የሚመርጣችኹም ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ።

25 ፤ አንዱን ፡ ከሰሜን ፡ አነሣኹ ፡ መጥቷልም ፤ አንዱም ፡ ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ስሜን ፡ የሚጠራ ፡ ይመጣል ፤ በጭቃ ፡
ላይ ፡ እንደሚመጣ ፡ ሰው ፡ ዐፈርም ፡ እንደሚረግጥ ፡ ሸክለኛ ፡ በአለቃዎች ፡ ላይ ፡ ይመጣል ።

26 ፤ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ከጥንት ፡ የተናገረው ፦ እውነት ፡ ነው ፡ እንልም ፡ ዘንድ ፡ ቀድሞ ፡ የተናገረው ፡ ማን ፡
ነው ፧ የሚናገር ፡ የለም ፣ የሚገልጥም ፡ የለም ፣ ቃላችኹንም ፡ የሚሰማ ፡ የለም ።

27 ፤ በመዠመሪያ ፡ ለጽዮን ፦ እንሂቸው ፡ እላለኹ ፤ ለኢየሩሳሌምም ፡ የምሥራች ፡ ነጋሪን ፡ እሰጣለኹ ።

28 ፤ ብመለከት ፡ ማንም ፡ አልነበረም ፤ ብጠይቃቸውም ፡ የሚመልስልኝ ፡ አማካሪ ፡ በመካከላቸው ፡ የለም ።

29 ፤ እንሆ ፣ እነርሱ ፡ ዅሉ ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸው ፣ ሥራቸውም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ናት ፤ ቀልጠው ፡ የተሠሩት ፡
ምስሎቻቸውም ፡ ነፋስና ፡ ኢምንት ፡ ናቸው ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፣ ምዕራፍ ፡ 42 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 42 ።

1 ፤ እንሆ ፣ ደግፌ ፡ የያዝኹት ፡ ባሪያዬ ፤ ነፍሴ ፡ ደስ ፡ የተሠኘችበት ፡ ምርጤ ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ መንፈሴን ፡
አድርጌያለኹ ፣ ርሱም ፡ ለአሕዛብ ፡ ፍርድን ፡ ያወጣል ።

2 ፤ አይጮኽም ፡ ቃሉንም ፡ አያነሣም ፣ ድምፁንም ፡ በሜዳ ፡ አያሰማም ።

3 ፤ የተቀጠቀጠን ፡ ሸምበቆ ፡ አይሰብርም ፣ የሚጤስንም ፡ ክር ፡ አያጠፋም ፤ በእውነት ፡ ፍርድን ፡ ያወጣል ።

4 ፤ በምድርም ፡ ፍርድን ፡ እስኪያደርግ ፡ ድረስ ፡ ይበራል ፡ እንጂ ፡ አይጠፋም ፤ አሕዛብም ፡ በስሙ ፡ ይታመናሉ ።

5 ፤ ሰማያትን ፡ የፈጠረ ፡ የዘረጋቸውም ፣ ምድርንና ፡ በውስጧ ፡ ያለውን ፡ ያጸና ፣ በርሷ ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡
እስትንፋስን ፣ ለሚኼዱባትም ፡ መንፈስን ፡ የሚሰጥ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

6 ፤ 7 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ ጠርቼኻለኹ ፣ እጅኽንም ፡ እይዛለኹ ፡ እጠብቅኽማለኹ ፣ የዕውሩንም ፡ ዐይን ፡
ትከፍት ፡ ዘንድ ፡ የተጋዘውንም ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ በጨለማም ፡ የተቀመጡትን ፡ ከወህኒ ፡ ቤት ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፡
ለሕዝብ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለአሕዛብም ፡ ብርሃን ፡ አድርጌ ፡ እሰጥኻለኹ ።

8 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ ስሜ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ክብሬን ፡ ለሌላ ፣ ምስጋናዬንም ፡ ለተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ አልሰጥም ።

9 ፤ እንሆ ፣ የቀድሞው ፡ ነገር ፡ ተፈጸመ ፣ ዐዲስ ፡ ነገርንም ፡ እናገራለኹ ፤ አስቀድሞም ፡ ሳይበቅል ፡ ርሱን ፡
አስታውቃችኋለኹ ።

10 ፤ ወደ ፡ ባሕር ፡ የምትወርዱ ፡ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ያላችኹ ፡ ዅሉ ፣ ደሴቶችና ፡ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የምትኖሩ ፡
ሆይ ፣ ለእግዚአብሔር ፡ ዐዲስ ፡ መዝሙር ፣ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ ምስጋናውን ፡ ዘምሩ ።

11 ፤ ምድረ ፡ በዳውና ፡ ከተማዎቹ ፡ የቄዳርም ፡ ሰዎች ፡ የሚቀመጡባቸው ፡ መንደሮች ፡ ድምፃቸውን ፡ ያንሡ ፤ በሴላ ፡
የሚኖሩ ፡ እልል ፡ ይበሉ ፣ በተራራዎችም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ ይጩኹ ።

12 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ክብርን ፡ ይስጡ ፣ ምስጋናውንም ፡ በደሴቶች ፡ ይናገሩ ።

13 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኀያል ፡ ይወጣል ፡ እንደ ፡ ሰልፈኛም ፡ ቅንአትን ፡ ያስነሣል ፤ ይጮኻል ፡ ድምፁንም ፡
ያሰማል ፡ በጠላቶቹም ፡ ላይ ፡ ይበረታል ።

14 ፤ ከድሮ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ዝም ፡ ብያለኹ ፣ ዝም ፡ ብዬም ፡ ታግሻለኹ ፤ አኹን ፡ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡
እጮኻለኹ ፤ አጠፋለኹ ፡ በአንድነትም ፡ እጨርሳለኹ ።

15 ፤ ተራራዎችንና ፡ ኰረብታዎችን ፡ አፈርሳለኹ ፣ ቡቃያዎቻቸውንም ፡ ዅሉ ፡ አደርቃለኹ ፤ ወንዞችንም ፡ ደሴቶች ፡
አደርጋለኹ ፣ ኵሬዎችንም ፡ አደርቃለኹ ።

16 ፤ ዕውሮችንም ፡ በማያውቋት ፡ መንገድ ፡ አመጣቸዋለኹ ፣ በማያውቋትም ፡ ጐዳና ፡ እመራቸዋለኹ ፤ በፊታቸውም ፡
ጨለማውን ፡ ብርሃን ፡ አደርጋለኹ ፣ ጠማማውንም ፡ አቀናለኹ ። ይህን ፡ አደርግላቸዋለኹ ፣ አልተዋቸውምም ።



www.ethiopianorthodox.org

17 ፤ በተቀረጹትም ፡ ምስሎች ፡ የሚታመኑ ፥ ቀልጠው ፡ የተሠሩትንም ፡ ምስሎች ፦ አምላኮቻችን ፡ ናችኹ ፡ የሚሉ ፡
ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ ፈጽመውም ፡ ያፍራሉ ።

18 ፤ እናንተ ፡ ደንቈሮዎች ፥ ስሙ ፤ እናንተም ፡ ዕውሮች ፥ ታዩ ፡ ዘንድ ፡ ተመልከቱ ።

19 ፤ ከባሪያዬ ፡ በቀር ፡ ዕውር ፡ ማን ፡ ነው ፧ እንደምልከው ፡ መልእክተኛዬስ ፡ በቀር ፡ ደንቈሮ ፡ የኾነ ፡ ማን ፡
ነው ፧ እንደ ፡ ፍጹሙ ፡ ወይስ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ዕውር ፡ የኾነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

20 ፤ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ታያላችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትጠባበቁትም ፤ ዦሯችኹም ፡ ተከፍተዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትሰሙም ።

21 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ጽድቁ ፡ ሕጉን ፡ ታላቅ ፡ ያደርግና ፡ ያከብር ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ።

22 ፤ ይህ ፡ ግን ፡ የተበዘበዘና ፡ የተዘረፈ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፤ ዅላቸው ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ተጠምደዋል ፡ በግዞት ፡ ቤትም ፡
ተሸሽገዋል ፤ ብዝበዛ ፡ ኾነዋል ፡ የሚያድንም ፡ የለም ፥ ምርኮም ፡ ኾነዋል ፥ ማንም ፦ መልሱ ፡ አይልም ።

23 ፤ ከመካከላችኹ ፡ ይህን ፡ የሚያደምጥ ፥ ለሚመጣውም ፡ ጊዜ ፡ የሚያደምጥና ፡ የሚሰማ ፡ ማን ፡ ነው ፧

24 ፤ ያዕቆብን ፡ ለማረኩ ፡ እስራኤልንም ፡ ለበዘበዙ ፡ ሰዎች ፡ የሰጠ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እኛ ፡ የበደልነው ፥ እነርሱም ፡
በመንገዱ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ያልወደዱት ፡ ለሕጉም ፡ ያልታዘዙለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አይደለምን ፧

25 ፤ ስለዚህ ፥ የቍጣውን ፡ መዓትና ፡ የሰልፉን ፡ ጽናት ፡ አፈሰሰበት ፤ በዙሪያም ፡ አነደደው ፥ ርሱ ፡ ግን ፡
አላወቀም ፥ አቃጠለውም ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ ልብ ፡ አላደረገም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 43 ።

ምዕራፍ ፡ 43 ።

1 ፤ አኹንም ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ የፈጠረኽ ፥ እስራኤልም ፡ ሆይ ፥ የሠራኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ ተቤዠቼኻለኹና ፡ አትፍራ ፤ በስምኽም ፡ ጠርቼኻለኹ ፥ አንተ ፡ የእኔ ፡ ነኽ ።

2 ፤ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ ባለፍኽ ፡ ጊዜ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፥ በወንዞችም ፡ ውስጥ ፡ ባለፍኽ ፡ ጊዜ ፡
አያሰጥሙኽም ፤ በእሳትም ፡ ውስጥ ፡ በኼድኽ ፡ ጊዜ ፡ አትቃጠልም ፥ ነበልባሉም ፡ አይፈጅኽም ።

3 ፤ እኔ ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኀኒትኽ ፡ ነኝ ፤ ግብጽን ፡ ለአንተ ፡ ቤዛ ፡
አድርጌ ፥ ኢትዮጵያንና ፡ ሳባንም ፡ ለአንተ ፡ ፋንታ ፡ ሰጥቻለኹ ።

4 ፤ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ የከበርኽና ፡ የተመሰገንኽ ፡ ነኽና ፥ እኔም ፡ ወድጄኻለኹና ፡ ስለዚህ ፡ ሰዎችን ፡ ለአንተ ፡ አሕዛብንም ፡
ለነፍስኽ ፡ እሰጣለኹ ።

5 ፤ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍራ ፤ ዘርኽንም ፡ ከምሥራቅ ፡ አመጣዋለኹ ፥ ከምዕራብም ፡ እሰበስብኻለኹ ።

6 ፤ 7 ፤ ሰሜንን ፦ መልሰኽ ፡ አምጣ ፥ ደቡብንም ፦ አትከልክል ፤ ወንዶች ፡ ልጆቼን ፡ ከሩቅ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቼንም ፡
ከምድር ፡ ዳርቻ ፥ በስሜ ፡ የተጠራውን ፡ ለክብሬም ፡ የፈጠርኹትን ፥ የሠራኹትንና ፡ ያደረግኹትን ፡ ዅሉ ፡ አምጣ ፡
እላለኹ ።

8 ፤ ዐይኖች ፡ ያሏቸውን ፡ ዕውሮችን ፡ ሕዝብ ፥ ዦሮዎችም ፡ ያሏቸውን ፡ ደንቈሮዎቹን ፡ አውጣ ።

9 ፤ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ በአንድነት ፡ ይሰብሰቡ ፡ ወገኖችም ፡ ይከማቹ ፤ ከመካከላቸው ፤ ይህን ፡ የሚናገር ፥ የቀድሞውንስ ፡
ነገር ፡ የሚያሳየን ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይጸድቁ ፡ ዘንድ ፡ ምስክሮቻቸውን ፡ ያምጡ ፥ ሰምተውም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይበሉ ።

10 ፤ ታውቁና ፡ ታምኑብኝ ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ እንደኾንኹ ፡ ታስተውሉ ፡ ዘንድ ፥ እናንተ ፡ የመረጥኹትም ፡ ባሪያዬ ፡
ምስክሮቼ ፡ ናችኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከእኔ ፡ በፊት ፡ አምላክ ፡ አልተሠራም ፡ ከእኔም ፡ በኋላ ፡ አይኾንም ።

11 ፤ እኔ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፥ ከእኔ ፡ ሌላም ፡ የሚያድን ፡ የለም ።

12 ፤ ተናግሬያለኹ ፡ አድኜማለኹ ፡ አሳይቼማለኹ ፥ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ባዕድ ፡ አምላክ ፡
አልነበረም ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ ምስክሮቼ ፡ ናችኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ።

13 ፤ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ከእጄም ፡ የሚያመልጥ ፡ የለም ፤ እሠራለኹ ፥ የሚከለክልስ ፡ ማን ፡ ነው ፧



www.ethiopianorthodox.org

14 ፤ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፣ የሚቤዣችኹ ፣ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለ ፡ እናንተ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡
ሰድጃለኹ ፣ ከለዳውያንንም ፡ ኹሉ ፡ ስደተኛዎች ፡ አድርጌ ፡ በሚመኩባቸው ፡ መርከቦች ፡ አዋርዳቸዋለኹ ።

15 ፤ ቅዱሳችኹ ፣ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፣ ንጉሣችኹ ፣ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

16 ፤ እግዚአብሔር ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ መንገድን ፡ በኀይለኛም ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ መተላለፊያን ፡ ያደርጋል ፤

17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሠረገላውንና ፡ ፈረሱን ፡ ሰራዊቱንና ፡ ዐርበኛውን ፡ ያወጣል ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ በአንድነት ፡
ተኝተዋል ፣ አይነሡም ፤ ቀርተዋል ፣ እንደ ፡ ጧፍ ፡ ኵስታሪም ፡ ጠፍተዋል ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

18 ፤ የፊተኛውን ፡ ነገር ፡ አታስተውሉ ፣ የጥንቱንም ፡ ነገር ፡ አታስቡ ።

19 ፤ እንሆ ፣ ዐዲስ ፡ ነገርን ፡ አደርጋለኹ ፤ ርሱም ፡ አኹን ፡ ይበቅላል ፣ እናንተም ፡ አታውቁትምን ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡
መንገድን ፣ በበረሓም ፡ ወንዞችን ፡ አደርጋለኹ ።

20 ፤ 21 ፤ ምስጋናዬን ፡ እንዲናገሩ ፡ ለእኔ ፡ የፈጠርኹት ፡ ሕዝብ ፣ የመረጥኹትን ፡ ሕዝቤን ፡ አጠጣ ፡
ዘንድ ፣ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውሃን ፡ በበረሓም ፡ ወንዞችን ፡ ሰጥቻለኹና ፣ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፣ ቀበሮዎችና ፡
ሰጐኖች ፣ ያከብሩኛል ።

22 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፣ አንተ ፡ ግን ፡ አልጠራኸኝም ፣ አንተም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፣ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ደክመኻል ።

23 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በጎችኽን ፡ አላቀረብኽልኝም ፡ በሌላም ፡ መሥዋዕትኽ ፡ አላከበርኸኝም ፤ በእኽልም ፡
ቍርባን ፡ አላስቸገርኹኽም ፡ በዕጣንም ፡ አላደከምኹኽም ።

24 ፤ ዕጣንም ፡ በገንዘብ ፡ አልገዛኽልኝም ፡ በመሥዋዕትኽም ፡ ስብ ፡ አላጠገብኸኝም ፤ ነገር ፡ ግን ፣ በኀጢአትኽ ፡
አስቸገርኸኝ ፣ በበደልኽም ፡ አደከምኸኝ ።

25 ፤ መተላለፍኽን ፦ ስለ ፡ እኔ ፡ ስል ፡ የምደመስስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ኀጢአትኽንም ፡ አላስብም ።

26 ፤ አሳስበኝ ፣ በአንድነትም ፡ ኾነን ፡ እንፋረድ ፤ እንድትጸድቅ ፡ ነገርኽን ፡ ተናገር ።

27 ፤ ፊተኛው ፡ አባትኽ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቷል ፣ መምህሮችኽም ፡ በድለውኛል ።

28 ፤ ስለዚህ ፣ የመቅደሱን ፡ አለቃዎች ፡ አረከስኹ ፣ ያዕቆብንም ፡ ርግማን ፣ እስራኤልንም ፡ ስድብ ፡ አደረግኹ ።

________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፣ ምዕራፍ ፡ 44 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 44 ።

1 ፤ አኹንም ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ የመረጥኹኽም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፣ ስማ ።

2 ፤ የፈጠረኽ ፡ ከማሕፀንም ፡ የሠራኽ ፡ የሚረዳኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡
የመረጥኹኽም ፡ ይሹሩን ፡ ሆይ ፣ አትፍራ ።

3 ፤ በተጠማ ፡ ላይ ፡ ውሃን ፡ በደረቅም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ፈሳሾችን ፡ አፈሳለኹና ፤ መንፈሴን ፡ በዘርኽ ፡ ላይ ፡ በረከቴንም ፡
በልጆችኽ ፡ ላይ ፡ አፈሳለኹ ፣

4 ፤ በፈሳሾችም ፡ አጠገብ ፡ እንደሚበቅሉ ፡ እንደ ፡ አሓያ ፡ ዛፎች ፡ በሣር ፡ መካከል ፡ ይበቅላሉ ።

5 ፤ ይህ ፦ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ይላል ፣ ያም ፡ በያዕቆብ ፡ ስም ፡ ይጠራል ፤ ይህም ፦ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ነኝ ፡ ብሎ ፡ በእጁ ፡ ይጽፋል ፣ በእስራኤልም ፡ የቍልምጫ ፡ ስም ፡ ይጠራል ።

6 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብሔር ፣ የሚቤዠም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡
ፊተኛ ፡ ነኝ ፣ እኔም ፡ ኋለኛ ፡ ነኝ ፤ ከእኔ ፡ ሌላም ፡ አምላክ ፡ የለም ።

7 ፤ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፥ ይነሣና ፡ ይጥራ ፡ ይናገርም ፤ ከጥንት ፡ የፈጠርኹትን ፡ ሕዝብ ፡
ያዘጋጅልኝ ፣ የሚመጣውም ፡ ነገር ፡ ሳይደርስ ፡ ይንገሩኝ ።

8 ፤ አትፍሩ ፡ አትደንግጡም ፤ ከጥንቱ ፡ ዠምሬ ፡ አልነገርኋችኹምን ፥ ወይስ ፡ አላሳየኋችኹምን ፥ እናንተ ፡ ምስክሮቼ ፡
ናችኹ ። ከእኔ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አለን ፥ ዐምባ ፡ የለም ፤ ማንንም ፡ አላውቅም ።



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ የሚሠሩ ፡ ዅሉ ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸው ፥ የወደዱትም ፡ ነገር ፡
አይረባቸውም ፤ ምስክሮቻቸውም ፡ አያዩምና ፡ አያውቁም ፤ ስለዚህ ፥ ያፍራሉ ።

10 ፤ አምላክን ፡ የሠራ ፡ ወይስ ፡ ለምንም ፡ የማይረባ ፡ ምስልን ፡ የቀረጸ ፡ ማን ፡ ነው ፧

11 ፤ እንሆ ፥ ባልንጀራዎቹ ፡ ዅሉ ፡ ያፍራሉ ፥ ሠራተኛዎቹም ፡ ከሰዎች ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ዅላቸው ፡ ተሰብስበው ፡
ይቁሙ ፤ ይፈራሉ ፡ በአንድነትም ፡ ያፍራሉ ።

12 ፤ ብረት ፡ ሠሪ ፡ መጥረቢያውን ፡ ይሠራል ፥ በፍምም ፡ ውስጥ ፡ ያደርገዋል ፥ በመዶሻም ፡ መቶ ፡ ቅርጽ ፡
ይሰጠዋል ፥ በክንዱም ፡ ኀይል ፡ ይሠራዋል ፥ ርሱም ፡ ይራባል ፡ ይደክምማል ፥ ውሃም ፡ አይጠጣም ፡ ይታክትማል ።

13 ፤ ጠራቢውም ፡ ገመድ ፡ ይዘረጋል ፡ በበረቅም ፡ ያመለክተዋል ፡ በመቅረጫም ፡ ይቀርጸዋል ፡ በመለኪያም ፡
ይለካዋል ፤ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ በሰው ፡ አምሳልና ፡ በሰው ፡ ውበት ፡ ያስመስለዋል ።

14 ፤ የዝግባን ፡ ዛፎች ፡ ይቈርጣል ፤ የዞጲንና ፡ የኮምቦልን ፡ ዛፍ ፡ ይመርጣል ፥ ከዱር ፡ ዛፎችም ፡ መካከል ፡ ይጠነክር ፡
ዘንድ ፡ ይተወዋል ፤ የጥድንም ፡ ዛፍ ፡ ይተክላል ፡ ዝናብም ፡ ያበቅለዋል ።

15 ፤ ለሰውም ፡ ማገዶ ፡ ይኾናል ፤ ከርሱም ፡ ወስዶ ፡ ይሞቃል ፥ አንድዶም ፡ እንጀራ ፡ ይጋግርበታል ፤ ከርሱም ፡ አምላክ ፡
አበጅቶ ፡ ይሰግድለታል ፥ የተቀረጸውንም ፡ ምስል ፡ ሠርቶ ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ይንበረከካል ።

16 ፤ ግማሹን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላል ፥ በዚያ ፡ በግማሹ ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ፥ ሥጋም ፡ ይጠብስበትና ፡
ይጠግባል ፤ ይሞቃልና ፦ ዕሠይ ፡ ሞቅ ኹ ፥ እሳቱን ፡ አይቻለ ኹ ፡ ይላል ።

17 ፤ የቀረውንም ፡ ዕንጨት ፡ አምላክ ፡ አድርጎ ፡ ምስል ፡ ይቀርጽበታል ፤ በፊቱም ፡ ተጐንብሶ ፡ ይሰግዳል ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡
እየጸለየ ፦ አምላኬ ፡ ነኽና ፥ አድነኝ ፡ ይላል ።

18 ፤ አያውቁም ፥ አያስቡም ፤ እንዳያዩ ፡ ዐይኖቻቸውን ፥ እንዳያስተውሉ ፡ ልቦቻቸውን ፡ ጨፍኖዋል ።

19 ፤ በልቡም ፡ ማንም ፡ አያስብም ፦ ግማሿን ፡ በእሳት ፡ አቃጥያለ ኹ ፥ በፍሟም ፡ ላይ ፡ እንጀራን ፡
ጋግሬያለ ኹ ፥ ሥጋም ፡ ጠብሼ ፡ በልቻለ ኹ ፤ የቀረውንም ፡ አስጸያፊ ፡ ነገር ፡ አደርጋለ ኹን ፧ ለዛፍስ ፡ ግንድ ፡
እሰግዳለ ኹን ፧ እንዲልም ፡ ዕውቀትና ፡ ማስተዋል ፡ የለውም ።

20 ፤ ዐመድ ፡ ይበላል ፥ የተታለለ ፡ ልብ ፡ አስቶታል ፥ ነፍሱን ፡ ለማዳን ፡ አይችልም ፥ ወይም ፦ በቀኜ ፡ እጄ ፡ ሐሰት ፡
አለ ፡ አይልም ።

21 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ አንተም ፡ እስራኤል ፥ ባሪያዬ ፡ ነኽና ፥ ይህን ፡ ዐስብ ፤ እኔ ፡ ሠርቼኻለ ኹ ፡ አንተም ፡ ባሪያዬ ፡
ነኽ ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ያልተረሳ ፡ ትኾናለኽ ።

22 ፤ መተላለፍኽን ፡ እንደ ፡ ደመና ፥ ኀጢአትኽንም ፡ እንደ ፡ ጭጋግ ፡ ደምስሻለ ኹ ፤ ተቤዥቼኻለ ኹና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
ተመለስ ።

23 ፤ ሰማያት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ አድርጎታልና ፥ ዘምሩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዕቆብን ፡ ተቤዥቷልና ፥ በእስራኤልም ፡
ዘንድ ፡ ይከበራልና ፥ አንተ ፡ የምድር ፡ ጥልቅ ፡ ሆይ ፥ ጩኽ ፤ እናንተም ፡ ተራራዎች ፡ አንተም ፡ ዱር ፡ ባንተም ፡ ያለ ፡
ዛፍ ፡ ዅሉ ፥ እልል ፡ በሉ ።

24 ፤ ከማሕፀን ፡ የሠራኽ ፥ የሚቤዥኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዅሉን ፡ የፈጠርኹ ፥ ሰማያትን ፡ ለብቻዬ ፡
የዘረጋኹ ፡ ምድርንም ፡ ያጸናኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ማን ፡ ነበረ ፧

25 ፤ የሐሰተኛዎችን ፡ ምልክት ፡ ከንቱ ፡ አደርጋለ ኹ ፥ ሟርተኛዎችንም ፡ አሳብዳለ ኹ ፥ ጥበበኛዎቹንም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡
እመልሳለ ኹ ፡ ዕውቀታቸውንም ፡ ስንፍና ፡ አደርጋለ ኹ ፤

26 ፤ የባሪያዬን ፡ ቃል ፡ አጸናለ ኹ ፥ የመልእክተኛዎቼንም ፡ ምክር ፡ እፈጽማለ ኹ ፤ ኢየሩሳሌምን ፦ የሰው ፡ መኖሪያ ፡
ትኾኛለሽ ፥ የይሁዳንም ፡ ከተማዎች ። ትታነጻላችኹ ፡ ፍራሾቻችኹንም ፡ አቆማለ ኹ ፡ እላለ ኹ ፤

27 ፤ ቀላዩንም ፦ ደረቅ ፡ ኹን ፥ ፈሳሾችኽንም ፡ አደርቃለ ኹ ፡ እላለ ኹ ፤

28 ፤ ቂሮስንም ፦ ርሱ ፡ እረኛዬ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ኢየሩሳሌምን ፦ ትታነጺያለሽ ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ ይመሠረታል ፡



www.ethiopianorthodox.org

ብሎ ፡ ፈቃዴን ፡ ኹሉ ፡ ይፈጽማል ፡ እላለኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 45 ።

ምዕራፍ ፡ 45 ።

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለቀባኹት ፥ አሕዛብንም ፡ በፊቱ ፡ አስገዛ ፡ ዘንድ ፡ የነገሥታትንም ፡ ወገብ ፡ እፈታ ፡
ዘንድ ፥ በሮቹም ፡ እንዳይዘጉ ፡ መዝጊያዎቹን ፡ በፊቱ ፡ እከፍት ፡ ዘንድ ፥ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ለያዝኹት ፡ ለቂሮስ ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦

2 ፤ በፊትኽ ፡ እኼዳለኹ ፡ ተራራዎችንም ፡ ትክክል ፡ አደርጋለኹ ፥ የናሱንም ፡ ደጆች ፡ እሰብራለኹ ፡ የብረቱንም ፡
መወርወሪያዎች ፡ እቈርጣለኹ ፤

3 ፤ በስምኽም ፡ የምጠራኽ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ በጨለማ ፡
የነበረችውን ፡ መዝገብ ፡ በስውርም ፡ የተደበቀችውን ፡ ሀብት ፡ እሰጥኻለኹ ።

4 ፤ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ያዕቆብ ፥ ስለ ፡ መረጥኹትም ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ብዬ ፡ በስምኽ ፡ ጠርቼኻለኹ ፤ በቍልምጫ ፡
ስምኽ ፡ ጠራኹኽ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አላወቅኸኝም ።

5 ፤ 6 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ ሌላ ፡ ማንም ፡ የለም ፤ ከእኔም ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ በፀሓይ ፡
መውጫና ፡ በምዕራብ ፡ ያሉ ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሌላ ፡ እንደሌለ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ አስታጠቅኹኽ ፥ አንተ ፡ ግን ፡
አላወቅኸኝም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፥ ከእኔም ፡ ሌላ ፡ ማንም ፡ የለም ።

7 ፤ ብርሃንን ፡ ሠራኹ ፥ ጨለማውንም ፡ ፈጠርኹ ፤ ደኅንነትን ፡ እሠራለኹ ፥ ክፋትንም ፡ እፈጥራለኹ ፤ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡
ያደረግኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

8 ፤ እናንተ ፡ ሰማያት ፡ ከላይ ፡ አንጠባጥቡ ፥ ደመናትም ፡ ጽድቅን ፡ ያዝንቡ ፤ ምድርም ፡ ትከፈት ፥ መድኀኒትንም ፡
ታብቅል ፥ ጽድቅም ፡ በአንድነት ፡ ይብቀል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጥሬዋለኹ ።

9 ፤ ከሠሪው ፡ ጋራ ፡ ለሚታገል ፡ ወዮለት! በምድር ፡ ሸክላዎች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ሸክላ ፡ ነው ። ጭቃ ፡
ሠሪውን ፦ ምን ፡ ትሠራለኽ ፧ ወይስ ፡ ሥራኽ ፦ እጅ ፡ የለውም ፡ ይላልን ፧

10 ፤ አባትን ፦ ምን ፡ ወልደኻል ፧ ወይም ፡ ሴትን ፦ ምን ፡ አማጥሽ ፧ ለሚል ፡ ወዮ!

11 ፤ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ሠሪውም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሚመጣው ፡ ነገር ፡ ጠይቁኝ ፥ ስለ ፡
ልጆቼና ፡ ስለእጄ ፡ ሥራም ፡ እዘዙኝ ።

12 ፤ እኔ ፡ ምድርን ፡ ሠርቻለኹ ፡ ሰውንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ፈጥሬያለኹ ፤ እኔ ፡ በእጄ ፡ ሰማያትን ፡
ዘርግቻለኹ ፥ ሰራዊታቸውንም ፡ ኹሉ ፡ አዝዣለኹ ።

13 ፤ እኔ ፡ በጽድቅ ፡ አስነሥቼዋለኹ ፥ መንገዱንም ፡ ኹሉ ፡ አቀናለኹ ፤ ርሱ ፡ ከተማዬን ፡ ይሠራል ፥ በዋጋም ፡ ወይም ፡
በደመ ፡ ወዝ ፡ ሳይኾን ፡ ምርኮኛዎቼን ፡ ያወጣል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የግብጽ ፡ ድካምና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ቁመተ ፡ ረዥሞችም ፡ የሳባ ፡
ሰዎች ፡ ወዳንተ ፡ ያልፋሉ ፤ ለአንተም ፡ ይኾናሉ ፡ እጆቻቸውም ፡ ታስረው ፡ ይከተሉኻል ፤ በፊትኽም ፡
ያልፋሉ ፥ ለአንተም ፡ እየሰገዱ ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንተ ፡ አለ ፥ ከርሱም ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፡ ብለው ፡
ይለምኑኻል ።

15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ መድኀኒት ፡ ሆይ ፥ በእውነት ፡ አንተ ፡ ራስኽን ፡ የምትሰውር ፡ አምላክ ፡ ነኽ ።

16 ፤ ኹሉም ፡ ያፍራሉ ፡ ይዋረዱማል ፥ ጣዖታትንም ፡ የሚሠሩ ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ ውርደት ፡ ይኼዳሉ ።

17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እስራኤልን ፡ በዘላለማዊ ፡ መድኀኒት ፡ ያድነዋል ፥ እናንተም ፡ ለዘለዓለም ፡ አታፍሩምና ፡
አትዋረዱም ።

18 ፤ ሰማያትን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፥ ርሱም ፡ ምድርን ፡ የሠራና ፡ ያደረገ ፡ ያጸናትም ፥ መኖሪያም ፡ ልትኾን ፡
እንጂ ፡ ለከንቱ ፡ እንድትኾን ፡ ያልፈጠራት ፡ አምላክ ፥ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሌላ ፡ የለም ።

19 ፤ በስውር ፡ ወይም ፡ በጨለማ ፡ ምድር ፡ ስፍራ ፡ አልተናገርኹም ፤ ለያዕቆብ ፡ ዘር ፡— በከንቱ ፡ ፈልጉኝ ፡
አላልኹም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽድቅን ፡ እናገራለኹ ፡ ቅንንም ፡ አወራለኹ ።

20 ፤ እናንተ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ኰናችኹ ፡ ያመለጣችኹ ፥ ተሰብስባችኹ ፡ ኑ ፡ በአንድነትም ፡ ቅረቡ ፤ የተቀረጸውን ፡
የምስላቸውን ፡ ዕንጨት ፡ የሚሸከሙና ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ወደማይችል ፡ አምላክ ፡ የሚጸልዩ ፡ ዕውቀት ፡ የላቸውም ።

21 ፤ ይናገሩ ፡ ይቅረቡም ፡ በአንድነትም ፡ ይማከሩ ፤ ከጥንቱ ፡ ይህን ፡ ያሳየ ፡ ከቀድሞስ ፡ የተናገረ ፡ ማን ፡
ነው ፡ ያሳየኹም ፡ የተናገርኹም ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይደለኹምን ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ እኔ ፡
ጻድቅ ፡ አምላክና ፡ መድኀኒት ፡ ነኝ ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የለም ።

22 ፤ እናንተ ፡ የምድር ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፥ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለምና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ዘወር ፡ በሉ ፡
ትድኑማላችኹ ።

23 ፤ ቃሌ ፡ ከአፌ ፡ በጽድቅ ፡ ወጥታለች ፥ አትመለስም ። ጕልበት ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ ይንበረከካል ፥ ምላስም ፡ ኹሉ ፡ በእኔ ፡
ይምላል ፡ ብዬ ፡ በራሴ ፡ ምያለኹ ።

24 ፤ ስለ ፡ እኔም ፡— በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ጽድቅና ፡ ኀይል ፡ አለ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ሰዎች ፡
ይመጣሉ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተቈጡ ፡ ኹሉ ፡ ያፍራሉ ።

25 ፤ የእስራኤልም ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይጸድቃሉ ፥ ይመካሉም ፡ ይባላል ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 46 ።

ምዕራፍ ፡ 46 ።

1 ፤ ቤል ፡ ተዋረደ ፥ ናባው ፡ ተሰባበረ ፤ ጣዖቶቻቸው ፡ በእንስሳና ፡ በከብት ፡ ላይ ፡ ተጭነዋል ፤ ሸክሞቻችኹ ፡ ለደካማ ፡
እንስሳ ፡ ከባድ ፡ ጭነት ፡ ኾነዋል ።

2 ፤ ተጐነበሱ ፡ በአንድነትም ፡ ተዋረዱ ፤ ሸክሙን ፡ ለማዳን ፡ አልቻሉም ፥ ራሳቸው ፡ ግን ፡ ተማረኩ ።

3 ፤ እናንተ ፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ ከሆድ ፡ ያነሣኋችኹ ፡ ከማሕፀንም ፡
የተሸከምኋችኹ ፥ ስሙኝ ።

4 ፤ እስከ ፡ ሽምግልና ፡ ድረስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ እስከ ፡ ሽበትም ፡ ድረስ ፡ እሸከማችኋለኹ ፤ እኔ ፡ ሠርቻለኹ ፡ እኔም ፡
አነሣለኹ ፤ እኔ ፡ እሸከማለኹ ፡ እኔም ፡ አድናለኹ ።

5 ፤ በማን ፡ ትመስሉኛላችኹ ፡ ከማንስ ፡ ጋራ ፡ ታስተካክሉኛላችኹ ፡ እንመሳሰል ፡ ዘንድ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡
ታስተያዩኛላችኹ ፡

6 ፤ ወርቁን ፡ ከኰረጆ ፡ የሚያፈሱ ፥ ብሩንም ፡ በሚዛን ፡ የሚመዝኑ ፡ እነርሱ ፡ አንጥረኛውን ፡ ይቀጥራሉ ፥ ርሱም ፡
አምላክ ፡ አድርጎ ፡ ይሠራ ፡ ዋል ፤ ለዚያም ፡ ይጐነበሱለታል ፥ ይሰግዱለትማል ።

7 ፤ በጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ አንሥተው ፡ ይሸከሙታል ፡ በስፍራውም ፡ ያደርጉታል ፥ በዚያም ፡ ይቆማል ፥ ከስፍራውም ፡
ፈቀቅ ፡ አይልም ፤ ሰውም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቢጮኽ ፡ አይሰማውም ፡ ከመከራውም ፡ አያድነውም ።

8 ፤ ይህን ፡ ዐስቡና ፡ አልቅሱ ፤ ተላላፊዎች ፡ ሆይ ፥ ንስሓ ፡ ግቡ ፥ ልባችኹንም ፡ መልሱ ።

9 ፤ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ፥ ሌላም ፡ የለምና ፡ የቀድሞውን ፡ የጥንቱን ፡ ነገር ፡ ዐስቡ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ እንደ ፡
እኔም ፡ ያለ ፡ ማንም ፡ የለም ።

10 ፤ በመዠመሪያ ፡ መጨረሻውን ፥ ከጥንትም ፡ ያልተደረገውን ፡ እነግራለኹ ፤ ምክሬ ፡ ትጸናለች ፡ ፈቃዴንም ፡ ኹሉ ፡
እፈጽማለኹ ፡ እላለኹ ።

11 ፤ ከምሥራቅ ፡ ነጣቂ ፡ ወፍን ፥ ከሩቅም ፡ አገር ፡ ምክሬን ፡ የሚያደርገውን ፡ ሰው ፡
እጠራዋለኹ ። ተናግሬያለኹ ፤ እፈጽማለኹ ፤ ዐስቤያለኹ ፡ አደርግማለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

12 ፤ እናንተ ፡ ከጽድቅ ፡ የራቃችኹ ፡ እልከኛዎች ፥ ስሙኝ ፤

13 ፤ ጽድቄን ፡ አቀርባለኹ ፥ አይርቅም ፡ መድኀኒቴም ፡ አይዘገይም ፤ ከጽዮን ፡ ለክብር ፡ እንዲኾን ፡ መድኀኒትን ፡
ለእስራኤል ፡ ሰጥቻለኹ ።

___________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 47 ። ___________________

ምዕራፍ ፡ 47 ።

1 ፤ አንቺ ፡ ድንግል ፡ የባቢሎን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ውረጂ ፡ በትቢያም ፡ ላይ ፡ ተቀመጪ ፤ የከለዳውያን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
ሆይ ፥ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅልጣናምና ፡ ቅምጥል ፡ አትባይምና ፥ ያለዙፋን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተቀመጪ ።

2 ፤ ወፍጮ ፡ ወስደሽ ፡ ዱቄትን ፡ ፍጪ ፤ መሸፈኛሽን ፡ አውጪ ፡ ረዥሙንም ፡ ልብስሽን ፡ አውልቀሽ ፡
ጣዪው ፤ ባትሽን ፡ ግለጪ ፥ ወንዙን ፡ ተሻገሪ ።

3 ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋሽ ፡ ይገለጣል ፡ ዕፍረትሽም ፡ ይታያል ፤ እኔ ፡ እበቀላለኹ ፥ ለማንም ፡ አልራራም ።

4 ፤ ታዳጊያችን ፥ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

5 ፤ የከለዳውያን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ከዚህ ፡ በኋላ ፦ የመንግሥታት ፡ እመቤት ፡ አትባይምና ፥ ዝም ፡ ብለሽ ፡
ተቀመጪ ፥ ወደ ፡ ጨለማም ፡ ውስጥ ፡ ግቢ ።

6 ፤ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ተቈጥቼ ፡ ነበር ፡ ርስቴንም ፡ አረከስኹ ፡ በእጅሽም ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኋቸው ፤ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡
ምሕረት ፡ አላደረግሽም ፥ በሽማግሌዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ቀንበርሽን ፡ እጅግ ፡ አክብደሻል ።

7 ፤ አንቺም ፦ እኔ ፡ ለዘለዓለም ፡ እመቤት ፡ እኾናለኹ ፡ ብለሻል ፤ ይህንም ፡ በልብሽ ፡ አላደረግሽም ፡ ፍጻሜውንም ፡
አላሰብሽም ።

8 ፤ አኹንም ፡ አንቺ ፡ ቅምጥል ፡ ተዘልለሽ ፡ የምትቀመጪ ፥ በልብሽም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡
የለም ፤ መበለትም ፡ ኾኜ ፡ አልኖርም ፡ የወላድ ፡ መካንነትንም ፡ አላውቅም ፡ የምትዪ ፡ ይህን ፡ ስሚ ፤

9 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፥ የወላድ ፡ መካንነትና ፡ መበለትነት ፥ በድንገት ፡
ይመጡብሻል ፤ ስለ ፡ መተቶችሽ ፡ ብዛትና ፡ ስለ ፡ አስማቶችሽ ፡ ጽናት ፡ ፈጽመው ፡ ይመጡብሻል ።

10 ፤ በክፋትሽ ፡ ታምነሻል ፤ የሚያየኝ ፡ የለም ፡ ብለሻል ፤ ጥበብሽና ፡ ዕውቀትሽ ፡ አታለውሻል ፥ በልብሽም ፦ እኔ ፡
ነኝ ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ብለሻል ።

11 ፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይመጣብሻል ፥ በሟርትሽም ፡ እንዴት ፡ እንደምታርቂው ፡ አታውቂም ፤ ጕዳት ፡
ይወድቅብሻል ፥ ታስወግጂውም ፡ ዘንድ ፡ አይቻልሽም ፤ የማታውቂያትም ፡ ጕስቍልና ፡ ድንገት ፡ ትመጣብሻለች ።

12 ፤ ምናልባትም ፡ መጠቀም ፡ ትችዪ ፡ ወይም ፡ ታስደነግጪ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከአስማቶችሽና ፡ ከሕፃንነትሽ ፡ ዠምረሽ ፡
ከደከምሽበት ፡ ከመተቶችሽ ፡ ብዛት ፡ ጋራ ፡ ቁሚ ።

13 ፤ በምክርሽ ፡ ብዛት ፡ ደክመሻል ፤ አኹንም ፡ የሰማይን ፡ ከዋክብት ፡ የሚቈጥሩ ፥ ከዋክብትንም ፡
የሚመለከቱ ፥ በየመባቻውም ፡ የሚመጣውን ፡ ነገር ፡ የሚናገሩ ፡ ተነሥተው ፡ ከሚመጣብሽ ፡ ነገር ፡ ያድኑሽ ።

14 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ እብቅ ፡ ይኾናሉ ፥ እሳትም ፡ ያቃጥላቸዋል ፡ ሰውነታቸውንም ፡ ከነበልባል ፡ ኀይል ፡
አያድኑም ፤ ርሱም ፡ ሰው ፡ እንደሚሞቀው ፡ ፍም ፥ ወይም ፡ በፊቱ ፡ ሰው ፡ እንደሚቀመጥበት ፡ እሳት ፡ ያለ ፡ አይደለም ።

15 ፤ የደከምሽባቸው ፡ ነገሮች ፡ እንዲህ ፡ ይኾኑብሻል ፤ ከሕፃንነትሽ ፡ ዠምረው ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ይነግዱ ፡ የነበሩ ፡
እያንዳንዳቸው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ይኼዳሉ ፥ የሚያድንሽም ፡ የለም ።

___________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 48 ። ___________________

ምዕራፍ ፡ 48 ።

1 ፤ እናንተ ፡ በእስራኤል ፡ ስም ፡ የተጠራችኹ ፡ ከይሁዳም ፡ ውሃዎች ፡ የወጣችኹ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡
የምትምሉ ፥ በእውነት ፡ ሳይኾን ፡ በጽድቅም ፡ ሳይኾን ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ የምትጠሩ ፥



www.ethiopianorthodox.org

2 ፤ በቅድስት ፡ ከተማ ፡ ስም ፡ የተጠራችኹ ፥ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚባል ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የምትደገፉ ፥ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ስሙ ።

3 ፤ የቀድሞውን ፡ ነገር ፡ ከጥንት ፡ ተናግሬያለኹ ፥ ከአፌም ፡ ወጥቷል ፡ አሳይቼውማለኹ ፤ ድንገት ፡ አድርጌዋለኹ ፡ ተፈጽሞማል ።

4 ፤ አንተ ፡ እልከኛ ፥ ዐንገትኽም ፡ የብረት ፡ ዥማት ፥ ግንባርኽም ፡ ናስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቄያለኹ ፤

5 ፤ ስለዚህ ፥ አንተ ፦ ጣዖቴ ፡ ይህን ፡ አድርጓል ፥ የተቀረጸው ፡ ምስሌና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራው ፡ ምስሌ ፡ ይህን ፡ አዘዙኝ ፡ እንዳትል ፥ አስቀድሜ ፡ ነግሬኽ ፡ ነበር ፡ ሳይኾንም ፡ አሳይቼኽ ፡ ነበር ።

6 ፤ ሰምተኻል ፤ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ተመልከት ፤ እናንተም ፡ የምትናገሩት ፡ አይደላችኹምን ፧ የተሰወሩትን ፡ ያላወቅኻቸውንም ፡ ዐዲሶች ፡ ነገሮችን ፡ ከዚህ ፡ ዠምሬ ፡ አሳይቼኻለኹ ።

7 ፤ እነርሱም ፡ አኹን ፡ እንጂ ፡ ከጥንት ፡ አልተፈጠሩም ፤ አንተም ፦ እንሆ ፥ ዐውቄያቸዋለኹ ፡ እንዳትል ፡ ከዛሬ ፡ በፊት ፡ አልሰማኻቸውም ።

8 ፤ አልሰማኽም ፥ አላወቅኽም ፥ ዦሮኽ ፡ ከጥንት ፡ አልተከፈተችም ፤ አንተ ፡ ፈጽሞ ፡ ወንጀለኛ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ከማሕፀንም ፡ ዠምረኽ ፡ ተላላፊ ፡ ተብለኽ ፡ አንደ ፡ ተጠራኽ ፡ ዐውቄያለኹና ።

9 ፤ ስለ ፡ ስሜ ፡ ቍጣዬን ፡ አዘገያለኹ ፥ እንዳላጠፋኽም ፡ ስለ ፡ ምስጋናዬ ፡ እታገሣለኹ ።

10 ፤ እንሆ ፥ አንጥሬኻለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ብር ፡ አይደለም ፤ በመከራም ፡ እቶን ፡ ፈትኜኻለኹ ።

11 ፤ ስለ ፡ እኔ ፥ ስለ ፡ ራሴ ፡ አደርገዋለኹ ፡ ስሜ ፡ ተነቅፏልና ፤ ክብሬንም ፡ ለሌላ ፡ አልሰጥም ።

12 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ የጠራኹኽም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስማኝ ፤ እኔ ፡ ነኝ ፤ እኔ ፡ ፊተኛው ፡ ነኝ ፡ እኔም ፡ ኋለኛው ፡ ነኝ ።

13 ፤ እጄም ፡ ምድርን ፡ መሠርታለች ፡ ቀኜም ፡ ሰማያትን ፡ ዘርግታለች ፤ በጠራኋቸው ፡ ጊዜ ፡ በአንድነት ፡ ይቆማሉ ።

14 ፤ እናንተ ፡ ኹሉ ፥ በአንድነት ፡ ተሰብስባችኹ ፡ ስሙ ፤ ከነርሱ ፡ ይህን ፡ የተናገረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እግዚአብሔር ፡ የወደደው ፡ ፈቃዱን ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ፥ ክንዱም ፡ በከለዳውያን ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

15 ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ ተናግሬያለኹ ፤ እኔ ፡ ጠርቼዋለኹ ፤ አምጥቼዋለኹ ፥ መንገዱም ፡ ትከናወንለታለች ።

16 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ቅረቡ ፡ ይህንም ፡ ስሙ ፤ እኔ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሬ ፡ በስውር ፡ አልተናገርኹም ፤ ከኾነበት ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እኔ ፡ በዚያ ፡ ነበርኹ ፥ አኹንም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርና ፡ መንፈሱ ፡ ልከውኛል ።

17 ፤ ታዳጊኽ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ የሚረባኽን ፡ ነገር ፡ የማስተምርኽ ፡ በምትኼድባትም ፡ መንገድ ፡ የምመራኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

18 ፤ ትእዛዜን ፡ ብትሰማ ፡ ኖሮ ፥ ሰላምኽ ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ ጽድቅኽም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ሞገድ ፡ በኾነ ፡ ነበር ፤

19 ፤ ዘርኽም ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ የሆድኽም ፡ ትውልድ ፡ እንደምድር ፡ ትቢያ ፡ በኾነ ፡ ነበር ፥ ስሙም ፡ ከፊቴ ፡ ባልጠፋና ፡ ባልፈረሰ ፡ ነበር ።

20 ፤ ከባቢሎን ፡ ውጡ ፡ ከከለዳውያንም ፡ ኰብልሉ ፤ በእልልታ ፡ ድምፅ ፡ ተናገሩ ፡ ይህንም ፡ ንገሩ ፡ እስከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ አውሩና ፦ እግዚአብሔር ፡ ባሪያውን ፡ ያዕቆብን ፡ ታድጎታል ፡ በሉ ።

21 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ በኩል ፡ በመራቸው ፡ ጊዜ ፡ አልተጠሙም ፤ ውሃንም ፡ ከአለቱ ፡ ውስጥ ፡ አፈለቀላቸው ፥ አለቱንም ፡ ሰነጠቀ ፡ ውሃውም ፡ ፈሰሰ ።

22 ፤ ለክፉዎች ፡ ሰላም ፡ የላቸውም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 49 ።

ምዕራፍ ፡ 49 ።

1 ፤ ደሴቶች ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፥ እናንተም ፡ በሩቅ ፡ ያላችኹ ፡ አሕዛብ ፥ አድምጡ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከማሕፀን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ጠርቶኛል ፥ ከእናቴም ፡ ሆድ ፡ ዠምሮ ፡ ስሜን ፡ አንሥቷል ፤

2 ፤ አፌንም ፡ እንደ ፡ ተሳለ ፡ ሰይፍ ፡ አድርጓል ፥ በእጁ ፡ ጥላ ፡ ሰውሮኛል ፤ እንደ ፡ ተሳለ ፡ ፍላጻም ፡
አድርጎኛል ፥ በሰገባውም ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጎኛል ።

3 ፤ ርሱም ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ነኽ ፡ ባንተም ፡ እከበራለኹ ፡ አለኝ ።

4 ፤ እኔ ፡ ግን ፦ በከንቱ ፡ ደከምኹ ፥ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ለሌለውና ፡ ለከንቱ ፡ ጕልበቴን ፡ ፈጀኹ ፤ ፍርዴ ፡ ግን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፥ ዋጋዬም ፡ በአምላኬ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

5 ፤ አኹንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ ክብሬያለኹና ፥ አምላኬም ፡ ጕልበት ፡ ኾኖኛልና ፥ ያዕቆብን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡
እንድመልስ ፡ እስራኤልንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ እንድሰበስብ ፡ ባሪያ ፡ እኾነው ፡ ዘንድ ፡ ከማሕፀን ፡ ዠምሮ ፡ የሠራኝ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

6 ፤ ርሱም ፦ የያዕቆብን ፡ ነገዶች ፡ እንድታስነሣ ፡ ከእስራኤልም ፡ የዳኑትን ፡ እንድትመስል ፡ ባሪያዬ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡
እጅግ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነውና ፥ እስከምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ መድኀኒት ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ለአሕዛብ ፡ ብርሃን ፡ አድርጌ ፡
ሰጥቼኻለኹ ፡ ይላል ።

7 ፤ የእስራኤል ፡ ታዳጊ ፡ ቅዱሱም ፥ እግዚአብሔር ፥ ሰዎች ፡ ለሚንቁት ፡ ሕዝብም ፡ ለሚጠላው ፡ ለገዢዎች ፡ ባሪያ ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለ ፡ ታማኙ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፥ ስለ ፡ መረጠኽም ፡ ስለእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ነገሥታት ፡ አይተው ፡
ይነሣሉ ፥ መሳፍንትም ፡ አይተው ፡ ይሰግዳሉ ።

8 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በተወደደ ፡ ጊዜ ፡ ሰምቼኻለኹ ፥ በመድኀኒትም ፡ ቀን ፡
ረድቼኻለኹ ፤ እጠብቅኽማለኹ ፥ ምድርንም ፡ ታቀና ፡ ዘንድ ፥ ውድማ ፡ የኾኑትንም ፡ ርስቶች ፡ ታወርስ ፡ ዘንድ ፥

9 ፤ የተጋዙትንም ፦ ውጡ ፥ በጨለማም ፡ የተቀመጡትን ፦ ተገለጡ ፡ ትል ፡ ዘንድ ፥ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጌ ፡ ለሕዝቡ ፡
ሰጥቼኻለኹ ። በመንገድም ፡ ላይ ፡ ይሰማራሉ ፥ ማሰማሪያቸውም ፡ በወና ፡ ኰረብታ ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

10 ፤ የሚራራላቸውም ፡ ይመራቸዋልና ፥ በውሃም ፡ ምንጮች ፡ በኩል ፡
ይነዳቸዋልና ፥ አይራቡም ፥ አይጠሙም ፥ ትኵሳት ፡ ወይም ፡ ፀሓይ ፡ አይጐዳቸውም ።

11 ፤ ተራራዎቼንም ፡ ዅሉ ፡ መንገድ ፡ አደርጋለኹ ፥ ጐዳናዎቼም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ።

12 ፤ እንሆ ፥ እነዚህ ፡ ከሩቅ ፥ እንሆም ፥ እነዚህ ፡ ከሰሜንና ፡ ከምዕራብ ፥ እነዚህም ፡ ከሲኒም ፡ አገር ፡ ይመጣሉ ።

13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ አጽናንቷልና ፥ ለችግረኛዎቹም ፡ ራርቷልና ፥ ሰማያት ፡ ሆይ ፥ ዘምሩ ፥ ምድር ፡
ሆይ ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ ተራራዎችም ፡ ሆይ ፥ እልል ፡ በሉ ።

14 ፤ ጽዮን ፡ ግን ፦ እግዚአብሔር ፡ ትቶኛል ፡ ጌታም ፡ ረስቶኛል ፡ አለች ።

15 ፤ በእውኑ ፡ ሴት ፡ ከማሕፀኗ ፡ ለተወለደው ፡ ልጅ ፡ እስከማትራራ ፡ ድረስ ፡ ሕፃኗን ፡ ትረሳ ፡ ዘንድ ፡
ትችላለችን ፧ አዎን ፥ ርሷ ፡ ትረሳ ፡ ይኾናል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አልረሳሽም ።

16 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ በእጄ ፡ መዳፍ ፡ ቀርጬሻለኹ ፥ ቅጥሮችሽም ፡ ዅልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አሉ ።

17 ፤ ልጆችሽ ፡ ይፈጥናሉ ፤ ያፈረሱሽና ፡ ያወደሙሽ ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ ይወጣሉ ።

18 ፤ ዐይንሽን ፡ አንሥተሽ ፡ በዙሪያሽ ፡ ተመልከቺ ፤ እነዚህ ፡ ዅሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ። እኔ ፡
ሕያው ፡ ነኝና ፡ እነዚህን ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ ጌጥ ፡ ትለብሻቸዋለሽ ፥ እንደ ፡ ሙሽራም ፡ ትጐናጸፊአቸዋለሽ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

19 ፤ ባድማሽና ፡ ውድማሽ ፡ ወናም ፡ የኾነው ፡ ምድርሽ ፡ ከሚኖሩብሽ ፡ የተነሣ ፡ ዛሬ ፡ ጠባብ ፡
ትኾናለችና ፥ የዋጡሽም ፡ ይርቃሉና ።

20 ፤ የወላድ ፡ መካን ፡ ከኾንሽ ፡ በኋላ ፡ የተወለዱልሽ ፡ ልጆችሽ ፡ በዦሮሽ ፦ ስፍራ ፡ ጠቦኛልና ፥ እቀመጥ ፡ ዘንድ ፡
ቦታ ፡ አስፊልኝ ፡ ይላሉ ።

21 ፤ አንቺም ፡ በልብሽ ፥ የወላድ ፡ መካን ፡ ኾኛለኹና ፥ እኔም ፡ ብቻዬን ፡ ተሰድጃለኹና ፡ ተቅበዝብዤለኹምና ፡



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን ፡ ማን ፡ ወለደልኝ ፡፡ እነዚህንስ ፡ ማን ፡ አሳደጋቸው ፡፡ እነሆ ፥ ብቻዬን ፡ ቀርቼ ፡ ነበር ፤ እነዚህስ ፡ ወዴት ፡ ነበሩ ፡፡ ትያለሽ ።

22 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ እጄን ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ አነሣለኹ ፥ ዓላማዬንም ፡ ወደ ፡ ወገኖች ፡ አቆማለኹ ፤ ወንዶች ፡ ልጆችሽንም ፡ በብብታቸው ፡ ያመጧቸዋል ፥ ሴቶች ፡ ልጆችሽንም ፡ በጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ ይሸከሟቸዋል ።

23 ፤ ነገሥታትም ፡ አሳዳጊ ፡ አባቶችሽ ፡ ይኾናሉ ፥ እቴጌዎቻቸውም ፡ ሞግዚቶችሽ ፡ ይኾናሉ ፤ ግንባራቸውንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ ይሰግዱልሻል ፥ የእግርሽንም ፡ ትቢያ ፡ ይልሳሉ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቂያለሽ ፥ እኔንም ፡ በመተማመን ፡ የሚጠባበቁ ፡ አያፍሩም ።

24 ፤ በእውኑ ፡ ብዝበዛ ፡ ከኀያል ፡ እጅ ፡ ይወሰዳልን ፡፡ ወይስ ፡ የጨካኙ ፡ ምርኮኛዎች ፡ ያመልጣሉን ፡፡

25 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በኀያላን ፡ የተማረኩ ፡ ይወሰዳሉ ፥ የጨካኞችም ፡ ብዝበዛ ፡ ያመልጣል ፤ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ የሚጣሉትን ፡ እጣላቸዋለኹ ፥ ልጆችሽንም ፡ አድናለኹ ።

26 ፤ አስጨናቂዎችሽንም ፡ ሥጋቸውን ፡ አስበላቸዋለኹ ፥ እንደ ፡ ጣፋጭም ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ደማቸውን ፡ ጠጥተው ፡ ይሰክራሉ ፤ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ዅሉ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኀኒትሽና ፡ ታዳጊሽ ፥ የያዕቆብ ፡ ኀያል ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 50 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 50 ።

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናታችኹን ፡ የፈታኹበት ፡ የፍቿ ፡ ጽሕፈት ፡ የት ፡ አለ ፡፡ ወይስ ፡ እናንተን ፡ የሸጥኹ ፡ ከአበዳሪዎች ፡ ለየትኛው ፡ ነው ፡፡ እነሆ ፥ ስለ ፡ ኀጢአታችኹ ፡ ተሸጣችኋል ፥ ስለ ፡ በደላችኹም ፡ እናታችኹ ፡ ተፈታለች ።

2 ፤ በመጣኹስ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልነበረም ፡፡ በጠራኹስ ፡ ጊዜ ፡ የሚመልስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልነበረም ፡፡ መታደግ ፡ እንዳትችል ፡ እጄ ፡ ዐጪር ፡ ኾናለችን ፡፡ ወይስ ፡ ለማዳን ፡ ኀይል ፡ የለኝምን ፡፡ እነሆ ፥ በገሥጽኹ ፡ ጊዜ ፡ ባሕርን ፡ አደርቃለኹ ፥ ወንዞችንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አደርጋቸዋለኹ ፤ ውሃም ፡ በማጣት ፡ ዓሣዎቻቸው ፡ ይገማሉ ፡ በጥማትም ፡ ይሞታሉ ።

3 ፤ ሰማያትን ፡ ጥቍረት ፡ አለብሳቸዋለኹ ፥ መጋረጃቸውንም ፡ ማቅ ፡ አደርጋለኹ ።

4 ፤ የደከመውን ፡ በቃል ፡ እንዴት ፡ እንደምደግፍ ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተማሩትን ፡ ምላስ ፡ ሰጥቶኛል ፡ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ያነቃኛል ፥ እንደ ፡ ተማሪዎችም ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ዦሮዬን ፡ ያነቃቃል ።

5 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዦሮዬን ፡ ከፍቷል ፥ እኔም ፡ ዐመፀኛ ፡ አልነበርኹም ፡ ወደ ፡ ኋላዬም ፡ አልተመለስኹም ።

6 ፤ ዠርባዬን ፡ ለገራፊዎች ፡ ጕንጨንም ፡ ለጠጕር ፡ ነጪዎች ፡ ሰጠኹ ፥ ፊቴንም ፡ ከውርደትና ፡ ከትፋት ፡ አልመለስኹም ።

7 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛልና ፥ ስለዚህ ፡ አልታወክኹም ፤ ስለዚህም ፡ ፊቴን ፡ እንደ ፡ ባልጩት ፡ ድንጋይ ፡ አድርጌዋለኹ ፥ እንዳላፍርም ፡ ዐውቃለኹ ።

8 ፤ የሚያጸድቀኝ ፡ ቅርብ ፡ ነው ፤ ከእኔስ ፡ ጋራ ፡ የሚከራከር ፡ ማን ፡ ነው ፡፡ በአንድነት ፡ እንቁም ፤ የሚከራከረኝ ፡ ማን ፡ ነው ፡፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይቅረብ ።

9 ፤ እነሆ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፤ ማን ፡ ይፈርድብኛል ፡፡ እነሆ ፥ ዅሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃሉ ፡ ብልም ፡ ይበላቸዋል ።

10 ፤ ከእናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፥ የባሪያውንም ፡ ቃል ፡ የሚሰማ ፥ በጨለማም ፡ የሚኼድ ፥ ብርሃንም ፡ የሌለው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሚታመን ፥ በአምላኩም ፡ የሚደገፍ ፡ ማን ፡ ነው ፡፡

11 ፤ እነሆ ፥ እሳት ፡ የምታነዱ ፡ የእሳትንም ፡ ወላፈን ፡ የምትታጠቁ ፡ ዅላችኹ ፥ በእሳታችኹ ፡ ነበልባል ፡



www.ethiopianorthodox.org

ባነደዳችኹትም ፡ ወላፈን ፡ ኺዱ ፤ ይህ ፡ ከእጄ ፡ ይኾንባችኋል ፤ በሐዘን ፡ ትተኛላችኹ ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 51 ።

ምዕራፍ ፡ 51 ።

1 ፤ እናንተ ፡ ጽድቅን ፡ የምትከተሉ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የምትሹ ፥ ስሙኝ ፤ ከርሱ ፡ የተቈረጣችኹበትን ፡ ድንጋይ ፡
ከርሱም ፡ የተቈፈራችኹበትን ፡ ጕድጓድ ፡ ተመልከቱ ።

2 ፤ ወደ ፡ አባታችኹ ፡ ወደ ፡ አብርሃም ፥ ወደ ፡ ወለደቻችኹም ፡ ወደ ፡ ሳራ ፡ ተመልከቱ ፤ አንድ ፡ ብቻውን ፡ በኾነ ፡
ጊዜ ፡ ጠራኹት ፥ ባረክኹትም ፥ አበዛኹትም ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጽዮንን ፡ ያጽናናል ፤ በርሷም ፡ ባድማ ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ያጽናናል ፥ ምድረ ፡ በዳዋንም ፡ እንደ ፡
ዔዴን ፡ በረሓዋንም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ ያደርጋል ፤ ደስታና ፡ ተድላ ፡ ምስጋናና ፡ የዝማሬ ፡ ድምፅ ፡
ይገኝበታል ።

4 ፤ ወገኔ ፡ ሆይ ፥ አድምጠኝ ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ስማኝ ፤ ሕግ ፡ ከእኔ ፡ ይወጣልና ፥ ፍርዴም ፡ ለአሕዛብ ፡ ብርሃን ፡
ይኾናልና ።

5 ፤ ጽድቄ ፡ ፈጥኖ ፡ ቀርቧል ፥ ማዳኔም ፡ ወጥቷል ፥ ክንዴም ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ይፈርዳል ፤ ደሴቶች ፡ እኔን ፡
በመተማመን ፡ ይጠባበቃሉ ፥ በክንዴም ፡ ይታመናሉ ።

6 ፤ ዐይናችኹን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንሡ ፥ ወደ ፡ ታችም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተመልከቱ ፤ ሰማያት ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ በንው ፡
ይጠፋሉ ፥ ምድርም ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ታረጃለች ፥ የሚኖሩባትም ፡ እንዲሁ ፡ ይሞታሉ ፤ ማዳኔ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡
ይኾናል ፥ ጽድቄም ፡ አይፈርስም ።

7 ፤ ጽድቅን ፡ የምታውቁ ፡ ሕጌም ፡ በልባችኹ ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ የሰውን ፡ ተግዳሮት ፡
አትፍሩ ፥ በስድባቸውም ፡ አትደንግጡ ።

8 ፤ እንደ ፡ ልብስም ፡ ብል ፡ ይበላቸዋል ፥ እንደ ፡ በግ ፡ ጠጕርም ፡ ትል ፡ ይበላቸዋል ፤ ጽድቄ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡
ማዳኔም ፡ ለትውልድ ፡ ኹሉ ፡ ይኾናል ።

9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ክንድ ፡ ሆይ ፥ ተነሥ ፥ ተነሥ ፥ ኀይልንም ፡ ልበስ ፤ በቀድሞው ፡ ወራትና ፡ በጥንቱ ፡ ዘመን ፡
በነበረው ፡ ትውልድ ፡ እንደኾነው ፡ ተነሥ ። ረዓብን ፡ የቈራረጥኽ ፡ ዘንዶውንም ፡ የወጋኽ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧

10 ፤ ባሕሩንና ፡ የታላቁን ፡ ጥልቅ ፡ ውሃ ፡ ያደረቅኸው ፥ የዳኑትም ፡ ይሻገሩ ፡ ዘንድ ፡ ጠሊቁን ፡ ባሕር ፡ መንገድ ፡
ያደረግኽ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተቤዣቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ ወደ ፡ ጽዮንም ፡ ይመጣሉ ፤ የዘለዓለምም ፡ ደስታ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡
ይኾናል ፤ ደስታንና ፡ ተድላን ፡ ያገኛሉ ፥ ሐዘንና ፡ ልቅሶም ፡ ይሸሻል ።

12 ፤ የማጽናናችኹ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ እኔ ፡ ነኝ ፤ የሚሞተውን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሣርም ፡ የሚጠወልገውን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡
ትፈራ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧

13 ፤ ሰማያትንም ፡ የዘረጋው ፡ ምድርንም ፡ የመሠረተውን ፡ ፈጣሪኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረስተኻል ፤ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡
ባዘጋጀ ፡ ጊዜ ፡ ካስጨናቂው ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡ ኹልጊዜ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ፈርተኻል ፤ የአስጨናቂው ፡ ቍጣ ፡ የት ፡ አለ ፧

14 ፤ ምርኮኛ ፡ ፈጥኖ ፡ ይፈታል ፤ አይሞትም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድም ፡ አይወርድም ፥ እንጀራም ፡ አይጐድልበትም ።

15 ፤ ሞገዱም ፡ እንዲተሙ ፡ ባሕርን ፡ የማናውጥ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ ስሜም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ፡ ነው ።

16 ፤ ሰማያትን ፡ እዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ ምድርንም ፡ እመሠርት ፡ ዘንድ ፥ ጽዮንንም ፦ አንቺ ፡ ሕዝቤ ፡ ነሽ ፡ እል ፡ ዘንድ ፡
ቃሌን ፡ በአፍኽ ፡ አድርጌያለኹ ፥ በእጄም ፡ ጥላ ፡ ጋርጄኻለኹ ።

17 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የቍጣውን ፡ ጽዋ ፡ የጠጣሽ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ንቂ ፥ ንቂ ፥ ቁሚ ፤ የሚያንገደግድን ፡
ዋንጫ ፡ ጠጥተሻል ፡ ጨልጠሽውማል ።



www.ethiopianorthodox.org

18 ፤ ከወለደቻቸው ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ የሚመራት ፡ የለም ፥ ካሳደገቻቸውም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እጇን ፡ የሚይዝ ፡ የለም ።

19 ፤ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፡ ኾነውብሻል ፥ ማንስ ፡ ያስተዛዝንሻል ፧ መፈታትና ፡ ጥፋት ፡ ራብና ፡ ሰይፍ ፡
ናቸው ፤ እንዴትስ ፡ አድርጌ ፡ አጽናናሻለኹ ፧

20 ፤ ልጆችሽ ፡ ዝለዋል ፤ በወጥመድ ፡ እንደተያዘ ፡ ሚዳቋ ፡ በአደባባይ ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡
ተኝተዋል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣና ፡ በአምላክሽ ፡ ተግሣጽ ፡ ተሞልተዋል ።

21 ፤ ስለዚህም ፡ ያለወይን ፡ ጠጅ ፡ የሰከርሽ ፡ አንቺ ፡ ችግረኛ ፥ ይህን ፡ ስሚ ፤

22 ፤ ስለ ፡ ወገኑ ፡ የሚሟገት ፡ አምላክሽ ፡ ጌታሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እንሆ ፥ የሚያንገደግድን ፡ ጽዋ ፡
የቍጣዬንም ፡ ዋንጫ ፡ ከእጅሽ ፡ ወስጃለኹ ፤ ደግመሽም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትጠጪውም ።

23 ፤ ነፍስሽንም ፡— እንሻገር ፡ ዘንድ ፡ ዝቅ ፡ በዪ ፡ በሚሏት ፡ በአስጨናቂዎችሽ ፡ እጅ ፡ አኖረዋለኹ ፤ ዠርባሽንም ፡
ለሚሻገሩት ፡ እንደ ፡ መሬትና ፡ እንደ ፡ መንገድ ፡ አደረግሽላቸው ።

____________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 52 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 52 ።

1 ፤ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ተነሺ ፥ ተነሺ ፥ ኀይልሽን ፡ ልበሺ ፤ ቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ያልተገረዘና ፡ ርኩስ ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይገባብሽምና ፡ ጌጠኛ ፡ ልብስሽን ፡ ልበሺ ።

2 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ትቢያን ፡ አራግፊ ፤ ተነሺ ፥ ተቀመጪ ፤ ምርኮኛዪቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የዐንገትሽን ፡
እስራት ፡ ፍቺ ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በከንቱ ፡ ተሸጣችኹ ፡ ነበር ፥ ያለገንዘብም ፡ ትቤዧላችኹ ።

4 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ወገኔ ፡ በዚያ ፡ እንግዳ ፡ ኾኖ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡
ግብጽ ፡ ወረደ ፥ አሶርም ፡ ያለምክንያት ፡ በደለው ።

5 ፤ ወገኔ ፡ በከንቱ ፡ ተወስዷልና ፥ አኹን ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የሚገዟቸው ፡
ይጮኻሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ስሜም ፡ ኹልጊዜ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ይሰደባል ።

6 ፤ ስለዚህ ፥ ወገኔ ፡ ስሜን ፡ ያውቃል ፥ ስለዚህም ፡ የምናገር ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ያውቃሉ ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ነኝ ።

7 ፤ የምሥራች ፡ የሚናገር ፥ ሰላምንም ፡ የሚያወራ ፥ የመልካምንም ፡ ወሬ ፡ የምሥራች ፡ የሚናገር ፥ መድኀኒትንም ፡
የሚያወራ ፥ ጽዮንንም ፡— አምላክሽ ፡ ነግሧል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ እግሩ ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነው ።

8 ፤ እንሆ ፥ ጕበኛዎችሽ ፡ ጮኸዋል ፤ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ጽዮን ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ዐይን ፡ በዐይን ፡ ይተያያሉና ፡
ድምፃቸውን ፡ ያነሣሉ ፥ በአንድነትም ፡ ይዘምራሉ ።

9 ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ፍርስራሾች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ አጽናንቷልና ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡
ታድጓልና ፥ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ በአንድነትም ፡ ዘምሩ ።

10 ፤ እግዚአብሔር ፡ የተቀደሰውን ፡ ክንዱን ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ገልጧል ፥ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ የሚኖሩትም ፡ ኹሉ ፡
የአምላካችንን ፡ መድኀኒት ፡ ያያሉ ።

11 ፤ እናንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡ የምትሸከሙ ፡ ሆይ ፥ እልፍ ፡ በሉ ፥ እልፍ ፡ በሉ ፥ ከዚያ ፡ ውጡ ፥ ርኩስን ፡ ነገር ፡
አትንኩ ፥ ከመካከሏ ፡ ውጡ ፥ ንጹሓን ፡ ኹኑ ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይቀድማችኋልና ፥ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ይከተላችኋልና ፥ በችኰላ ፡ አትወጡም ፡
በመኰብለልም ፡ አትኼዱም ።

13 ፤ እንሆ ፥ ባሪያዬ ፡ በማስተዋል ፡ ያደርጋል ፤ ይከብራል ፡ ከፍ ፡ ከፍም ፡ ይላል ፥ እጅግ ፡ ታላቅም ፡ ይኾናል ።

14 ፤ ፊቱ ፡ ከሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፥ መልኩም ፡ ከሰዎች ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ተጐሳቍሏልና ፥ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ አንተ ፡



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፡ ተደነቁ ፥ እንዲሁ ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ ያስደንቃል ፤

15 ፤ ያልተነገረላቸውንም ፡ ያያሉና ፥ ያልሰሙትንም ፡ ያስተውላሉና ፡ ነገሥታት ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አፋቸውን ፡ ይዘጋሉ ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 53 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 53 ።

1 ፤ የሰማነውን ፡ ነገር ፡ ማን ፡ አምኗል ፧ የእግዚአብሔርስ ፡ ክንድ ፡ ለማን ፡ ተገልጧል ፧

2 ፤ በፊቱ ፡ እንደ ፡ ቡቃያ ፡ ከደረቅም ፡ መሬት ፡ እንደ ፡ ሥር ፡ አድጓል ። መልክና ፡ ውበት ፡ የለውም ፥ ባየነውም ፡ ጊዜ ፡ እንወደው ፡ ዘንድ ፡ ደም ፡ ግባት ፡ የለውም ።

3 ፤ የተናቀ ፡ ከሰውም ፡ የተጠላ ፥ የሕማም ፡ ሰው ፡ ደዌንም ፡ የሚያውቅ ፡ ነው ፤ ሰውም ፡ ፊቱን ፡ እንደሚሰውርበት ፡ የተናቀ ፡ ነው ፥ እኛም ፡ አላከበርነውም ።

4 ፤ በእውነት ፡ ደዌያችንን ፡ ተቀበለ ፡ ሕመማችንንም ፡ ተሸክሟል ፤ እኛ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተመታ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተቀሠፈ ፡ እንደ ፡ ተቸገረም ፡ ቈጠርነው ።

5 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ መተላለፋችን ፡ ቈሰለ ፥ ስለ ፡ በደላችንም ፡ ደቀቀ ፤ የደኅንነታችንም ፡ ተግሣጽ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፥ በርሱም ፡ ቍስል ፡ እኛ ፡ ተፈወስን ።

6 ፤ እኛ ፡ ኹላችን ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ ተቅበዝብዘን ፡ ጠፋን ፤ ከእኛ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡ መንገዱ ፡ አዘነበለ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የኹላችንን ፡ በደል ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አኖረ ።

7 ፤ ተጨነቀ ፡ ተሣቀየም ፡ አፉንም ፡ አልከፈተም ፤ ለመታረድ ፡ እንደሚነዳ ፡ ጠቦት ፥ በሸላቾቹም ፡ ፊት ፡ ዝም ፡ እንደሚል ፡ በግ ፥ እንዲሁ ፡ አፉን ፡ አልከፈተም ።

8 ፤ በማስጨነቅና ፡ በፍርድ ፡ ተወሰደ ፤ ስለሕዝቤ ፡ ኀጢአት ፡ ተመቶ ፡ ከሕያዋን ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተወገደ ፡ ከትውልዱ ፡ ማን ፡ አስተዋለ ፧

9 ፤ ከክፉዎችም ፡ ጋራ ፡ መቃብሩን ፡ አደረጉ ፥ ከባለጠጋዎችም ፡ ጋራ ፡ በሞቱ ፡ ኾኖም ፡ ግፍን ፡ አላደረገም ፡ ነበር ፥ በአፉም ፡ ተንኰል ፡ አልተገንበትም ፡ ነበር ።

10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በደዌ ፡ ያደቅው ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደ ፤ ነፍሱን ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ዘሩን ፡ ያያል ፥ ዕድሜውም ፡ ይረዝማል ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ በእጁ ፡ ይከናወናል ።

11 ፤ ከነፍሱ ፡ ድካም ፡ ብርሃን ፡ ያያል ፡ ደስም ፡ ይለዋል ፤ ጻድቅ ፡ ባሪያዬም ፡ በዕውቀቱ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያጸድቃል ፥ ኀጢአታቸውን ፡ ይሰከማል ።

12 ፤ ስለዚህም ፡ ርሱ ፡ ብዙዎችን ፡ ይወርሳል ፥ ከኀያላንም ፡ ጋራ ፡ ምርኮን ፡ ይከፋፈላል ፤ ነፍሱን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፥ ከዐመፀኛዎችም ፡ ጋራ ፡ ተቈጥሯልና ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ኀጢአት ፡ ተሸከመ ፥ ስለ ፡ ዐመፀኛዎችም ፡ ማለደ ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 54 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 54 ።

1 ፤ አንቺ ፡ ያልወለድሽ ፡ መካን ፡ ሆይ ፥ ዘምሪ ፤ አንቺ ፡ ያላማጥሽ ፡ ሆይ ፥ እልል ፡ በዪ ፥ ጩኺም ፤ ባል ፡ ካላት ፡ ይልቅ ፡ ፈት ፡ የኾነቺቱ ፡ ልጆች ፡ በዝተዋልና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

2 ፤ የድንኳንሽን ፡ ስፍራ ፡ አስፊ ፥ መጋረጃዎችሽንም ፡ ይዘርጉ ፤ አትቈጥቢ ፤ አውታሮችሽን ፡ አስረዝሚ ፡ ካስማዎችሽንም ፡ አጽኚ ።

3 ፤ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ትሰፋፊያለሽና ፥ ዘርሽም ፡ አሕዛብን ፡ ይወርሳልና ፥ የፈረሱትንም ፡ ከተማዎች ፡ መኖሪያ ፡ ያደርጋልና ።

4 ፤ አታፍሪምና ፡ አትፍሪ ፤ አትዋረጂምና ፡ አትደንግጪ ፤ የሕፃንነትሽንም ፡ ዕፍረት ፡ ትረሺዋለሽ ፥ የመበለትነትሽንም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ስድብ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታስቢም ።

5 ፤ ፈጣሪሽ ፡ ባልሽ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ ታዳጊሽ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ የምድር ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ ይባላል ።

6 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተተወችና ፡ እንደ ፡ ተበሳጨች ፡ በልጅነቷም ፡ እንደ ፡ ተጣለች ፡ ሚስት ፡ ጠርቶሻል ፥ ይላል ፡ አምላክሽ ።

7 ፤ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተውኹሽ ፥ በታላቅም ፡ ምሕረት ፡ እሰበስብሻለኹ ።

8 ፤ በጥቂት ፡ ቍጣ ፡ ለቅጽበት ፡ ዐይን ፡ ፊቴን ፡ ከአንቺ ፡ ሰወርኹ ፥ በዘለዓለምም ፡ ቸርነት ፡ እምርሻለኹ ፥ ይላል ፡ ታዳጊሽ ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ ይህ ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ ኖኅ ፡ ውሃ ፡ ነው ፤ የኖኅ ፡ ውሃ ፡ ደግሞ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዳያልፍ ፡ እንደ ፡ ማልኹ ፥ እንዲሁ ፡ አንቺን ፡ እንዳልቈጣ ፡ እንዳልዘልፍሽም ፡ ምያለኹ ።

10 ፤ ተራራዎች ፡ ይፈልሳሉ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ይወገዳሉ ፤ ቸርነቴ ፡ ግን ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ አይፈልስም ፡ የሰላሜም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አይወገድም ፥ ይላል ፡ መሓሪሽ ፡ እግዚአብሔር ።

11 ፤ አንቺ ፡ የተቸገርሽ ፡ በዐውል ፡ ነፋስም ፡ የተናወጥሽ ፡ ያልተጽናናሽም ፥ እንሆ ፥ ድንጋዮችሽን ፡ ሸላልሜ ፡ እገነባለኹ ፥ በሰንፔርም ፡ እመሠርትሻለኹ ።

12 ፤ የግንብሽንም ፡ ጒልላት ፡ በቀይ ፡ ዕንቍ ፥ በሮችሽንም ፡ በሚያብረቀርቅ ፡ ዕንቍ ፥ ዳርቻሽንም ፡ ኹሉ ፡ በከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ እሠራለኹ ።

13 ፤ ልጆችሽም ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተማሩ ፡ ይኾናሉ ፥ የልጆችሽም ፡ ሰላም ፡ ብዙ ፡ ይኾናል ።

14 ፤ በጽድቅ ፡ ትታነጺያለሽ ፤ ከግፍ ፡ ራቂ ፥ አትፈሪምም ፥ ድንጋጤም ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ አትቀርብም ።

15 ፤ እንሆ ፥ ይሰበሰባሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አይኾንም ፤ ባንቺም ፡ ላይ ፡ የሚሰበሰቡ ፡ ኹሉ ፡ ከአንቺ ፡ የተነሣ ፡ ይወድቃሉ ።

16 ፤ እንሆ ፥ ፍሙን ፡ በወናፍ ፡ የሚያናፋ ፡ ለሥራውም ፡ መሣሪያ ፡ የሚያወጣ ፡ ብረት ፡ ሠሪን ፡ እኔ ፡ ፈጥሬያለኹ ፤ የሚያፈርሰውንም ፡ እንዲያጠፋ ፡ ፈጥሬያለኹ ።

17 ፤ ባንቺ ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ መሣሪያ ፡ ኹሉ ፡ አይከናወንም ፤ በፍርድም ፡ በሚነሣብሽ ፡ ምላስ ፡ ኹሉ ፡ ትፈርጂበታለሽ ። የእግዚአብሔር ፡ ባሪያዎች ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ጽድቃቸውም ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 55 ።

ምዕራፍ ፡ 55 ።

1 ፤ እናንተ ፡ የተጠማችኹ ፡ ኹሉ ፥ ወደ ፡ ውሃ ፡ ኑ ፥ ገንዘብም ፡ የሌላችኹ ፡ ኑና ፡ ግዙ ፡ ብሉም ፤ ኑ ፡ ያለገንዘብም ፡ ያለዋጋም ፡ የወይን ፡ ጠጅና ፡ ወተት ፡ ግዙ ።

2 ፤ ገንዘብን ፡ እንጀራ ፡ ላይደለ ፥ የድካማችኹንም ፡ ዋጋ ፡ ለማያጠግብ ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ትመዝናላችኹ ፧ አድምጡኝ ፥ በረከትንም ፡ ብሉ ፥ ሰውነታችኹም ፡ በጮማ ፡ ደስ ፡ ይበለው ።

3 ፤ ዦሯችኹን ፡ አዘንብሉ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ቅረቡ ፤ ስሙ ፡ ሰውነታችኹም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለች ፤ የታመነችዪቱን ፡ የዳዊትን ፡ ምሕረት ፥ የዘለዓለምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አደርጋለኹ ።

4 ፤ እንሆ ፥ ለአሕዛብ ፡ ምስክር ፥ ለወገኖችም ፡ አለቃና ፡ አዛዥ ፡ እንዲኾን ፡ ሰጥቼዋለኹ ።

5 ፤ እንሆ ፥ የማታውቀውን ፡ ሕዝብ ፡ ትጠራለኽ ፥ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ አክብሮኻልና ፥ ስለ ፡ አምላክኽ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማያውቁኽ ፡ ሕዝብ ፡ ወዳንተ ፡ ይሮጣሉ ።

6 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ፈልጉት ፥ ቀርቦም ፡ ሳለ ፡ ጥሩት ፤



www.ethiopianorthodox.org

7 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ መንገዱን ፡ በደለኛም ፡ ዐሳቡን ፡ ይተው ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመለስ ፡ ርሱም ፡
ይምረዋል ፥ ይቅርታውም ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ይመለስ ።

8 ፤ ዐሳቤ ፡ እንደ ፡ ዐሳባችኹ ፡ መንገዳችኹም ፡ እንደ ፡ መንገዴ ፡ አይደለምና ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ ሰማይ ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ እንደሚል ፥ እንዲሁ ፡ መንገዴ ፡ ከመንገዳችኹ ፡ ዐሳቤም ፡ ከዐሳባችኹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

10 ፤ ዝናብና ፡ በረዶ ፡ ከሰማይ ፡ እንደሚወርድ ፥ ምድርን ፡ እንደሚያረካት ፥ ታበቅልና ፡ ታፈራም ፡ ዘንድ ፡
እንደሚያደርጋት ፥ ዘርንም ፡ ለሚዘራ ፡ እንጀራንም ፡ ለሚበላ ፡ እንደሚሰጥ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እንደማይመለስ ፥

11 ፤ ከአፌ ፡ የሚወጣ ፡ ቃሌ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ፤ የምሻውን ፡ ያደርጋል ፡ የላክኹትንም ፡ ይፈጽማል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡
እኔ ፡ በከንቱ ፡ አይመለስም ።

12 ፤ እናንተም ፡ በደስታ ፡ ትወጣላችኹ ፡ በሰላምም ፡ ትሸኛላችኹ ፤ ተራራዎችና ፡ ኰረብታዎች ፡ በፊታችኹ ፡ እልልታ ፡
ያደርጋሉ ፥ የሜዳም ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ያጨበጭባሉ ።

13 ፤ በሾኽም ፡ ፋንታ ፡ ጥድ ፡ በሸርንችትም ፡ ፋንታ ፡ ባርሰነት ፡ ይበቅላል ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ መታሰቢያን ፡
ለዘለዓለምም ፡ የማይጠፋ ፥ ምልክት ፡ ይኾናል ።

___________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 56 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 56 ።

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ማዳኔ ፡ ሊመጣ ፡ ጽድቄም ፡ ሊገለጥ ፡ ቀርቧልና ፥ ፍርድን ፡ ጠብቁ ፡ ጽድቅንም ፡
አድርጉ ።

2 ፤ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ይህንንም ፡ የሚይዝ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፥ እንዳያረክሰው ፡ ሰንበትንም ፡ የሚጠብቅ ፡ እጁንም ፡
ክፉት ፡ ከማድረግ ፡ የሚጠብቅ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

3 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የተጠጋ ፡ መጻተኛ ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ይለየኛል ፡ አይበል ፤ ጃን ፡
ደረባም ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ደረቅ ፡ ዛፍ ፡ ነኝ ፡ አይበል ።

4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰንበቴን ፡ ስለሚጠብቁ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘኝንም ፡ ነገር ፡ ስለሚመርጡ ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡
ስለሚይዙ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

5 ፤ በቤቴና ፡ በቅጥሬ ፡ ውስጥ ፡ ከወንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጥ ፡ መታሰቢያና ፡ ስም ፡
እሰጣቸዋለኹ ፤ የማይጠፋም ፡ የዘለዓለም ፡ ስም ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

6 ፤ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ ይወዱ ፡ ዘንድ ፡ ባሪያዎቹም ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
የሚጠጉትንም ፡ መጻተኛዎች ፥ እንዳያረክሱት ፡ ሰንበትን ፡ የሚጠብቁትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ የሚይዙትን ፡ ኹሉ ፥

7 ፤ ወደተቀደሰ ፡ ተራራዬ ፡ አመጣቸዋለኹ ፥ በጸሎቴም ፡ ቤት ፡ ደስ ፡ አሠኛቸዋለኹ ፤ ቤቴ ፡ ለአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡
የሚኾን ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ይባላልና ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታቸውንና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡
እቀበላለኹ ።

8 ፤ ከእስራኤል ፡ የተበተኑትን ፡ የሚሰበስብ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ ወደተሰበሰቡት ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡
እሰበስብለታለኹ ፡ ይላል ።

9 ፤ እናንተ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፥ እናንተም ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፥ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ ቅረቡ ።

10 ፤ ጕበኛዎቹ ፡ ዕውሮች ፡ ናቸው ፥ ኹሉ ፡ ያለዕውቀት ፡ ናቸው ፤ ኹሉም ፡ ዲዳ ፡ የኾኑ ፡ ውሻዎች ፡ ናቸው ፡
ይጮኹም ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ፤ ሕልምን ፡ ያልማሉ ፤ ይተኛሉ ፤ ማንቀላፋትንም ፡ ይወዳሉ ።

11 ፤ መብል ፡ ወዳጆች ፡ ክፉ ፡ የማይጠግቡ ፡ ውሻዎች ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ የማይችሉ ፡ እረኛዎች ፡
ናቸው ፤ ኹሉ ፡ ወደ ፡ መንገዳቸው ፥ ከፊተኛው ፡ እስከ ፡ ኋለኛው ፡ ድረስ ፡ ኹሉ ፥ እያንዳንዳቸው ፡ ወደ ፡ ጥቅማቸው ፡
ዘወር ፡ ብለዋል ።

12 ፤ ኑ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንውሰድ ፥ በሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ እንርካ ፤ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዲሁ ፡ ነገ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይኹናል ፥ ከዛሬም ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ይበልጣል ፡ ይላሉ ።

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 57 ።

ምዕራፍ ፡ 57 ።

1 ፤ ጻድቅ ፡ ይሞታል ፥ በልቡም ፡ ነገሩን ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ ምሕረተኛዎችም ፡ ይወገዳሉ ፥ ጻድቅም ፡ ከክፋት ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተወገደ ፡ ማንም ፡ አያስተውልም ።

2 ፤ ወደ ፡ ሰላም ፡ ይገባል ፤ በቅንነት ፡ የኼደ ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ያርፋል ።

3 ፤ እናንተ ፡ የአስማተኛዪቱ ፡ ልጆች ፥ የአመንዝራውና ፡ የጋለሞታዪቱ ፡ ዘር ፥ ወደዚህ ፡ ቅረቡ ።

4 ፤ በማን ፡ ታላግጣላችኹ ፧ በማንስ ፡ ላይ ፡ አፋችኹን ፡ ታላቅቃላችኹ ፧ ምላሳችኹንስ ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ታስረዝማላችኹ ፧

5 ፤ እናንተ ፡ በአድባር ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ በለመለመም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ በፍትወት ፡ የምትቃጠሉ ፥ እናንተም ፡ በሸለቆዎች ፡ ውስጥ ፡ በአለትም ፡ ስንጣቂዎች ፡ በታች ፡ ሕፃናትን ፡ የምታርዱ ፥ የዐመፅ ፡ ልጆችና ፡ የሐሰት ፡ ዘር ፡ አይደላችኹምን ፧

6 ፤ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የለዘቡ ፡ ድንጋዮች ፡ ዕድል ፡ ፈንታሽ ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፡ ዕጣሽ ፡ ናቸው ፤ ለእነርሱም ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ አፍሰሻል ፥ የእኽልንም ፡ ቍርባን ፡ አቅርበሻል ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አልቈጣምን ፧

7 ፤ ከፍ ፡ ባለውም ፡ በረዘመውም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ መኝታሽን ፡ አደረግሽ ፥ መሥዋዕትንም ፡ ትሠዊ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ ወጣሽ ።

8 ፤ ከመዝጊያውና ፡ ከመቃኑ ፡ በኋላ ፡ መታሰቢያሽን ፡ አደረግሽ ፤ እኔን ፡ ትተሽ ፡ ለሌላ ፡ ተገልጠሻል ፥ ወጥተሽ ፡ መኝታሽን ፡ አስፍተሻል ፤ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ተጋባሻቸው ፥ ባየሽበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ መኝታቸውን ፡ ወደድሽ ።

9 ፤ ዘይትም ፡ ይዘሽ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ኼድሽ ፥ ሽቱሽንም ፡ አበዛሽ ፥ መልእክተኛዎችሽንም ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ላክሽ ፥ እስከ ፡ ሲኦልም ፡ ድረስ ፡ ተዋረድሽ ።

10 ፤ በመንገድሽም ፡ ብዛት ፡ ደከምሽ ፥ ነገር ፡ ግን ፦ ተስፋ ፡ የለም ፡ አላልሽም ፤ የጕልበትን ፡ መታደስ ፡ አገኘሽ ፥ ስለዚህም ፡ አልዛልሽም ።

11 ፤ ሐሰትን ፡ የተናገርሺው ፡ እኔንም ፡ ያላሰብሺው ፡ በልብሽም ፡ ነገሩን ፡ ያላኖርሺው ፡ ማንን ፡ ሠግተሽ ፡ ነው ፧ ማንንስ ፡ ፈርተሽ ፡ ነው ፧ እኔ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አልኹ ፥ አንቺም ፡ አልፈራሽም ።

12 ፤ እኔ ፡ ጽድቅሽን ፡ እናገራለኹ ፥ ሥራሽም ፡ አይረባሽም ።

13 ፤ ወደ ፡ አንቺ ፡ የሰበሰብሻቸው ፡ በጮኽሽ ፡ ጊዜ ፡ ይታደጉሽ ፤ ነፋስ ፡ ግን ፡ ይወስዳቸዋል ፡ ሽውሽውታም ፡ ኹሉን ፡ ያስወግዳቸዋል ። በእኔ ፡ የታመነ ፡ ግን ፡ ምድሪቱን ፡ ይገዛል ፥ የተቀደሰውንም ፡ ተራራዬን ፡ ይወርሳል ።

14 ፤ ርሱም ፦ ጥረጉ ፥ መንገድን ፡ አዘጋጁ ፥ ከሕዝቤም ፡ መንገድ ፡ ዕንቅፋትን ፡ አውጡ ፡ ይላል ።

15 ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ስሙም ፡ ቅዱስ ፡ የኾነ ፥ ከፍ ፡ ያለው ፡ ልዑል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የተዋረዱትን ፡ ሰዎች ፡ መንፈስ ፡ ሕያው ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፥ የተቀጠቀጠውንም ፡ ልብ ፡ ሕያው ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፥ የተቀጠቀጠና ፡ የተዋረደ ፡ መንፈስ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ በከፍታና ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ እቀመጣለኹ ።

16 ፤ መንፈስም ፡ የፈጠርኹትም ፡ ነፍስ ፡ ከፊቴ ፡ እንዳይዝል ፡ ለዘለዓለም ፡ አልጣላም ፥ ኹልጊዜም ፡ አልቈጣም ።

17 ፤ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቈጥቼ ፡ ቀሠፍኹት ፥ ፊቴን ፡ ሰውሬ ፡ ተቈጣኹ ፤ ርሱም ፡ በልቡ ፡ መንገድ ፡ እያፈገፈገ ፡ ኼደ ።

18 ፤ መንገዱን ፡ አይቻለኹ ፡ እፈውሰውማለኹ ፥ እመራውማለኹ ፥ ለርሱና ፡ ስለ ፡ ርሱም ፡ ለሚያለቅሱ ፡ መጽናናትን ፡ እመልሳለኹ ።

19 ፤ የከንፈሮችን ፡ ፍሬ ፡ እፈጥራለኹ ፤ በሩቅም ፡ በቅርብም ፡ ላለው ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይኹን ፥ እፈውሰውማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

20 ፤ ክፉዎች ፡ ግን ፡ እንደሚንቀሳቀስ ፡ ባሕር ፡ ናቸው ፤ ጸጥ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፥ ውሃዎቹም ፡ ጭቃና ፡ ጕድፍ ፡ ያወጣሉና ።

21 ፤ ለክፉዎች ፡ ሰላም ፡ የላቸውም ፡ ይላል ፡ አምላኬ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 58 ።

ምዕራፍ ፡ 58 ።

1 ፤ በኀይልኽ ፡ ጩኽ ፥ አትቈጥብ ፥ ድምፅኽን ፡ እንደ ፡ መለከት ፡ አንሣ ፥ ለሕዝቤ ፡ መተላለፋቸውን ፡ ለያዕቆብ ፡ ቤትም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ንገር ።

2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሹኛል ፡ መንገዴንም ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ይወዳሉ ፤ ጽድቅን ፡ እንዳደረጉ ፡ የአምላካቸውንም ፡ ፍርድ ፡ እንዳልተዉ ፡ ሕዝብ ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ይለምኑኛል ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለመቅረብ ፡ ይወዳሉ ።

3 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ጾምን ፥ አንተም ፡ አልተመለከትኸንም ፧ ሰውነታችንንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አዋረድን ፥ አንተም ፡ አላወቅኸም ፧ ይላሉ ። እንሆ ፥ በጾማችኹ ፡ ቀን ፡ ፈቃዳችኹን ፡ ታደርጋላችኹ ፥ ሠራተኛዎቻችኹንም ፡ ኹሉ ፡ ታስጨንቃላችኹ ።

4 ፤ እንሆ ፥ ለጥልና ፡ ለክርክር ፡ ትጾማላችኹ ፡ በግፍ ፡ ጡጫም ፡ ትማታላችኹ ፤ ድምፃችኹንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ታሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ እንደምትጾሙት ፡ አትጾሙም ።

5 ፤ እኔ ፡ የመረጥኹት ፡ ጾም ፡ ይህ ፡ ነውን ፧ ሰውስ ፡ ነፍሱን ፡ የሚያዋርደው ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ቀን ፡ ነውን ፧ በእውኑ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ እንግጫ ፡ ዝቅ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ማቅንና ፡ ዐመድንም ፡ በበታቹ ፡ ያነጥፍ ፡ ዘንድ ፡ ነውን ፧ በእውኑ ፡ ይህን ፡ ጾም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ቀን ፡ ትለዋለኽን ፧

6 ፤ እኔስ ፡ የመረጥኹት ፡ ጾም ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፧ የበደልን ፡ እስራት ፡ ትፈቱ ፡ ዘንድ ፥ የቀንበርንስ ፡ ጠፍር ፡ ትለቅቁ ፡ ዘንድ ፥ የተገፉትንስ ፡ ሐራነት ፡ ትሰዱ ፡ ዘንድ ፥ ቀንበሩንስ ፡ ኹሉ ፡ ትሰብሩ ፡ ዘንድ ፡ አይደለምን ፧

7 ፤ እንጀራኽንስ ፡ ለተራበ ፡ ትቈርስ ፡ ዘንድ ፥ ስደተኛዎቹን ፡ ድኻዎች ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ታገባ ፡ ዘንድ ፥ የተራቈተውንስ ፡ ብታይ ፡ ታለብሰው ፡ ዘንድ ፥ ከሥጋ ፡ ዘመድኽ ፡ እንዳትሸሸግ ፡ አይደለምን ፧

8 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብርሃንኽ ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ይበራል ፥ ፈውስኽም ፡ ፈጥኖ ፡ ይበቅላል ፥ ጽድቅኽም ፡ በፊትኽ ፡ ይኼዳል ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ በኋላኽ ፡ ኾኖ ፡ ይጠብቅኻል ።

9 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ትጠራለኽ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይሰማኻል ፤ ትጮኻለኽ ፡ ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ ይላል ። ከመካከልኽ ፡ ቀንበርን ፡ ብታርቅ ፥ ጣትኽንም ፡ መጥቀስ ፡ ብትተው ፥

10 ፤ ባታንጐራጕርም ፥ ነፍስኽንም ፡ ለተራበ ፡ ብታፈስ ፥ የተጨነቀውንም ፡ ነፍስ ፡ ብታጠግብ ፥ ብርሃንኽ ፡ በጨለማ ፡ ይወጣል ፡ ጨለማኽም ፡ እንደ ፡ ቀትር ፡ ይኾናል ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኹልጊዜ ፡ ይመራኻል ፤ ነፍስኽንም ፡ በመልካም ፡ ነገር ፡ ያጠግባል ፡ ዐጥንትኽንም ፡ ያጠናል ፤ አንተም ፡ እንደሚጠጣ ፡ ገነት ፥ ውሃውም ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ምንጭ ፡ ትኾናለኽ ።

12 ፤ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ የፈረሱት ፡ ስፍራዎች ፡ ይሠራሉ ፥ የብዙ ፡ ትውልድም ፡ መሠረት ፡ ይታነጻል ፤ አንተም ፦ ሰባራውን ፡ ጠጋኝ ፥ የመኖሪያ ፡ መንገድን ፡ ዐዳሽ ፡ ትባላለኽ ።

13 ፤ ፈቃድኽን ፡ በተቀደሰው ፡ ቀኔ ፡ ከማድረግ ፡ እግርኽን ፡ ከሰንበት ፡ ብትመልስ ፥ ሰንበትንም ፡ ደስታ ፥ እግዚአብሔርም ፡ የቀደሰውን ፡ ክቡር ፡ ብትለው ፥ የገዛ ፡ መንገድኽንም ፡ ከማድረግ ፡ ፈቃድኽንም ፡ ከማግኘት ፡ ከንቱ ፡ ነገርንም ፡ ከመናገር ፡ ተከልክለኽ ፡ ብታከብረው ፥

14 ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይልኻል ፥ በምድርም ፡ ከፍታዎች ፡ ላይ ፡ አወጣኻለኹ ፥ የአባትኽንም ፡ የያዕቆብን ፡ ርስት ፡ አበላኻለኹ ፤ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ተናግሯልና ።



www.ethiopianorthodox.org

## ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 59 ።

ምዕራፍ ፡ 59 ።

1 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ከማዳን ፡ አላጠረችም ፥ ጆሮውም ፡ ከመስማት ፡ አልደነቈረችም ፤

2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በደላችኹ ፡ በእናንተና ፡ በአምላካችኹ ፡ መካከል ፡ ለይታለች ፥ እንዳይሰማም ፡ ኀጢአታችኹ ፡ ፊቱን ፡
ከእናንተ ፡ ሰውሮታል ።

3 ፤ እጃችኹ ፡ በደም ፡ ጣታችኹም ፡ በበደል ፡ ረክሳለች ፥ ከንፈራችኹም ፡ ሐሰትን ፡ ተናግሯል ፥ ምላሳችኹም ፡
ኀጢአትን ፡ አሰምቷል ።

4 ፤ በጽድቅ ፡ የሚጠራ ፡ በእውነትም ፡ የሚፈርድ ፡ የለም ፤ በምናምንቴ ፡ ነገር ፡ ታምነዋል ፡ ሐሰትንም ፡
ተናግረዋል ፤ ጕዳትን ፡ ፀንሰዋል ፡ በደልንም ፡ ወልደዋል ፤

5 ፤ የእባብን ፡ ዕንቍላል ፡ ቀፈቀፉ ፥ የሸረሪትንም ፡ ድር ፡ አደሩ ፤ ዕንቍላላቸውንም ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡
ይሞታል ፥ ዕንቍላሉም ፡ ሲሰበር ፡ እፍኝት ፡ ይወጣል ።

6 ፤ ድሮቻቸውም ፡ ልብስ ፡ አይኾኑላቸውም ፥ በሥራቸውም ፡ አይሸፈኑም ፤ ሥራቸውም ፡ የበደል ፡ ሥራ ፡
ነው ፥ የግፍም ፡ ሥራ ፡ በእጃቸው ፡ ነው ።

7 ፤ እግሮቻቸው ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ ይሮጣሉ ፥ ንጹሑን ፡ ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ ይፈጥናሉ ፤ ዐሳባቸው ፡ የኀጢአት ፡ ዐሳብ ፡
ነው ፥ ጕስቍልናና ፡ ቅጥቃጤ ፡ በመንገዳቸው ፡ አለ ።

8 ፤ የሰላምን ፡ መንገድ ፡ አያውቁም ፥ በአካኼዳቸውም ፡ ፍርድ ፡ የለም ፤ መንገዳቸውን ፡ አጣመዋል ፥ የሚኼድባትም ፡
ኹሉ ፡ ሰላምን ፡ አያውቅም ።

9 ፤ ስለዚህ ፥ ፍርድ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ርቋል ፥ ጽድቅም ፡ አላገኘንም ፤ ብርሃንን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቅ ፡
ነበር ፥ እንሆም ፥ ጨለማ ፡ ኾነ ፤ ጸዳልን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቅ ፡ ነበር ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በጨለማ ፡ ኼድን ።

10 ፤ እንደ ፡ ዕውሮች ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ ተርመሰመስን ፥ ዐይን ፡ እንደሌላቸው ፡ ተርመሰመስን ፤ በቀትር ፡ ጊዜ ፡
በድግዝግዝታ ፡ እንዳለ ፡ ሰው ፡ ተሰናከልን ፥ እንደ ፡ ሙታን ፡ በጨለማ ፡ ስፍራ ፡ ነን ።

11 ፤ ኹላችን ፡ እንደ ፡ ድቦች ፡ እንጮኻለን ፥ እንደ ፡ ርግብ ፡ እንለቃቀሳለን ፤ ፍርድን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቅ ፡
ነበር ፥ ርሱም ፡ የለም ፤ መዳንም ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ርቋል ።

12 ፤ ዐመፃችን ፡ ባንተ ፡ ፊት ፡ በዝቷልና ፥ ኀጢአታችን ፡ መስክሮብናልና ፥ ዐመፃችን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ነውና ፥ በደላችንን ፡ እናውቃለንና ።

13 ፤ ዐምፀናል ፥ ሐሰትን ፡ ተናግረናል ፥ አምላካችንንም ፡ ከመከተል ፡ ተመልሰናል ፤ ግፍንና ፡ ዐመፅንም ፡
ተናግረናል ፥ የኀጢአት ፡ ቃልንም ፡ ፀንሰን ፡ ከልብ ፡ አውጥተናል ።

14 ፤ ፍርድም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሷል ፥ ጽድቅም ፡ በሩቅ ፡ ቆሟል ፤ እውነትም ፡ በአደባባይ ፡ ላይ ፡
ወድቋልና ፥ ቅንነትም ፡ ሊገባ ፡ አልቻለምና ።

15 ፤ እውነትም ፡ ታጥቷል ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ሰው ፡ ለብዝበዛ ፡ ኾኗል ።

እግዚአብሔርም ፡ አየ ፥ ፍርድም ፡ ስለሌለ ፡ ተከፋ ።

16 ፤ ሰውም ፡ እንደሌለ ፡ አየ ፥ ወደ ፡ ርሱ ፡ የሚማልድ ፡ እንደሌለ ፡ ተረዳ ፥ ተደነቀም ፤ ስለዚህ ፥ የገዛ ፡ ክንዱ ፡
መድኀኒት ፡ አመጣለት ፥ ጽድቁም ፡ አገዘው ።

17 ፤ ጽድቅንም ፡ እንደ ፡ ጥሩር ፡ ለበሰ ፥ በራሱም ፡ ላይ ፡ የማዳንን ፡ ራስ ፡ ቍር ፡ አደረገ ፤ የበቀልንም ፡ ልብስ ፡
ለበሰ ፥ በቅንአትም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ተጐናጸፈ ።

18 ፤ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ ቍጣን ፡ ለባላጋራዎቹ ፥ ፍዳንም ፡ ለጠላቶቹ ፡ ይከፍላል ፤ ለደሴቶችም ፡
ፍዳቸውን ፡ ይከፍላል ።



www.ethiopianorthodox.org

19 ፤ ርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነፋስ ፡ እንደሚነዳው ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ፈሳሽ ፡ ይመጣልና ፥ በምዕራብ ፡ ያሉት ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፥ በፀሓይ ፡ መውጫም ፡ ያሉት ፡ ክብሩን ፡ ይፈራሉ ።

20 ፤ ለጽዮን ፡ ታዳጊ ፡ ይመጣል ፥ በያዕቆብም ፡ ዘንድ ፡ ከኀጢአት ፡ ለሚርቁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

21 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መንፈሴ ፡
በአፍኽም ፡ ውስጥ ፡ ያደረግኹት ፡ ቃሌ ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ከአፍኽ ፡ ከዘርኽም ፡ አፍ ፡ ከዘር ፡
ዘርኽም ፡ አፍ ፡ አያልፍም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 60 ።

ምዕራፍ ፡ 60 ።

1 ፤ ብርሃንሽ ፡ መጥቷልና ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ወጥቶልሻልና ፥ ተነሺ ፥ አብሪ ።

2 ፤ እንሆ ፥ ጨለማ ፡ ምድርን ፡ ድቅድቅ ፡ ጨለማም ፡ አሕዛብን ፡ ይሸፍናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይወጣል ፡ ክብሩም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ይታያል ፤

3 ፤ አሕዛብም ፡ ወደ ፡ ብርሃንሽ ፡ ነገሥታትም ፡ ወደ ፡ መውጫሽ ፡ ጸዳል ፡ ይመጣሉ ።

4 ፤ ዐይኖችሽን ፡ አንሥተሽ ፡ በዙሪያሽ ፡ ተመልከቺ ፤ እነዚህ ፡ ዅሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ፤ ወንዶች ፡
ልጆችሽ ፡ ከሩቅ ፡ ይመጣሉ ፥ ሴቶች ፡ ልጆችሽንም ፡ በጫንቃ ፡ ላይ ፡ ይሸከሟቸዋል ።

5 ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የባሕሩ ፡ በረከት ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ስለሚመለስ ፥ የአሕዛብም ፡ ብልጥግና ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡
ስለሚመጣ ፥ አይተሽ ፡ ደስ ፡ ይልሻል ፥ ልብሽም ፡ ይደነቃል ፡ ይሰፋማል ።

6 ፤ የግመሎች ፡ ብዛት ፥ የምድያምና ፡ የጌፌር ፡ ግመሎች ፥ ይሸፍኑሻል ፤ ዅሉ ፡ ከሳባ ፡ ይመጣሉ ፥ ወርቅንና ፡
ዕጣንን ፡ ያመጣሉ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ምስጋና ፡ ያወራሉ ።

7 ፤ የቄዳር ፡ መንጋዎች ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይሰበሰባሉ ፡ የነባዮትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ያገለግሉሻል ፤ እኔን ፡ ደስ ፡
ሊያሠኙ ፡ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፥ የክብሬንም ፡ ቤት ፡ አከብራለኹ ።

8 ፤ ርግቦች ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ እንደሚበሩ ፥ እነዚህ ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ የሚበሩ ፡ እነማን ፡ ናቸው ፧

9 ፤ ርሱ ፡ አክብሮሻልና ፥ ለአምላክሽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስምና ፡ ለእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ልጆችሽን ፡ ከሩቅ ፡ ከነርሱ ፡
ጋራም ፡ ብራቸውንና ፡ ወርቃቸውን ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ደሴቶች ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦችም ፡ አስቀድመው ፡
ይጠባበቁኛል ።

10 ፤ በቍጣዬ ፡ ቀሥፌ ፡ በፍቅሬ ፡ ምሬሻለኹና ፡ መጻተኛዎች ፡ ቅጥርሽን ፡ ይሠራሉ ፥ ነገሥታታቸውም ፡ ያገለግሉሻል ።

11 ፤ በሮችሽም ፡ ዅልጊዜ ፡ ይከፈታሉ ፤ ሰዎች ፡ የአሕዛብን ፡ ብልጥግና ፡ የተማረኩትንም ፡ ነገሥታታቸውን ፡ ወደ ፡
አንቺ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ አይዘጉም ።

12 ፤ ለአንቺም ፡ የማይገዛ ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥት ፡ ይጠፋል ፥ እነዚያ ፡ አሕዛብም ፡ ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ።

13 ፤ የመቅደሴንም ፡ ስፍራ ፡ ያስጌጡ ፡ ዘንድ ፡ የሊባኖስ ፡ ክብር ፥ ጥዱና ፡ አስታው ፡ ባርሰነቱም ፥ ወደ ፡ አንቺ ፡
ይመጣሉ ፥ የእግሬንም ፡ ስፍራ ፡ አከብራለኹ ።

14 ፤ የአስጨናቂዎችሽም ፡ ልጆች ፡ ዐንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ፥ የናቁሽም ፡ ዅሉ ፡ ወደእግርሽ ፡
ጫማ ፡ ይሰግዳሉ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ከተማ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ የኾንሽ ፡ ጽዮን ፡ ይሉሻል ።

15 ፤ ከሰውም ፡ ማንም ፡ እስከማያልፍብሽ ፡ ድረስ ፡ የተተውሽና ፡ የተጠላሽ ፡ ነበርሽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የዘለዓለም ፡
ትምክሕትና ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ደስታ ፡ አደርግሻለኹ ።

16 ፤ የአሕዛብንም ፡ ወተት ፡ ትጠጫለሽ ፡ የነገሥታትንም ፡ ጡት ፡ ትጠቢያለሽ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ የያዕቆብ ፡
ኀይል ፥ መድኀኒትሽና ፡ ታዳጊሽ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቂያለሽ ።

17 ፤ በናስ ፡ ፋንታ ፡ ወርቅን ፥ በብረትም ፡ ፋንታ ፡ ብርን ፥ በዕንጨትም ፡ ፋንታ ፡ ናስን ፥ በድንጋይም ፡ ፋንታ ፡ ብረትን ፡



www.ethiopianorthodox.org

አመጣለኹ ። አለቃዎችሽንም ፡ ሰላም ፥ የበላይ ፡ ገዢዎችሽንም ፡ ጽድቅ ፡ አደርጋለኹ ፤

18 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በምድርሽ ፡ ውስጥ ፡ ግፍ ፥ በዳርቻሽም ፡ ውስጥ ፡ ጕስቍልናና ፡ ቅጥቃጤ ፡ አይሰማም ፤ ቅጥርሽን ፡
መዳን ፡ በሮችሽንም ፡ ምስጋና ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪያለሽ ፡

19 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ ብርሃንሽ ፥ አምላክሽም ፡ ክብርሽ ፡ ይኾናልና ፥ ፀሓይ ፡ በቀን ፡ ብርሃን ፡
አይኾንልሽም ፥ የጨረቃም ፡ ብርሃን ፡ በሌሊት ፡ አይበራልሽም ።

20 ፤ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ ብርሃንሽ ፡ ይኾናልና ፥ የልቅሶሽም ፡ ወራት ፡ ታልቃለችና ፡ ፀሓይሽ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡
አትጠልቅም ፡ ጨረቃሽም ፡ አይቋረጥም ።

21 ፤ ሕዝብሽም ፡ ኹሉ ፡ ጻድቃን ፡ ይኾናሉ ፤ እኔም ፡ እከብር ፡ ዘንድ ፡ የአታክልቴን ፡ ቍቃያ ፥ የእጄ ፡ ሥራ ፡ የምትኾን ፡
ምድሪቱንም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይወርሳሉ ።

22 ፤ ታናሹ ፡ ለሺሕ ፡ የኹሉም ፡ ታናሹ ፡ ለብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ ይኾናል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘመኑ ፡ ይህን ፡
አፋጥነዋለኹ ።

______________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 61 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 61 ።

1 ፤ የጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነው ፥ ለድኾዎች ፡ የምሥራችን ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡
ቀብቶኛልና ፤ ልባቸው ፡ የተሰበረውን ፡ እጠግን ፡ ዘንድ ፥ ለተማረኩትም ፡ ነጻነትን ፡ ለታሰሩትም ፡ መፈታትን ፡ እናገር ፡
ዘንድ ፡ ልኮኛል ።

2 ፤ የተወደደችውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዓመት ፡ አምላካችንም ፡ የሚበቀልበትን ፡ ቀን ፡ እናገር ፡
ዘንድ ፥ የሚያለቅሱትንም ፡ ኹሉ ፡ አጽናና ፡ ዘንድ ፤

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለክብሩ ፡ የተከላቸው ፡ የጽድቅ ፡ ዛፎች ፡ እንዲባሉ ፡ ለጽዮን ፡ አልቃሾች ፡ አደርግላቸው ፡
ዘንድ ፥ በዐመድ ፡ ፋንታ ፡ አክሊልን ፥ በልቅሶም ፡ ፋንታ ፡ የደስታን ፡ ዘይት ፥ በሐዘንም ፡ መንፈስ ፡ ፋንታ ፡ የምስጋናን ፡
መጐናጸፊያ ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ልኮኛል ።

4 ፤ ከጥንትም ፡ ዠምሮ ፡ ባድማ ፡ የነበሩትን ፡ ይሠራሉ ፡ ከቀድሞ ፡ የፈረሱትንም ፡ ያቆማሉ ፤ ባድማ ፡ የነበሩትንና ፡
ከብዙ ፡ ትውልድ ፡ በፊት ፡ የፈረሱትን ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይሠራሉ ።

5 ፤ መጻተኛዎችም ፡ ቆመው ፡ በጎቻችኹን ፡ ያሰማራሉ ፥ ሌላዎች ፡ ወገኖችም ፡ ዐራሾችና ፡ ወይም ፡ ጠባቂዎች ፡
ይኾኑላችኋል ።

6 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡ ትባላላችኹ ፥ ሰዎቹም ፡ የአምላካችን ፡ አገልጋዮች ፡ ብለው ፡
ይጠሯችኋል ፤ የአሕዛብን ፡ ሀብት ፡ ትበላላችኹ ፥ በክብራቸውም ፡ ትመካላችኹ ።

7 ፤ በዕፍረታችኹ ፡ ፋንታ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ይኾንላችኋል ፥ በውርደታችኹም ፡ ፋንታ ፡ ዕድል ፡ ፈንታችኹ ፡ ደስ ፡
ይላቸዋል ፤ ስለዚህ ፥ በምድራቸው ፡ ኹሉ ፡ ዕጥፍ ፡ ይገዛሉ ፥ የዘለዓለምም ፡ ደስታ ፡ ይኾንላቸዋል ።

8 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ የምወድ ፡ ስርቆትንና ፡ በደልን ፡ የምጠላ ፡ ነኝ ፤ ፍዳቸውንም ፡ በእውነት ፡
እሰጣቸዋለኹ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደርጋለኹ ።

9 ፤ ዘራቸውም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፥ ልጆቻቸውም ፡ በወገኖች ፡ መካከል ፡ የታወቁ ፡ ይኾናሉ ፤ ያያቸው ፡ ኹሉ ፡
እግዚአብሔር ፡ የባረካቸው ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ይገነዘባል ።

10 ፤ አክሊልን ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ ሙሽራ ፥ በጌጥ ፡ ሽልማቷም ፡ እንዳጌጠች ፡ ሙሽራ ፥ የማዳንን ፡ ልብስ ፡
አልብሶኛልና ፥ የጽድቅንም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ደርቦልኛልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ ነፍሴም ፡
በአምላኬ ፡ ሐሤት ፡ ታደርጋለች ።

11 ፤ ምድርም ፡ ቡቃያዋን ፡ እንደምታወጣ ፥ ገነትም ፡ ዘሩን ፡ እንደሚያበቅል ፥ እንዲሁ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጽድቅንና ፡ ምስጋናን ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ያበቅላል ።



www.ethiopianorthodox.org

___________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 62 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 62 ።

1 ፤ ስለ ፡ ጽዮን ፡ ዝም ፡ አልልም ፥ ስለ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ጸጥ ፡ አልልም ፥ ጽድቋ ፡ እንደ ፡ ጸዳል ፡ መዳኗም ፡
እንደሚበራ ፡ ፋና ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ።

2 ፤ አሕዛብም ፡ ጽድቅሽን ፡ ነገሥታትም ፡ ኹሉ ፡ ክብርሽን ፡ ያያሉ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ አፍ ፡ በሚጠራበት ፡ በዐዲሱ ፡
ስም ፡ ትጠሪያለሽ ።

3 ፤ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የክብር ፡ አክሊል ፥ በአምላክሽም ፡ እጅ ፡ የመንግሥት ፡ ዘውድ ፡ ትኾኛለሽ ።

4 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ። የተተወች ፡ አትባዪም ፤ ምድርሽም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ። ውድማ ፡ አትባልም ፤ ነገር ፡
ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ባንቺ ፡ ደስ ፡ ብሎታልና ፥ ምድርሽም ፡ ባል ፡ ታገባለችና ፡ አንቺ ። ደስታዬ ፡ የሚኖርባት ፡
ትባያለሽ ፡ ምድርሽም ፦ ባል ፡ ያገባች ፡ ትባላለች ።

5 ፤ ጕልማሳም ፡ ድንግሊቱን ፡ እንደሚያገባ ፥ እንዲሁ ፡ ልጆችሽ ፡ ያገቡሻል ፤ ሙሽራም ፡ በሙሽራዪቱ ፡ ደስ ፡
እንደሚለው ፥ እንዲሁ ፡ አምላክሽ ፡ ባንቺ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

6 ፤ 7 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ጕበኛዎችን ፡ በቅጥርሽ ፡ ላይ ፡ አቁሜያለኹ ፤ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ከቶ ፡ ዝም ፡
አይሉም ፤ እናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምታሳስቡ ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ እስኪያጸና ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ምስጋና ፡
እስኪያደርጋት ፡ ድረስ ፡ አትረፉ ፡ ለርሱም ፡ ዕረፍት ፡ አትስጡ ።

8 ፤ እግዚአብሔር ፦ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በርግጥ ፡ ለጠላቶችሽ ፡ መብል ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እኽልሽን ፡
አልሰጥም ፥ መጻተኛዎችም ፡ የደከምኽበትን ፡ ወይንሽን ፡ አይጠጡም ፤

9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰበሰቡት ፡ ይበሉታል ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ያመሰግናሉ ፥ ያከማቹትም ፡ በመቅደሴ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡
ይጠጡታል ፡ ብሎ ፡ በቀኙና ፡ በኀይሉ ፡ ክንድ ፡ ምሏል ።

10 ፤ ዕለፉ ፥ በበሮች ፡ በኩል ፡ ዕለፉ ፤ የሕዝቡንም ፡ መንገድ ፡ ጥረጉ ፤ አዘጋጁ ፥ ጐዳናውን ፡ አዘጋጁ ፥ ድንጋዮቹንም ፡
አስወግዱ ፤ ለአሕዛብም ፡ ዓላማ ፡ አንሡ ።

11 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለምድር ፡ ዳርቻ ፡ ዐዋጅ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነግሯል ፦ ለጽዮን ፡
ልጅ ፦ እንሆ ፥ መድኀኒትሽ ፡ ይመጣል ፤ እንሆ ፥ ዋጋው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሥራውም ፡ በፊቱ ፡ አለ ፡ በሏት ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፦ የተቤዣቸው ፥ የተቀደሰ ፡ ሕዝብ ፡ ብለው ፡ ይጠሯቸዋል ፤ አንቺም ፦ የተፈለገች ፡
ያልተተወችም ፡ ከተማ ፡ ትባያለሽ ።

___________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 63 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 63 ።

1 ፤ ይህ ፡ ከኤዶምያስ ፥ ልብሱም ፡ የቀላ ፡ ከባሶራ ፡ የሚመጣ ፥ አለባበሱ ፡ ያማረ ፥ በጕልበቱ ፡ ጽናት ፡ የሚራመድ ፡
ማን ፡ ነው ፧ በጽድቅ ፡ የምናገር ፡ ለማዳንም ፡ የምበረታ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

2 ፤ ቀሚስኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቀላ ፧ ልብስኽስ ፡ በወይን ፡ መጥመቂያ ፡ እንደሚረግጥ ፡ ሰው ፡ ልብስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መሰለ ፧

3 ፤ መጥመቂያውን ፡ ብቻዬን ፡ ረግጫለኹ ፥ ከአሕዛብም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አልነበረም ፤ በቍጣዬ ፡
ረገጥኋቸው ፡ በመዓቴም ፡ ቀጠቀጥኋቸው ፤ ደማቸውም ፡ በልብሴ ፡ ላይ ፡ ተረጭቷል ፥ ልብሴንም ፡ ኹሉ ፡
አሳድፌያለኹ ።

4 ፤ የምበቀልበት ፡ ቀን ፡ በልቤ ፡ ነውና ፥ የምቤዥበትም ፡ ዓመት ፡ ደርሷልና ።

5 ፤ ተመለከትኹ ፥ የሚረዳም ፡ አልተገኘም ፤ የሚያግዝም ፡ አልነበረምና ፡ ተደነቅኹ ፤ ስለዚህ ፥ የገዛ ፡ ክንዴ ፡
መድኀኒት ፡ አመጣልኝ ፥ ቍጣዬም ፡ ርሱ ፡ አገዘኝ ።

6 ፤ በቍጣዬም ፡ አሕዛብን ፡ ረገጥኹ ፡ በመዓቴም ፡ ቀጠቀጥኋቸው ፥ ደማቸውንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አፈሰስኹት ።



www.ethiopianorthodox.org

7 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ ኹሉ ፣ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፣ እንደ ፡ ምሕረቱና ፡
እንደ ፡ ቸርነቱም ፡ ብዛት ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ትልቅ ፡ በጎነት ፡ አሳስባለኹ ።

8 ፤ ርሱም ፦ በእውነት ፡ ሕዝቤ ፣ ሐሰትን ፡ የማያደርጉ ፡ ልጆች ፣ ናቸው ፡ አለ ፤ መድኀኒትም ፡ ኾነላቸው ።

9 ፤ በጭንቃቸው ፡ ኹሉ ፡ ርሱ ፡ ተጨነቀ ፣ የፊቱም ፡ መልአክ ፡ አዳናቸው ፤ በፍቅሩና ፡ በርኅራኄውም ፡
ተቤዣቸው ፣ በቀደመውም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ አንሥቶ ፡ ተሸከማቸው ።

10 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ዐመፁ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈሱንም ፡ አስመረሩ ፤ ስለዚህ ፣ ተመልሶ ፡ ጠላት ፡ ኾናቸው ፣ ርሱም ፡
ተዋጋቸው ።

11 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የቀደመውን ፡ ዘመን ፡ ዐሰበ ። የበጎቹን ፡ እረኛ ፡ ከባሕሩ ፡ ያወጣው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡
ያለ ፧ ቅዱስ ፡ መንፈሱንም ፡ በመካከላቸው ፡ ያኖረ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለ ፧

12 ፤ የከበረውንም ፡ ክንድ ፡ በሙሴ ፡ ቀኝ ፡ ያስኼደ ፣ ለራሱም ፡ የዘለዓለምን ፡ ስም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ውሃውን ፡
በፊታቸው ፡ የከፈለ ፣

13 ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ እንደሚያልፍ ፡ ፈረስ ፣ በቀላይ ፡ ውስጥ ፡ ያለዕንቅፋት ፡ ያሳለፋቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለ ፧

14 ፤ ወደ ፡ ሸለቆ ፡ እንደሚወርዱ ፡ ከብቶች ፣ እንዲሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ዕረፍት ፡
አመጣቸው ፤ እንዲሁም ፡ ለራስኽ ፡ የከበረ ፡ ስም ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝብን ፡ መራኽ ።

15 ፤ ከሰማይ ፡ ተመልከት ፣ ከቅዱስነትኽና ፡ ከክብርኽም ፡ ማደሪያ ፡ ጐብኝ ፤ ቅንአትኽና ፡ ኀይልኽስ ፡ ወዴት ፡
ነው ፧ ለኔም ፡ የኾነው ፡ የልብኽ ፡ ናፍቆትና ፡ ርኅራኄኽ ፡ ተከለከለ ።

16 ፤ አብርሃም ፡ ባያውቀን ፡ እስራኤልም ፡ ባይገነዘበን ፡ አንተ ፡ አባታችን ፡ ነኽ ፤ አቤቱ ፣ አንተ ፡ አባታችን ፡
ነኽ ፣ ስምኽም ፡ ከዘለዓለም ፡ ታዳጊያችን ፡ ነው ።

17 ፤ አቤቱ ፣ ከመንገድኽ ፡ ለምን ፡ አሳትኸን ፧ እንዳንፈራኽም ፡ ልባችንን ፡ ለምን ፡ አጸናኽብን ፧ ስለ ፡ ባሪያዎችኽ ፡
ስለ ፡ ርስትኽ ፡ ነገዶች ፡ ተመለስ ።

18 ፤ የተቀደሰው ፡ ሕዝብኽ ፡ መቅደስኽን ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ወረሱት ፤ ጠላቶቻችንም ፡ ረግጠውታል ።

19 ፤ ከዘለዓለም ፡ እንዳልገዛኸን ፡ በስምኽም ፡ እንዳልተጠራን ፡ ኾነናል ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፣ ምዕራፍ ፡ 64 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 64 ።

1 ፤ ሰማዮችን ፡ ቀደኽ ፡ ምነው ፡ ብትወርድ! ተራራዎችም ፡ ምነው ፡ ቢናወጡ!

2 ፤ እሳት ፡ ጭራሮውን ፡ እንደሚያቃጥል ፣ እሳትም ፡ ውሃውን ፡ እንደሚያፈላ ፣ ስምኽ ፡ ለጠላቶችኽ ፡ ይገለጥ ፡
ዘንድ ፣ አሕዛብም ፡ በፊትኽ ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ዘንድ ።

3 ፤ ያልተጠባበቅነውን ፡ የክብርኽን ፡ ሥራ ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፣ ወረድኽ ፡ ተራራዎችም ፡ በፊትኽ ፡ ተንቀጠቀጡ ።

4 ፤ ሰዎች ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ለሚጠብቁኽ ፣ ከምትሠራላቸው ፡ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክን ፡
አልሰሙም ፣ በጆሯቸውም ፡ አልተቀበሉም ፣ ዐይንም ፡ አላየችም ።

5 ፤ ጽድቅን ፡ የሚያደርገውን ፣ በመንገዶችኽም ፡ የሚያስቡኽን ፡ ትገናኛቸዋለኽ ። እንሆ ፣ አንተ ፡ ተቈጣኽ ፣ እኛም ፡
ኀጢአት ፡ ሠራን ፤ ስለዚህም ፡ ተሳሳትን ።

6 ፤ ኹላችን ፡ እንደ ፡ ርኩስ ፡ ሰው ፡ ኾነናል ፣ ጽድቃችንም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ነው ፤ ኹላችንም ፡
እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረግፈናል ፣ በደላችንም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ወስዶናል ።

7 ፤ ስምኽንም ፡ የሚጠራ ፣ አንተንም ፡ ሊይዝ ፡ የሚያስብ ፡ የለም ፤ ፊትኽንም ፡ ከእኛ ፡ ሰውረኻል ፣ በኀጢአታችንም ፡
አጥፍተኸናል ።

8 ፤ አኹን ፡ ግን ፣ አቤቱ ፣ አንተ ፡ አባታችን ፡ ነኽ ፤ እኛ ፡ ጭቃ ፡ ነን ፡ አንተም ፡ ሠሪያችን ፡ ነኽ ፣ እኛም ፡ ኹላችን ፡



www.ethiopianorthodox.org

የእጅኽ ፡ ሥራ ፡ ነን ።

9 ፤ አቤቱ ፥ እጅግ ፡ አትቈጣ ፥ ለዘለዓለምም ፡ ኀጢአትን ፡ አታስብ ፤ እንሆ ፥ እባክኽ ፥ ተመልከት ፥ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ሕዝብኽ ፡ ነን ።

10 ፤ የተቀደሱ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነዋል ፤ ጽዮን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ውድማ ፡ ኾናለች ።

11 ፤ አባቶቻችን ፡ አንተን ፡ ያመሰገኑበት ፡ የተቀደሰና ፡ የተዋበ ፡ ቤታችን ፡ በእሳት ፡ ተቃጥሏል ፥ ያማረውም ፡ ስፍራችን ፡ ኹሉ ፡ ፈርሷል ።

12 ፤ አቤቱ ፥ በእውኑ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ትታገሣለኽን ፧ ዝምስ ፡ ትላለኽን ፧ አጥብቀኽስ ፡ ታስጨንቀናለኽን ፧

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 65 ።

ምዕራፍ ፡ 65 ።

1 ፤ ላልጠየቁኝ ፡ ተገለጥኹ ፥ ላልፈለጉኝም ፡ ተገኘኹ ፤ በስሜም ፡ ያልተጠራውን ፡ ሕዝብ ፦ እንሆኝ ፥ እንሆኝ ፡ አልኹት ።

2 ፤ መልካም ፡ ባልኾነው ፡ መንገድ ፥ ዐሳባቸውን ፡ እየተከተሉ ፥ ወደሚኼዱ ፡ ወደ ፡ ዐመፀኛ ፡ ሕዝብ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ እጆቼን ፡ ዘረጋኹ ።

3 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ዘወትር ፡ የሚያስቈጡኝ ፡ ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በአትክልት ፡ ውስጥ ፡ የሚሠዉ ፡ በጡብም ፡ ላይ ፡ የሚያጥኑ ፥

4 ፤ በመቃብርም ፡ መካከል ፡ የሚቀመጡ ፥ በስውርም ፡ ስፍራ ፡ የሚያድሩ ፥ የዕሪያ ፡ ሥጋም ፡ የሚበሉ ፡ ናቸው ። የረከሰው ፡ መረቅ ፡ በዕቃቸው ፡ ውስጥ ፡ አለ ።

5 ፤ እነርሱም ፦ ለራስኽ ፡ ቁም ፥ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ይልቅ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አትቅረብ ፡ ይላሉ ፤ እነዚህ ፡ በአፍንጫዬ ፡ ዘንድ ፡ ጢስ ፡ ቀኑንም ፡ ኹሉ ፡ የምትነድ ፡ እሳት ፡ ናቸው ።

6 ፤ እንሆ ፥ በፊቴ ፡ ተጽፏል ፦ ኀጢአታችኹና ፡ የአባቶቻችኹን ፡ ኀጢአት ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ብብታቸው ፡ ፍዳ ፡ አድርጌ ፡ እመልሳለኹ ፡ እንጂ ፡ ዝም ፡ አልልም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

7 ፤ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ ስላጠኑ ፥ በኰረብታዎችም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሰደቡኝ ፥ ስለዚህ ፡ አስቀድመው ፡ የሠሩትን ፡ ሥራቸውን ፡ በብብታቸው ፡ እሰፍራለኹ ።

8 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወይን ፡ በዘለላው ፡ በተገኘች ፡ ጊዜ ፦ በረከት ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ አለና ፡ አታጥፉት ፡ እንደሚባለው ፥ ኹሉን ፡ እንዳላጠፋ ፡ ስለ ፡ ባሪያዎቼ ፡ እንዲሁ ፡ አደርጋለኹ ።

9 ፤ ከያዕቆብ ፡ ዘርን ፡ ከይሁዳም ፡ ተራራዎቼን ፡ የሚወርሰውን ፡ አወጣለኹ ፤ እኔም ፡ የመረጥኋቸው ፡ ይወርሷታል ፥ ባሪያዎቼም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ።

10 ፤ ሳሮንም ፡ የበጎች ፡ ማሰማሪያ ፥ የዐኮርም ፡ ሸለቆ ፡ የላሞች ፡ መመሰጊያ ፡ ለፈለጉኝ ፡ ሕዝቤ ፡ ይኾናል ።

11 ፤ እናንተን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተዋችኹትን ፥ ቅዱሱንም ፡ ተራራዬን ፡ የረሳችኹትን ፥ ጕድ ፡ ለተባለ ፡ ጣዖትም ፡ ማእድ ፡ ያዘጋጃችኹትን ፥ ዕድል ፡ ለተባለ ፡ ጣዖትም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ የቀዳችኹትን ፥

12 ፤ ዕድላችኹን ፡ ለሰይፍ ፡ አደርገዋለኹ ፥ ኹላችኹም ፡ ለመታረድ ፡ ትጐነበሳላችኹ ፤ በፊቴም ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አደረጋችኹ ፥ ያልወደድኹትንም ፡ መረጣችኹ ፡ እንጂ ፡ በጠራኹ ፡ ጊዜ ፡ አልመለሳችኹልኝምና ፥ በተናገርኹም ፡ ጊዜ ፡ አልሰማችኹኝምና ።

13 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ይበላሉ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ትራባላችኹ ፤ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ይጠጣሉ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ትጠማላችኹ ፤ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ታፍራላችኹ ፤

14 ፤ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ከልባቸው ፡ ደስታ ፡ የተነሣ ፡ ይዘምራሉ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ከልባችኹ ፡ ሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ትጮኻላችኹ ፥ መንፈሳችኹም ፡ ስለ ፡ ተሰበረ ፡ ወዮ ፡ ትላላችኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

15 ፤ ስማችኹንም ፡ ለተመረጡት ፡ ሕዝቤ ፡ ርግማን ፡ አድርጋችኹ ፡ ትተዋላችኹ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይገድላችኋል ፥ ባሪያዎቹንም ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ይጠራቸዋል ።

16 ፤ እንዲሁም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የተባረከ ፡ በእውነት ፡ አምላክ ፡ ይባረካል ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ የማለ ፡ በእውነት ፡ አምላክ ፡ ይምላል ፤ የቀድሞው ፡ ጭንቀት ፡ ተረስቷልና ፥ ከዐይኔም ፡ ተሰውሯልና ።

17 ፤ እንሆ ፥ ዐዲስ ፡ ሰማይና ፡ ዐዲስ ፡ ምድር ፡ እፈጥራለኹና ፤ የቀደሙትም ፡ አይታሰቡም ፥ ወደ ፡ ልብም ፡ አይገቡም ።

18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፈጠርኹት ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ለዘለዓለምም ፡ ሐሤት ፡ አድርጉ ፤ እንሆ ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ ለሐሤት ፥ ሕዝቧንም ፡ ለደስታ ፡ እፈጥራለኹና ።

19 ፤ እኔም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሐሤት ፡ አደርጋለኹ ፡ በሕዝቤም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ የልቅሶ ፡ ድምፅና ፡ የዋይታ ፡ ድምፅ ፡ አይሰማባትም ።

20 ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ የሚኖር ፡ ሕፃን ፥ ወይም ፡ ዕድሜውን ፡ ያልፈጸመ ፡ ሽማግሌ ፡ አይገኝም ፤ ጕልማሳው ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ኾኖት ፡ ይሞታልና ፥ ኀጢአተኛውም ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ኾኖት ፡ የተረገመ ፡ ይኾናልና ።

21 ፤ ቤቶችንም ፡ ይሠራሉ ፡ ይቀመጡባቸውማል ፤ ወይኑንም ፡ ይተክላሉ ፡ ፍሬውንም ፡ ይበላሉ ።

22 ፤ ሌላ ፡ እንዲቀመጥበት ፡ አይሠሩም ፥ ሌላም ፡ እንዲበላው ፡ አይተክሉም ፤ የሕዝቤ ፡ ዕድሜ ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ዕድሜ ፡ ይኾናልና ፥ እኔም ፡ የመረጥኋቸው ፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ።

23 ፤ እነርሱ ፡ ከነልጆቻቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቡሩካን ፡ ዘር ፡ ናቸውና ፥ በከንቱ ፡ አይደክሙም ፡ ለጥፋትም ፡ አይወልዱም ።

24 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ ሳይጠሩ ፡ እመልስላቸዋለኹ ፥ ገናም ፡ ሲናገሩ ፡ እሰማለኹ ።

25 ፤ ተኵላና ፡ ጠቦት ፡ በአንድነት ፡ ይሰማራሉ ፥ አንበሳም ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ገለባ ፡ ይበላል ፥ የእባብም ፡ መብል ፡ ትቢያ ፡ ይኾናል ። በተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ ኹሉ ፡ አይጐዱም ፥ አያጠፉምም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

__________________ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 66 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 66 ።

1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነው ፥ ምድርም ፡ የእግሬ ፡ መረገጫ ፡ ናት ፤ የምትሠሩልኝ ፡ ቤት ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ፧ የማርፍበትስ ፡ ስፍራ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

2 ፤ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ እጄ ፡ ሠርታለችና ፡ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የእኔ ፡ ናቸው ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደዚህ ፡ ወደ ፡ ትሑት ፥ መንፈሱም ፡ ወደተሰበረ ፥ በቃሌም ፡ ወደሚንቀጠቀጥ ፡ ሰው ፡ እመለከታለኹ ።

3 ፤ በሬን ፡ የሚያርድልኝ ፡ ሰውን ፡ እንደሚገድል ፡ ነው ፤ ጠቦትንም ፡ የሚሠዋ ፡ የውሻውን ፡ ዐንገት ፡ እንደሚሰብር ፡ ነው ፤ የእኽልን ፡ ቍርባን ፡ የሚያቀርብ ፡ የዕሪያን ፡ ደም ፡ እንደሚያቀርብ ፡ ነው ፤ ዕጣንን ፡ የሚያጥን ፡ ጣዖትን ፡ እንደሚባርክ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የገዛ ፡ መንገዳቸውን ፡ መረጡ ፤ ነፍሳቸውም ፡ በርኵሰታቸው ፡ ደስ ፡ ይላታል ፤

4 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የተሳለቀባቸውን ፡ እመርጣለኹ ፥ የፈሩትንም ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለኹ ፤ በፊቴ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አደረጉ ፥ ያልወደድኹትንም ፡ መረጡ ፡ እንጂ ፡ በጠራኹ ፡ ጊዜ ፡ አልመለሱልኝምና ፥ በተናገርኹም ፡ ጊዜ ፡ አልሰሙኝምና ።

5 ፤ በቃሉ ፡ የምትንቀጠቀጡ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፦ የጠሏችኹ ፡ ስለ ፡ ስሜም ፡ ያባረሯችኹ ፡ ወንድሞቻችኹ ፦ ደስታችኹን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ብለዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ያፍራሉ ።

6 ፤ የጩኸት ፡ ድምፅ ፡ ከከተማ ፥ ድምፅም ፡ ከመቅደስ ፥ በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ ፍዳን ፡ የሚያመጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

7 ፤ ሳታምጥ ፡ ወለደች ፤ ምጥም ፡ ሳያገኛት ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ።

8 ፤ ከቶ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሰምቷል ፧ እንዲህስ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ አይቷል ፧ በእውኑ ፡ አገር ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ታምጣለችን ፡ ወይስ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ ይወለዳልን ፡ ጽዮን ፡ እንዳማጠች ፡ ወዲያው ፡ ልጆቿን ፡ ወልዳለችና ።

9 ፤ በእውኑ ፡ ወደ ፡ መውለድ ፡ የማደርስ ፡ እኔ ፡ አላስወልድምን ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የማስወልድስ ፡ ማሕፀንን ፡
እኔ ፡ እዘጋለኍን ፡ ይላል ፡ አምላክሽ ።

10 ፤ እናንተ ፡ የምትወድዋት ፡ ኹሉ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ጋራ ፡ ሐሤትን ፡ አድርጉ ፥ ስለ ፡ ርሷም ፡ ደስ ፡
ይበላችኹ ፤ እናንተም ፡ የምታለቅሱላት ፡ ኹሉ ፥ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ በደስታ ፡ ሐሤትን ፡ አድርጉ ፥

11 ፤ ትጠቡ ፡ ዘንድ ፡ ከማጽናናቷም ፡ ጡት ፡ ትጠግቡ ፡ ዘንድ ፤ እጅግ ፡ ጠጥታችኹ ፡ በክብሯ ፡ ሙላት ፡ ደስ ፡
ይላችኹ ፡ ዘንድ ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ሰላምን ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፥ የአሕዛብንም ፡ ክብር ፡ እንደሚጐርፍ ፡
ፈሳሽ ፡ እመልስላታለኹ ፤ ከዚያም ፡ ትጠባላችኹ ፥ በጫንቃ ፡ ላይ ፡ ይሸከሟችኋል ፡ በጕልበትም ፡ ላይ ፡ እያስቀመጡ ፡
ያቀማጥሏችኋል ።

13 ፤ እናት ፡ ልጇን ፡ እንደምታጽናና ፡ እንዲሁ ፡ አጽናናችኋለኹ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ውስጥ ፡ ትጽናናላችኹ ።

14 ፤ ታያላችኹ ፥ ልባችኹም ፡ ሐሤት ፡ ታደርጋለች ፥ ዐጥንታችኹም ፡ እንደ ፡ ለምለም ፡ ሣር ፡
ትበቅላለች ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ ለሚፈሩት ፡ ትታወቃለች ፥ በጠላቶቹም ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ።

15 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ መዓቱን ፡ በቍጣ ፥ ዘለፋውንም ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ከእሳት ፡ ጋራ ፡
ይመጣል ፥ ሠረገላዎቹም ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይኾናሉ ።

16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በእሳትና ፡ በሰይፉ ፡ ይፈርዳል ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ተወግተው ፡
የሞቱት ፡ ይበዛሉ ።

17 ፤ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ አንዱን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ገነቱ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ሰውነታቸውን ፡ የሚቀድሱና ፡
የሚያነጹ ፥ የዕሪያንም ፡ ሥጋ ፡ አስጸያፊ ፡ ነገርንም ፡ ዐይጥንም ፡ የሚበሉ ፡ በአንድነት ፡ ይጠፋሉ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

18 ፤ ሥራቸውንና ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዐውቄያለኹና ፤ አሕዛብንና ፡ ልሳናትን ፡ ኹሉ ፡ የምሰበስብበት ፡ ጊዜ ፡
ይደርሳል ፥ እነርሱም ፡ ይመጣሉ ፡ ክብሬንም ፡ ያያሉ ።

19 ፤ በመካከላቸውም ፡ ምልክት ፡ አደርጋለኹ ፥ ከነርሱም ፡ የዳኑትን ፡ ዝናዬን ፡ ወዳልሰሙ ፥ ክብሬንም ፡ ወዳላዩ ፡ ወደ ፡
አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ወደ ፡ ፉጥ ፡ ወደ ፡ ሉድ ፡ ወደ ፡ ሞሳሕ ፡ ወደ ፡ ቶቤል ፡ ወደ ፡ ያዋን ፡ በሩቅ ፡ ወዳሉ ፡ ደሴቶች ፡
እልካቸዋለኹ ፥ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ክብሬንም ፡ ይናገራሉ ።

20 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቍርባናቸውን ፡ በጥሩ ፡ ዕቃ ፡ አድርገው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
እንደሚያመጡ ፥ እንዲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ ኹሉ ፥ በፈረሶችና ፡
በሠረገላዎች ፥ በዐልጋዎችና ፡ በበቅሎዎች ፡ በጠያር ፡ ግመሎችም ፡ ላይ ፡ አድርገው ፥ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡
ወደተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያመጧቸዋል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

21 ፤ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ እንዲኾኑ ፡ ከነርሱ ፡ እወስዳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

22 ፤ እኔ ፡ የምሠራቸው ፡ ዐዲስ ፡ ሰማይና ፡ ዐዲስ ፡ ምድር ፡ ከፊቴ ፡ ጸንተው ፡ እንደሚኖሩ ፥ እንዲሁ ፡ ዘራችኹና ፡
ስማችኹ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

23 ፤ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ በየመባቻውና ፡ በየሰንበቱ ፡ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ በፊቴ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ዘወትር ፡
ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

24 ፤ ወጥተውም ፡ በእኔ ፡ ያመፁብኝን ፡ ሰዎች ፡ ሬሳቸውን ፡ ያያሉ ፤ ትላቸው ፡ አይሞትምና ፥ እሳታቸውም ፡
አይጠፋምና ፤ ለሥጋ ፡ ለባሽም ፡ ኹሉ ፡ አስጸያፊ ፡ ነገር ፡ ይኾናሉ ፨



www.ethiopianorthodox.org